


Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

All Rights Reserved

የመጀመሪያ ዕትም፡- ታህሳስ 2001

የኮምፒዩተር ጽሕፈት፡- ወ/ሪት ሸዋአነሰሽ ደሳለኝ

ድርሠቱን ወደ እንግሊዝኛ የመለሰው፡- Alan R. Clarke

Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

# ቅድመ ታሪክ

አልኬሚስቱ ከሲራራ ነጋዴዎቹ አንዱ ገዝቶ ያመጣውን መጽሐፍ አነሳ፡፡ ገፆቹን ሲገላልጥ የናርሲስን ታሪክ አገኘ፡፡

አልኬሚስቱ ስለ ናርሲስ የሚነገረውን አፈ ታሪክ ያውቀዋል፡፡ ናርሲስ በየእለቱ ከሐይቁ አጠገብ ተቀምጦ በራሱ ቁንጅና ሲመሰጥ ውሎ የሚያድር ወጣት መሆኑንም ያውቃል፡፡ ከራሱ ጋር በፍቅር ከመውደቁ ብዛት አንድ ጠዋት ሐይቁ ውስጥ ወድቆ ሰጥሟል፡፡ እሱ አወደቀበት ሥፍራ አንዲት አበባ አብባ ናርሲስ ተብላ በስሙ ተጠራች፡፡

ይሄ ግን ደራሲ ታሪኩን የቋጨበት መንገድ አይደለም፡፡

ናርሲስ ሲሞት የጫካው እንስት አማልክት ተገልጠው ቀድሞ ኩልል ያለ ቀዝቃዛ ውሃ የነበረበትንና አሁን ወደ ጨዋማ እንባነት በተለወጠ ውሃ የተሞላውን ሐይቅ አገኙት፡፡

'ለምን ታነባለህ?' አማልክቱ ጠየቁት፡፡



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

'ለሰናርሲስ አነባለሁ' ሐይቁ መለሰ፡፡

'ሆ! አንተ ለሰናርሲስ ማንባትህ ይገርማል' አሉት፤ 'ምክንያቱም እኛ ጫካ ለጫካ እሱን ለማግኘት ስንንከራተት አንተ ብቻ ነበርክ ቁንጅናውን በቅርበት ማየት የምትችለው፡፡'

'ግን ... ናርሲስ ቆንጆ ነበር?' ሐይቁ ጠየቀ፡፡

'ካንተ በላይ ደሞን ማን ያውቃል?' አማልክቱ ተገረሙ፡፡ 'ቀድሞውኑ እሱ ካንተው ጎን ሆኖ አልነበር እንዴ በውበቱ የሚመሰጠው!'

ሐይቁ ለጥቂት ሰከንዶች ጸጥ ብሉ ቆየ፡፡ በመጨረሻም እንዲህ አለ፡-

'ለሰናርሲስ አነባለሁ፤ ሆኖም ናርሲስ ቆንጆ እንደነበረ ልብ ብዬ አላውቅም፡፡ የማነባው እሱ ዳርቻዎቼ ላይ በርከክ በሚልባቸው ጊዜያት ሁሉ ዓይኖቹ ውስጥ የራሴን ቁንጅና ተንጸባርቆ አየው ስለነበር ነው፡፡'

'የሚጥም ታሪክ ነው!' ሲል አሰበ አልኬሚስቱ፡፡



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

# ክፍል አንድ

የብላቴናው ስም ሳንቲያጎ ነው። እሱ ወደ ተራቆተው የቤተክርስቲያን ቅጥር ሲደርስ ምሽቱ የቀኑን ብርሃን መጋረድ ጀምሮ ነበር። የቤተክርስቲያኑ ጣራ ከፈራረሰ ዘመናት አልፈውታል። ቤተልሄሙ በነበረበት ሥፍራ አንድ ግዙፍ የዋርካ ዛፍ ከበቀለበትም እንዲሁ።

እዚሁ ሲያድር ወስኖ በጎቹ ሁሉ በፈረሰው መግቢያ በኩል መግባታቸውን ካረጋገጠ በኋላ፣ መግቢያው ላይ የዛፍ ቅርንጫፎችን ረበረበ። መጠንቀቁ ተኩላዎች በጎቹን እንዳይበሉበት ሰግቶ አይደለም፤ እንዲያውም በአካባቢው የተኩላ ዘር የለም። ይልቅ አንዱ በግ በሌሊት ቢጠፋ በማግስቱ ቀኑን ሙሉ እሱን መፈለግ እንደሚኖርበት ስለሚያውቅ ነው።

ወለሉን በጃኬቱ ጠራርጎ በቅርቡ አንብቦ የጨረሰውን መጽሐፍ ትራሱ አድርጎ ተጋደመ። ወፍፍራም መጻሕፍት ማንበብ አለብኝ ብሎ ለራሱ ተናገረ፤ ምክንያቱም ከወፋፈሩ ቶሎ አያልቁበትም፤ በዚያ ላይ ምቹ ትራስ ይሆኑታል።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ነቅቶ በግማሽ በፈራረሰው ጣራ አጮልቆ ከዋክብትን ማየት እስኪችል ድረስ ገና ጨለማ ነበር፡፡

ትንሽ መተኛት እፈልጋለሁ ሲል አሰበ፡፡ ከሳምንት በፊትም እንደዚሁ ዓይነት ህልም አይቶ ነበር፤ ዛሬም ከእንቅልፉ የነቃው ህልሙ ሳያልቅ ነው፡፡

እሱ እንደነቃ አብዛኞቹ እንስሶች መነሳታቸውን ተገነዘበ፡፡ በትሩን ይዞ ተነሳና ያልነቁትን በጎቹን መቀስቀስ ጀመረ፡፡ ምግብና ውሃ ፍለጋ ገጠር ገጠሩን እየመራ ሁለት ዓመት አብሯቸው ያቆያቸውን የበጎቹን ህይወትና የእሱን ህይወት የሚያስተሳስር አንዳች ምስጢራዊ ኃይል ያለ ይመስላል፡፡ "ለእኔን እስኪያውቁ ድረስ ለምደውኛል" ሲል አጉተመተመ፡፡ ስለዚሁ ጉዳይ ለጥቂት ጊዜ አሰብ አደረገና ነገሩ በተቃራኒው ሲሆን እንደሚችልም ተገነዘበ፡- ከእነሱ ሰዓት ጋር የተላመደው እሱ እንደሆነስ?

ሆኖም አንዳንዶቹ ሳይነቁ ጥቂት ቆይተዋል፡፡ ብላቴናው እያንዳንዳቸውን በስም እየጠራ በቆልማማ በትሩ ነካ ነካ አደረጋቸው፡፡ በጎቹ እሱ የሚናገረውን እንደሚገነዘቡ ያምናል፡፡ ስለዚህም መጽሐፍ ሲያነብ የገረመውን ክፍል የሚያነብላቸው፣ ወይም አንድ እረኛ ስለሚኖርበት ብቸኝነት ወይም ስለሚኖረው ደስታ የሚያወራላቸው ጊዜ አለ፡፡ አንዳንዴ አልፏቸው ስለሚሄደው መንደሮች የተሰማውንም ለበጎቹ ይነግራቸዋል፡፡

ነገር ግን ካለፉት ጥቂት ቀናት ወዲህ የሚያወራላቸው ስለ አንድ ነገር ብቻ ሆኗል፡- ስለ ልጃገረዷ፤ ከአራት ቀን ጉዞ በኋላ በሚያገኙት መንገድ የሚኖረው የአንድ ነጋዴ ልጅ ስለሆነችው ልጃገረድ ብቻ፡፡ ይህን መንደር የጎበኘው አንድ ጊዜ ብቻ - ከአንድ ዓመት በፊት ነበረ፡፡ ነጋዴው የደረቅ



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

እቃዎች መሸጫና መለወጫ መደብር ባለቤት ሲሆን፣ እረኞች እንዳያጭበረብሩት ስለሚሰጋ በጎቻቸውን በፊት ለፊቱ እንዲሸልቱለት የሚጠይቅ ዓይነት ነው። እረኛው ስለዚህ ሰው ከአንድ ወዳጁ ሲሰማ በጎቹን ወደ እርሱ ወሰዳቸው።

* * *

"የበጎቼን ጸጉር መሸጥ እፈልጋለሁ" ለነጋዴው ነገረው።

መደብሩ በስራ ውክብክብ ያለበት ሰዓት ነበርና፣ ነጋዴው ብላቴናውን እስከ ከሰዓት እንዲጠብቀው ጠየቀው። ብላቴናውም በመደብሩ ደረጃዎች ላይ ተቀምጦ ከቦርሳው አንድ መጽሐፍ አወጣ።

"እረኞች ማንበብ እንደሚሆንላቸው አላውቅም ነበር" አለው የአንዲት ኮረዳ ድምጽ ከበስተኋላው።

የኮረዳዋ እንዲያው ፍስስ የሚል ኑግ የመሰለ ጸጉሯና የሙር ወራሪዎችን የሚያስታውሱ ዓይኖቿ ልጅቷ ከወደ አንዳሉዚያ መሆኗን ያሳብቁባታል።

"ለነገሩ ብዙ ጊዜ ከመጻህፍት የበለጠውን ትምህርት ከበጎቼ ነው የምቀስመው" መለሰላት። ሲያወሩ በቆዩባቸው ሁለት ሰዓታት የነጋዴው ልጅ ስለመሆኗና፣ በየእለቱ ያው ስለሆነው የመንደራቸው አኗኗር ነገረችው። ብላቴናው ደግሞ በተራው ስለ አንዳሉዚያ ገጠራማ አካባቢዎችና በየትናንሹ ከተማ ሲያልፍ ጆሮው ስለገቡ ወሬዎች አጫወታት። በጎቹን ከማናገሩ ይህችን ኮረዳ ወደ ማናገር መሸጋገሩ አስደሳች ነበር።

"ንባብን ከየት ተማርከው?" በመሐል ኮረዳዋ ጠየቀችው።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ሰው ሁሉ ከሚማርበት" አላት። "ከተማሪ ቤት።"

"እንግዲያውስ፣ ንባብን ካወቅህ ስለምን እረኛ ሆነህ ቀረህ?"

ብላቴናው ጥያቄዋን ለማረሳሳት ሞከረ። ልጅቷ ምክንያቱን እንደማትረዳለት እርግጠኛ ነው። ስለ ጉዞው ሲነግራት ብርሃን የሚረጩ ዓይኖቿ አንዴ በፍርሃት አንዳንዴም በመደነቅ እየሰፉ ይመጣሉ። ጊዜው መብረሩን ሲያስተውል ምነው ቀኑ ፈጽሞ ባላለቀ፣ ምነው አባቷ ፋታ አጥቶ ሰለት ቀን ባስጠበቀኝ ብሎ ተመኘ። ከዚህ በፊት ተሰምቶት የማያውቅ ነገር - በአንድ ሥፍራ ለዘላለም መኖር የመሻት ስሜት - እየተሰማው መሆኑን ተረዳ። ከባለዞማ ጸጉሯ ኮረዳ ጋር ከከረመ አዋዋል አስተዳደሩ ሙሉ በሙሉ ይለወጣል።

ሆኖም ነጋዴው መጥቶ የአራቱን በጎች ጸጉር እንዲሸልትለት ጠየቀው። ለጸጉሩ ከከፈለው በኋላ በሚቀጥለው ዓመት እንዲመለስም ጠየቀው።

* * *

ይኸው ዛሬ እንግዲህ ወደዚያ መንደር ለመድረስ የአራት ቀን መንገድ ብቻ ቀርቶታል። ከወዲሁ ልቡ በደስታ መምታት ጀምራለች፤ በዚያውም ልክ ተጨንቋል። ልጅቷ እኮ ፈጽሞ አታስታውሰው ይሆናል። አያሌ እረኞች የበግ ጸጉር ሊሸጡ ወደዚያ መደብር ይሄዳሉ፤ ይመለሳሉ።

"ይሄ አያሳስበኝም" አላቸው በጎቹን። "ሌሎች ሴቶች በሌሎች ሥፍራዎች ሞልተውልኛል።"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ልቡ ግን የጉዳዩን አሳሳቢነት ታውቃለች። እሱም ቢሆን እረኞች፣ እንደ ባህረኞችና እንደሲራራ ነጋዴዎች ምንጊዜም ጉዟቸውን የምታስረሳ አንዲት ሴት አንድ ከተማ ውስጥ እንደሚያገኙ ያውቃል።

ጎህ እየቀደደ ነውና፣ እረኛው በጎቹን ወደ ጸሐይ መውጫ አቅጣጫ ነዳቸው። እነሱማ ምንም ዓይነት ውሳኔ መወሰን የለባቸውም ብሎ አሰበ። ለዚህም መሆን አለበት ምን ጊዜም ከሥር ከሥሬ የሚሉት።

በጎቹን የሚያሳስቧቸው ብቸኛ ነገሮች ምግብና ውሃ ናቸው። ብላቴናው በምድረ አንዳሉዚያ ጥሩ ውሃና ሳር ያለበትን ሥፍራ እስካወቀ ድረስ ጓደኞቹ ይሆናሉ። እውነት ነው፤ ውሏቸው ተመሳሳይ ነው፤ ከጀምበር መውጣት እስከ ጀምበር መጥለቅ ድረስ የማያልቁ የሚመስሉ ሰዓታትን የተሞላ አዋዋል። ደግሞም በለጋነታቸው መጻሕፍትን ስላላነበቡ፣ ብላቴናው ስለከተሞች ገጽታ ሲነግራቸው አይገባቸውም። ልባቸው ምግብና መጠጣቸው ላይ ብቻ ያተኩራል፤ ሆኖም በለውጡ ጸጉራቸውን፣ ወዳጅነታቸውን፣ በሕይወት ዘመናቸው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜም ሥጋቸውን በልግስና ይሰጡታል።

አሁን እንደው ጭራቅ ብሆንና ሁሉንም አንድ በአንድ ልገድላቸው ብፈልግ፣ ሃሳቤ የሚገባቸው አብዛኞቹን ካረድኳቸው በኋላ ነው ብሎ አሰበ - ብላቴናው። ስለሚያምኑኝ በደመነፍሳቸው ላይ መተማመን ተስኗቸዋል፤ ምክንያቱም ምግብ ወደሚያገኙበት ሥፍራ እመራቸዋለሁና።

ብላቴናው በዚህ ሃሳቡ ተገረመ። ምናልባት ዋርካ የበቀለበት ያ ቤተክርስቲያን በመናፍስት ሳይወረር አልቀረም። ያንን ህልሙን መልሶ እንዲያየው ማድረጉ አንሶት አሁን ደግሞ ስለታማኝ ወዳጆቹ ክፉ አሳሰበው።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ትናንት ከእራት ካስተረፈው ወይን ትንሽ ተጎንጨለትና ጃኪቱን ወደ አካላቱ የበለጠ አስጠጋው።

ከጥቂት ሰዓታት በኋላ መሳዋ ስፔን ላይ እንቅልፍ የሚለቀው ከባድ የጸሐይ ሙቀት ሲመጣ ጃኬቱ ሸክም እንደሚሆንበት ቢያውቅም ጃኬቱን አልጠላውም።

ጃኬቱ ዓላማ አለው፤ ብላቴናውም እንደዚያው። ዓላማው መንገዝ ነው፤ እናም በአንዳሉዚያ በተዟዟረበት ሁለት ዓመት የአካባቢውን ከተሞች ሁሉ አውቋቸዋል። በዚህኛው ጉዞው ይሄ አንድ መናኛ እረኛ እንዴት ማንበብን እንዳወቀ ለልጃገረዷ ሊያስረዳት አቀደ። አስራ ስድስት ዓመት እስኪሞላው ድረስ መንፈሳዊ ትምህርት መማሩን ሊነግራት አሰበ። ገበሬዎቹ ቤተሰቦቹ ክህነትህን ተቀበልና መኩሪያ መመኪያ ሁነን ብለውት ነበረ። እነሱ ልክ እንደበጎቹ ለምግብና ለመጠጣቸው ያህል የሚሰሩ ነበሩ። ብላቴናው የላቲንና የስፓኒሽ ቋንቋ እንዲሁም ስነመለኮትን አውቋል። ነገር ግን ከልጅነቱ ጀምሮ ዓለምን ማወቅ ይፈልግ ነበር፤ ይሄ ደግሞ እግዚአብሔርን ከማወቅም ሆነ ስለሰው ልጅ ኃጢያቶች ከመማር በጣም ይበልጥበታል። አንድ ከሰዓት ከመንፈሳዊው ትምህርት ቤቱ ወላጆቹን ሊጠይቅ ወደ ቤት መጣና ድንገት ቄስ መሆን እንደማይፈልግና መንገዝ ብቻ እንደሚሻ ለአባቱ የመንገር ወኔ አገኘ።

* * *

— "ከመላው ዓለም የሚመጡ ሰዎች በመንደራችን ያልፋሉ፣ ልጅ" አለ አባትየው። "አዲስ ነገር ፍለጋ ይመጣሉ፤ ሆኖም እንዳመጣጣቸው



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ይመለሳሉ። ቤተመንግስቱን ለማየት ተራራውን ይወጣሉ፤ ከዚያም ድሮ ከዘንድሮ ይሻል ነበር ብለው ይደመድማሉ። ነጭ ፀጉር ወይም ጥቁር ቆዳ ቢኖራቸውም እነሱም እዚህ እንደሚኖሩት ሰዎች ናቸው።"

"እኔ ግን እነሱ በሚኖሩባቸው ከተሞች ውስጥ ያሉትን ቤተመንግስቶች ማየት እፈልጋለሁ።" ብላቴናው ምኞቱን ገለጸ።

"እነዚያ ሰዎች የእኛን አገር ሲያዩ ለዘላለም እዚሁ መኖር እንደሚፈልጉ ይናገራሉ።" አባትየው ቀጠለ።

"እንግዲያውስ አገራቸውንና አኗኗራቸውን ማየት እፈልጋለሁ" አለው ብላቴናው።

"እዚህ የሚመጡት ሰዎች ብዙ ገንዘብ ስላላቸው የጉዟቸውን ወጪ መሸፈን ይችላሉ" አለ አባትየው። "ከእኛ መሐል ግን የሚጓዙት እረኞች ብቻ ናቸው።"

"ታዲያ እረኛ እሆናለሁ'ኒ"

አባትየው ምንም መናገር አልቻለም። በማግስቱ ሶስት የስፔን የጥንት የወርቅ ሳንቲሞች ጨምሮበት አንድ ቦርሳ ሰጠው።

"እነዚህን አንድ ጊዜ ማሳ ውስጥ አገኘኋቸውና ላንተ ሳወርስህ ፈልጌ አስቀመጥኳቸው። ግና አሁን በጎች ግዛባቸው። በጎችህን አሰማራ፤ አንድ ቀን የእኛይቱ ገጠር ምድር ምርጥ፣ የኛዎቹ ሴቶች ወደር የለሽ ቆንጆዎች መሆናቸው ይገለጥልሃል።"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

አባት ልጁን መረቀው። ብላቴናው የአባቱ ዓይኖች ውስጥ ለአሥርት ዓመታት የሚጠጣ ውሃ፣ የሚበላ ምግብ፣ እድሜ ልኩን የሚተኛበትን ሥፍራ ለማግኘት በሚያደርገው ትግል ውስጥ የተቀበረ የመሔድ፣ የመጓዝ፣ ዓለምን የማወቅ ጉጉት ተመለከተ።

* * *

አድማሱ ቀይ ቀለም በሰሱ የተረጨበት ሸራ መስሎ ቀየና ድንገት ፀሐይ ብቅ አለች። ብላቴናው ከአባቱ ጋር አድርጎት የነበረውን ውይይት እያስታወሰ ደስታ ተሰማው። ብዙ ህንፃዎችን አይቷል፤ ብዙ ሴቶችንም አግኝቷል (አንዳቸውም ግን ለረጅም ጊዜ ሳያዩት የጓጓላትን ልጃገረድ አያክሉም)። ጃኬት፣ ሌላ መጽሐፍ የሚለውጥበት መጽሐፍ እንዲሁም አንድ መንጋ በጎች አሉት። ከዚህ ሁሉ በላይ ግን በየቀኑ ህልሙን መኖር ይችላል። የአንዳሉዚያ መስኮች ቢሰለቹት፣ በጎቹን ይሸጥና ወደ ባህር ይሄዳል። ባህሩ ቢበቃው ደግሞ ሌሎች ከተሞች፣ ሌሎች ሴቶች እና ሌሎች የመደሰቻ እድሎች እንዳሉትም ያውቃል። መንፈሳዊው ትምህርት ቤት ውስጥ እግዚአብሔርን አላገኘሁትም ነበር ብሎ አሰበ ፀሐይዋ ስትወጣ እየተመለከተ።

በተቻለው መጠን ለጉዞው አዳዲስ መንገዶችን ይፈልጋል። ብዙ ጊዜ በአካባቢያው ቢመላለስም እዚያ የፈራረሰ ቤተክርስቲያን ሄዶ አያውቅም። ዓለም ግዙፍና የማታሰለች ናት፤ እሱ የሚጠበቅበት በጎቹን የሆነ አቅጣጫ እንዲይዙ መተው ነው፤ ከዚያ ሌሎች አስደሳች አስገራሚ ነገሮችን ያገኛል። ችግሩ በጎቹ ከዚህ በፊት ሄደውበት በማያውቁት መንገድ ላይ መሆናቸውን



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

እንኳን አይገነዘቡም። የመስኮቹን አዲስነት የወቅቱንም መለዋወጥ ልብ አይሉም። የሚያስቡት ስለ ምግብና ስለ ውሃቸው ብቻ ነው።

ሁላችንም እንዲሁ ሳንሆን አንቀርም፤ ብላቴናው በሃሳብ ተዋጠ። የነጋዴውን ልጅ ካገኘኂት ወዲህ ስለ ሌሎች ሴቶች አስቤ አላውቅም። ፀሐይዋን እየተመለከተ ከአኩለ ቀን ታሪፋ እንደሚደርስ አሰላ። እዚያ ሲደርስ መጽሐፉን ወፈር ባለ ሌላ መጽሐፍ ይለውጣል፤ የወይን ጠርሙሱን ይሞላል፤ ጺሙን ይላጫል፤ ፀጉሩን ይስተካከላል፤ ከኮረዳዋ ጋር ለመገናኘት መዘገጃጀት አለበታ፤ ደግሞ ሌላ ብዙ በጎች ያሉት እረኛ ቀድሞት ደርሶ ኮረዳዋን የሚወስድበት እድል መኖሩን ማሰብም አይሻም።

ህይወትን አስደሳች የሚያደርጋት ህልማችን እውን የሚሆንበት እድል መኖሩ ነው ብሎ አሰበ፣ በድጋሚ የፀሐይዋን አቅጣጫ እየተመለከተና የእርምጃ ፍጥነቱን እየጨመረ። ድንገት ታሪፋ ውስጥ ህልም የሚፈቱ አሮጊት ሴትዮ መኖራቸው ታወሰው።

* * *

አሮጊቷ ብላቴናውን ወደ ጓዳቸው ይዘውት ገቡ፤ ጓዳው ከዋናው ክፍል የተለየው የተለያዩ ቀለማት ባሏቸው ጨሌዎች ባጌጠ መጋረጃ ነው። ክፍሉ ውስጥ ያሉት አንድ ጠረጴዛ፣ አንድ የተቀደሰው የኢየሱስ ልብ ምስል እና ሁለት ወንበሮች ናቸው።

ሴትዮዋ ተቀመጡና እሱንም እንዲቀመጥ ጋበዙት። ከዚያም ሁለት እጆቹን በእጆቻቸው ይዘው በለሆሳስ መጸለይ ጀመሩ።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

የጂፕሲ ጸሎት ይመስላል። ብላቴናው ከጂፕሲዎች ጋር መንገድ ላይ ብዙ ጊዜ ተገናኝቷል፤ በጎች እየነዱ አይደለም እንጂ እነሱም ተጓዦች ናቸው። ሰዎች ጂፕሲዎች እድሜያቸውን የሚጨርሱት ሌሎችን በማታለል ነው ይሏቸዋል። ከዲያብሎስ ጋር ግንኙነት ስላላቸው ህፃናትን ጠልፈው ወደ ምስጢራዊ መንደራቸው ይወስዱና ባሮች ያደርጓቸዋልም ይባላል። ብላቴናው ህፃን እያለ ጂፕሲዎች እንዳይወስዱት በጣም ይፈራ ነበር፤ ይሄ የህፃንነት ፍርሃት አሮጊቷ እጁን ሲይዙት ተመልሶ መጣበት።

ሆኖም እርሳቸው የኢየሱስን የተቀደሰ ልብ ምስል ቤታቸው አስቀምጠዋል ብሎ አሰበ፤ ራሱን ለማጽናናት እየሞከረ። እጁ መንቀጥቀጥ ጀምሮ ፍርሃቱን ለአሮጊቷ ማሳየት አልፈለገም። በጸጥታ አባታችን ሆይን ጸለየ።

"በጣም ግሩም ነው" አሉ አሮጊቷ ዓይኖቻቸውን ከልጁ እጆች ላይ ሳይነቅሉ፤ ከዚያ ዝምታ ዋጣቸው።

ብላቴናው መጨነቅ ጀመረ። እጆቹም ይንቀጠቀጡ ጀመር - ለሴትዮዋ እስኪታወቃቸው ድረስ። በፍጥነት እጆቹን ከእጆቻቸው ላይ መንጭቆ አስለቀቀ።

"እዚህ የመጣሁት መዳፌን እንዲያነቡልኝ አይደለም" አላቸው በመምጣቱ እየተጸጸተ። የሚጠይቁትን ከፍሎ የሚሉትን ሳይሰማ ሊወጣና ተደጋግሞ በታየው ህልም ላይ ትኩረቱን ሲያደርግ አሰበ።

"የመጣኸው ህልምህን ልታስፈታ ነው" አሉ አሮጊቷ። "ህልሞች ደግሞ የእግዚአብሔር ቋንቋዎች ናቸው። እርሱ በእኛ ቋንቋ ሲናገር እኔ የተናገረውን መተርጎም እችላለሁ። በነፍስ ቋንቋ ከተናገረ ግን አንተ ብቻ ነህ



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ንግግሩን መረዳት የምትችለው። ሆኖም በየትኛውም ይናገር አንተን ላማከርኩበት ክፍያ ያስፈልገኛል።"

ሌላ ማታለያ! ብሎ አሰበ ብላቴናው። እድሉን ለመጠቀም ወሰነ። እረኛ ተኩላም ሆነ ድርቅ ሲያጋጥመው ያለውን እድል ይጠቀማል፤ ይሄው ነው የእረኛን ህይወት አስደሳች የሚያደርገው።

"አንድ አይነት ህልም ሁለት ጊዜ አየሁ" ብሎ ጀመረ። "መስክ ላይ ከበጎቼ ጋር ያለሁ ይመስለኛል፤ አንዲት ህፃን ልጅ መጥታ ከበጎቼ ጋር መጫወት ጀመረች። ሰዎች እንደዚያ ሲያደርጉ ደስ አይለኝም፤ ምክንያቱም በጎች በአዳዲስ ሰዎች ይደነብራሉ። ህፃናት ግን ምን ጊዜም ሳያስደነብሯቸው አብረዋቸው ይጫወታሉ። ለምን እንደሆነ አይገባኝም። እንስሶች የሰዎችን እድሜ እንዴት እንደሚያውቁ አይገባኝም።"

"ስለ ህልምህ በደንብ ንገረኝ" አሉ ሴትየዋ። "ወደ ወጥ ቤት መመለስ አለብኝ፤ አንተም በቂ ገንዘብ ስለሌለህ ብዙ ጊዜ ካንተ ጋር ማጥፋት አልፈልግም።"

ብላቴናው ትንሽ በስጨት ቢልም ህልሙን መናገር ቀጠለ። "ህፃኗ ለጥቂት ጊዜ ከበጎቼ ጋር ስትጫወት ቆየችና ድንገት በሁለቱም እጆቿ ይዛኝ ወደ ግብጽ ፒራሚዶች ወሰደችኝ።"

የግብጽ ፒራሚዶች ምን እንደሆኑ ሴትዮዋ ማወቅ አለማወቃቸውን ለማየት ንግግሩን ገታ አደረገ።

"ከዚያ የግብጽ ፒራሚዶች ባሉበት ሥፍራ" አለ ቃላቱን ጠበቅ እያደረገ። "ህጻኗ እዚህ ከመጣህ የተደበቀ ሃብት ታገኛለህ አለችኝ። ልክ ሃብቱ ያለበትን ትክክለኛ ቦታ ልታሳየኝ ስትል ከእንቅልፌ ነቃሁ። ሁለቱም።"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ሴትየዋ ለጥቂት ጊዜ ዝም አሉ። ከዚያ እጆቹን መልሰው ወሰዷቸውና በጥንቃቄ አጠኗቸው።

"አሁን ምንም አላስከፍልህም" አሉት። "ሃብቱን ካገኘኸው ግን ከአስር አንዱን እጅ እንድትሰጠኝ እፈልጋለሁ።"

ብላቴናው በደስታ ሳቀ። ስለተደበቀ ሃብት ባየው ህልም ምክንያት የነበረችውን ጥቂት ገንዘብ ሊያድን ነው።

"በሉዋ ህልሜን ይፍቱልኝ።"

"መጀመሪያ ማልልኝ። አሁን በምነግርህ ነገር ሰውጥ ከሃብትህ ከአስሩ አንዱን እጅ እንደምትሰጠኝ ማልልኝ።"

እረኛው ማለላቸው። የኢየሱስን ቅዱስ ልብ ምስል እያዩ አሮጊቷ በድጋሚ እንዲምልላቸው ጠየቁት።

"በሁለንታ ቋንቋ የተነገረ ህልም ነው" አሉ። "እተረጉመው ዘንድ ይቻለኛል፤ ፍቺው ግን ከባድ ነው። ለዚህም ነው ከምታገኘው ሃብት ልታካፍለኝ እንደሚገባ የተሰማኝ።

"የእኔን ፍቺ እነሆ፦ ወደ ግብጽ ፒራሚዶች መሔድ አለብህ። ስለ እነሱ ሰምቼ አላውቅም፤ የነገረችህ ህፃን ልጅ ከሆነች ግን በርግጥም አሉ ማለት ነው። እዚያም ባለፀጋ የሚያደርግህ ሃብት ታገኛለህ።"

ብላቴናው ተገረመ፤ ወዲያው ደግሞ ተናደደ። ለዚህ ለዚህማ አሮጊቷ አያስፈልጉትም ነበር። ምንም መክፈል እንደማይጠበቅበት ሲያስታውስ ግን ተጽናና።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ለዚህ ብዬ ጊዜዬን ማባከን አልነበረብኝም" አለ።

"ህልምህ አስቸጋሪ ህልም እንደሆነ ነግሬህ ነበር። በህይወት ውስጥ በጣም ልዩ የሚሆኑት ነገሮች ቀላሉች ናቸው፤ ጠቢባን ብቻ ናቸው ሊረዷቸው የሚችሉት። እኔ ደግሞ ጠቢብ ባለመሆኔ መዳፍን እንደማንበብ ያሉ ሌሎች ጥበቦችን ማወቅ ነበረብኝ።"

"እሺ ታዲያ ወደ ግብጽ የምሄደው እንዴት ነው?"

"እኔ የማደርገው ህልም መፍታት ብቻ ነው። እነሱን እንዴት እውን ማድረግ እንደሚቻል አላውቅም። ለዚህ እኮ ነው የልጆቼ ተጧሪ የሆንኩት።"

"ግብጽ ባልሄድስ?"

"ክፍያዬን አላገኝማ። ይሄ ደግሞ የመጀመሪያ ጊዜዬ አይደለም።"

አሮጊቷ ከእሱ ጋር ከበቂ በላይ ማሳለፋቸውን ነግረውት እንዲሄድላቸው ጠየቁት።

ብላቴናው በዚህ ተናደደ፤ ሁለተኛ በህልም ላለማመንም ወሰነ። ገና ብዙ ማከናወን ያለበት ጉዳይ እንዳለ አስታወሰ። የሚበላ ነገር ፍለጋ ገበያ ሄደ፤ ያነበበውን መጽሐፍ በሌላ ወፍራም መጽሐፍ ለወጠ፤ የገዛውን አዲስ ወይን ጠጅም ቀመሰ። ቀኑ ሞቃታም ነበር፤ ወይኑ ደግሞ ሁለመናን ያድሳል። በጎቹ የከተማው መግቢያ ላይ ባለ የአንድ ወዳጁ ጋጣ ውስጥ ናቸው። ብላቴናው እዚህ ከተማ ከብዙ ሰዎች ጋር ይተዋወቃል። ተጓዥነቱን የሚወደው በዚህም ምክንያት ነው - በየጊዜው አዳዲስ ጓደኞች ያፈራል፤



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ሆኖም ጊዜውን ሁሉ ከእነሱ ጋር ማሳለፍ አይጠበቅበትም። መንፈሳዊው ትምህርት ቤት ውስጥ እንዳጋጠመው፣ አንድ ሰው በየቀኑ ከተመሳሳይ ሰዎች ጋር የሚገናኝ ከሆነ፤ በመጨረሻ እነዚህ ሰዎች የህይወቱ አካላት ይሆናሉ። እናም ሰውየው እንዲለወጥ ይፈልጋሉ። እነሱ እንደሚፈልጉት ካልሆነላቸው ይናደዱበታል። ሁሉም ሰው ስለሌሎች ሰዎች አኗኗር በደንብ የሚያውቅ የራሱን ግን የማያውቅ ይመስላል።

በጎቹን ወደ መስክ ከማሰማራቱ በፊት ፀሐይ መጥለቅ እስክትጀምር ለመጠበቅ ወሰነ። ከሶስት ቀናት በኋላ ከነጋዴው ልጅ ጋር ይገናኛል።

የገዛውን መጽሐፍ ማንበብ ጀመረ። በመጀመሪያው ገጹ ስለ አንድ የቀብር ስነ ስርዓት ይተርካል። ለመጥራት የሚያስቸግሩ ስሞች ያሏቸው ሰዎች ይጠቀሳሉ። እሱ መጽሐፍ ቢጽፍ በአንድ ጊዜ የአንድን ሰው ታሪክ ብቻ እንደሚተርክና አንባቢው ብዙ ስሞችን ለማስታወስ እንዳይጨነቅ ለማገዝ እንደሚሞክር አሰበ።

በመጽሐፉ መመሰጥ ሲጀምር እየወደደው መጣ፤ ቀብሩ በአንድ በረዷማ ቀን የተከናወነ በመሆኑ ብላቴናው የትረካው ቅዝቃዜ እንዲሰማው ፈቀደ። እያነበበ እያለ አንድ ሽማግሌ ከጎኑ ተቀመጡና ሊያዋሩት ሞከሩ።

አደባባዩ ላይ ወደተሰበሰቡት ሰዎች እየጠቆሙት፣ "ምን እያደረጉ ነው?" አሉት።

"እየሰሩ" ድርቅ ያለ መልስ ሰጣቸው፣ መጽሐፉ ላይ ማተኮር እንደሚፈልግ በሚያሳይ ድምጸት።

በእውነት እሱ በዚህ ሰዓት በነጋዴው ልጅ ፊት የበጎቹን ፀጉር እየሸለተ ስለ እሱ ያላትን ግምት ከፍ ስለማስደረግ እያሰበ ነበር። ሰውየው ግን መልሰው



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ከሃሳቡ አናጠቡት። እንደደከማቸውና እንደተጠሙ ጠየቁት። ጠጥተው ይሄዱልኛል ብሎ ተስፋ በማድረግ የወይን ጠርሙሱን ሰጣቸው።

ሽማግሌው ማውራት አሰኝቷቸዋል፤ ምን መጽሐፍ እያነበበ እንደሆነ ጠየቁት። ብላቴናው ጥሏቸው ወደ ሌላ መቀመጫ ሊሄድ ተመኝቶ ነበር፤ ግና አባቱ አረጋዊያንን ማክበር እንዳለበት ያስተማረው ትምህርት ከመነሳት አገደው። ስለዚህም በሁለት ምክንያቶች መጽሐፉን ለሰውየው ሰጣቸው፤ አንድም ርእሱን በትክክል መጥራት ባለመቻሉ፣ አንድም አረጋዊው ማንበብ የማይችሉ ከሆነ እፍረት ተሰምቷቸው መቀመጫ ይቀይራሉ ብሎ በማሰብ።

አረጋዊው መጽሐፉን እያገላበጡ እንደ አንድ እንግዳ ነገር በመደነቅ ተመለከቱት። "ጠቃሚ መጽሐፍ ነው፤ ነገር ግን ያበሳጫል።"

ብላቴናው ደነገጠ። አረጋዊው ማንበብ ከመቻላቸውም በላይ ይሄንን መጽሐፍ አንብበውታል። መጽሐፉ አናዳጅ ከሆነ ደግሞ አሁንም ሊቀይረው ይችላል።

"በዓለም ላይ ያሉ መጻሕፍት ሁሉ የሚናገሩትን ተመሳሳይ ነገር የሚናገር መጽሐፍ ነው" ቀጠሉ አረጋዊው። "ሰዎች እጣ ፈንታቸውን መምረጥ ስላለመቻላቸው ይገልጻል። ከዚያም ሁሉም ሰዎች የዓለምን ትልቁን ውሸት ያምናሉ ብሎ ይደመድማል።"

"የዓለም ትልቁ ውሸት ምንድነው?" ብላቴናው ሙሉ በሙሉ ተገርሞ ጠየቀ።

"ይሄውልህ፡- በሕይወታችን የሆነ ነጥብ ላይ ስንደርስ የሚያጋጥሙንን ነገሮች መቆጣጠር ይሳነናል፤ ህይወታችንም በእጣፈንታችን ቁጥጥር ሥር ትወድቃለች። ይሄ ነው የዓለም ትልቁ ውሸት።"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"እንዲህ ያለ ነገር አጋጥሞኝ አያውቅም" አለ ብላቴናው። "ቄስ እንድሆን ፈለጉ፤ እኔ ግን እረኛ መሆን ወሰንኩ።"

"በጣም የሚሻል ነገር መርጠሃል" አረጋዊው ተናገሩ። "ምክንያቱም መጓዝ በጣም ትወዳለህ።"

ምን እንደማስብ ያውቃሉ ብሎ አሰበ ብላቴናው። አረጋዊው መጽሐፉን ሲገላልጡ ሊመልሱለት የፈለጉ አይመስሉም። የአረጋዊው አለባበስ ያልተለመደ መሆኑን አስተዋለ። አረብ ይመስላሉ፤ አረብ እዚህ ሥፍራ ማየት አያስደንቅም። አፍሪካ ከታሪፋ የጥቂት ሰዓታት ርቀት ነው ያላት፤ አፍሪካ ለመድረስ አንድ ሰው ጠባቦቹን መንገዶች በጀልባ ማቋረጥ ብቻ ነው የሚኖርበት። ብዙ ጊዜ አረቦቹ ከተማ ይመጣሉ፤ ይገበያያሉ፤ በቀን ለብዙ ጊዜ ያልተለመዱ ዓይነት ጸሎቶቻቸውን ያደርሳሉ።

"ከወዴት ነው የመጡት?" ጠየቀ ብላቴናው።

"ከብዙ ሥፍራዎች።"

"ማንም ሰው ከብዙ ሥፍራዎች ሊመጣ አይችልም" አለ ብላቴናው። "እኔ እረኛ ነኝ፤ ብዙ ቦታዎችን ረግጫለሁ፤ የመጣሁት ግን ከአንድ ቦታ ነው - የጥንት ሕንፃዎች ካሉባት ከተማ። የተወለድኩትም እዚያ ነው።"

"ታዲያ እንግዲህ፣ የተወለድኩት ሳሌም ነው ማለት እንችላለን።"

ብላቴናው ሳሌም የት እንደምትገኝ አያውቅም፤ ነገር ግን አላዋቂ መስሎ ላለመታየት ብሎ መጠየቅ አልፈለገም። አደባባዩ ላይ የተሰበሰቡትን ሰዎች አያቸው። ይመጣሉ፣ ይሄዳሉ፤ ሁሉም ደግሞ ሥራ የበዛባቸው ይመስላሉ።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ሳሌም እንዴት ናት?" ብሎ ጠየቀ ፍንጭ ብጤ ለማግኘት።

"ያው እንደነበረች ናት።"

ምንም ፍንጭ አላገኘም። ሳሌም አንዳሉዚያ ውስጥ እንዳልሆነች ግን ያውቃል። ብትሆን ኖሮ እስካሁን ስለ እሷ ይሰማ ነበር።

"ሳሌም ውስጥ ምን ይሰራሉ?" አልለቀቃቸውም።

"ሳሌም ውስጥ ምን እሠራለሁ?" አረጋዊው ሳቁ። "የሳሌም ንጉሥ ነኝ!"

ሰዎች ያልተለመዱ ነገሮችን መናገር ይወዳሉ ብሎ አሰበ - ብላቴናው። አንዳንዴ ከማይናገሩት በጎች ጋር መሆን ይሻላል። አረ እንዲያውም ከመጻሕፍት ጋር ብቻ መሆን ይሻላል። ልትሰሚቸው በፈለጋችሁ ጊዜ አስደናቂ ታሪካቸውን ይነግሯችኋል። ከሰዎች ጋር ስታወሩ ግን ወሬውን መቀጠል እስኪያቅታችሁ ድረስ ግራ የሚያጋቡ እንግዳ ነገሮችን ይነግሯችኋል።

"መልከጼዲቅ እባላለሁ" አሉ አረጋዊው። "ስንት በጎች አሉህ?"

"በቂ" አለ ብላቴናው። አረጋዊው ስለ እሱ ህይወት ይበልጥ ማወቅ እንደፈለጉ ታይቶታል።

"እንዲህ ከሆነ መቸገራችን ነው። በቂ በጎች እንዳሉህ ከተሰማህ ልረዳህ አልችልም።"

ብላቴናው በንዴት መቃጠል ጀመረ። እርዳታ እየጠየቀ አልነበረም። ራሳቸው አረጋዊው ናቸው ወይኑን የጠየቁትና ጨዋታ የጀመሩት።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"መጽሐፌን ይስጡኝ" አላቸው፡፡ "በጎቼን መሰብሰብና መንገድ መጀመር አለብኝ፡፡"

"ከበጎችህ ከአስር አንድ እጁን ስጠኝና የተደበቀውን ሀብት እንዴት እንደምታገኘው እነግርሃለሁ፡፡"

ብላቴናው ህልሙን አስታወሰና በድንገት ሁሉም ነገር ግልጽልጽ ብሎ ታየው፡፡ አሮጊቷ ምንም አላስከፈሉትም፤ እኚህ ሰውዬ ደግሞ ባላቸው ሊሆኑ ይችላሉ፤ አረጋዊው ፈጽሞ ስለሌለ ነገር መረጃ በመስጠት የበለጠ ገንዘብ ለማግኘት እየሞከሩ ነው፡፡ ጂፕሲም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ብላቴናው ምንም ነገር ከመናገሩ በፊት አረጋዊው እንጨት አንስተው አሸዋው ላይ መጻፍ ጀመሩ፡፡ ከደረታቸው ላይ የብላቴናውን ዓይን እስኪያጥበረብረው ድረስ ከፍተኛ ብርሃን ተረጨ፡፡ አረጋዊው በፍጥነት ደረታቸውን በኮፍያቸው ሸፈኑት፡፡ ብላቴናው እይታው ሲስተካከልለት አረጋዊው አሸዋው ላይ የጻፉትን ማንበብ ቻለ፡፡

በአሸዋውም ላይ የአባቱንና የእናቱን ስም እንዲሁም የተማረበትን መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ስም አነበበ፡፡ እስከዛሬ የማያውቀውን የነጋዴውን ልጅ የኮረዳዋን ስም አነበበ፤ ፈጽሞ ለሰው ነግሯቸው የማያውቁ ምስጢሮቹን ሳይቀር አሸዋው ላይ አነበበ፡፡

* * *

—"የሳሌም ንጉሥ ነኝ" ብለውት ነበር አረጋዊው፡፡



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"አንድ ንጉሥ ከአንድ እረኛ ጋር ለምን መነጋገር ፈለገ?" ብሎ ጠየቃቸው ብላቴናው ግራ እንደተጋባ።

"በብዙ ምክንያቶች። ዋናው ግን እጣ ፈንታህን ማወቅ ስለተሳካልህ ነው እንበል።"

ብላቴናው የአንድ ሰው "እጣፈንታ" ምን እንደሆነ አያውቅም።

"ሁልጊዜም ልታሳካው የምትፈልገው ነገር ነው። ሁሉም ሰዎች ወጣቶች እያሉ እጣፈንታቸው ምን እንደሆነ ያውቃሉ።

"በወጣትነት ዘመናቸው ሁሉም ነገር ግልጽ፣ ሁሉም ነገር የሚቻል ይሆንላቸዋል። ማለም አይፈሩም፤ በህይወታቸው ተፈጽሞ ሊያዩት ስለሚፈልጉት ነገር ከመቃተትም አይቆጠቡም። ጊዜው እየገፋ ሲሄድ ግን የሆነ ምስጢራዊ ኃይል እጣፈንታቸውን እውን ማድረግ እንደማይችሉ ያሳምናቸዋል።"

አረጋዊው ከተናገሩት ነገር ብዙም የማረከው የለም። ሆኖም "ምስጢራዊው ኃይል" ምን እንደሆነ ማወቅ ፈልጓል፤ የነጋዴው ልጅ ስለዚህ ነገር ሲነግራት ትማረከለታለች!

"አሉታዊ የሚመስል ኃይል ቢሆንም እጣፈንታህን እንዴት እውን እንደምታደርግ ያሳይሃል። መንፈስህንና ፈቃደ ልብህን ያዘጋጅልሀል፤ ምክንያቱም በዚህ ምድር ላይ አንድ ታላቅ እውነት አለ፡- ማንም ሁን ማንም ወይም ምንም ሥራ ምንም፣ የሆነ ነገር ከልብህ የምትፈልግ ከሆነ ፍላጎትህ የመጣው ከሁለንታ ነፍስ ነው። ያ መሻትህ በምድር ላይ ትፈጽመው ዘንድ የተሰጠህ ተልእኮ ነው።"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"የምፈልገው መንገዛ ወይም የአንድ የጨርቃጨርቅ ነጋዴን ልጅ ማግባት ቢሆንም እንኳ?"

"አዎን፣ ሃብትን መፈለግ ቢሆንም እንኳ። የሁለንታ ነፍስ ቀለብ የሰዎች ደስታ ነው። ደስታ ማጣቸው፣ ቅናታቸውና ምቀኝነታቸውም ጭምር። እጣፈንታን እውን ማድረግ የአንድ ሰው ብቸኛው ግዴታው ነው። ሁሉም ነገሮች አንድ ናቸው።

"አንተ የሆነ ነገር ስትፈልግ ዓለም ሁሉም ታሳካው ዘንድ ሊተባበርህ ይነሳል"

መሐሳቸው ለአፍታ ጸጥታ ሰፈነ። አረጋዊው ቀድመው ተናገሩ።

"የበጎችን መንጋ መከተል ለምን ወደድክ?"

"መጓዝ ስለምወድ።"

አረጋዊው በመደብሩ መስኮት ላይ የቆመውን ዳቦ ጋጋሪ ጠቆሙት። "ሕፃን እያለ ያም ሰው መጓዝ ይፈልግ ነበር። ነገር ግን መጀመሪያ ዳቦ መጋገሪያውን ሊገዛና ገንዘብ ሊያጠራቅም ወሰነ። ከሸመገለ በኋላ ወደ አፍሪካ ሄዶ አንድ ወር ሊሰነብት ነው። ሰዎች በፈለጉ ጊዜ የሚያልሙትን ነገር ማድረግ እንደሚችሉ አልተገነዘበም።"

"እረኛ ለመሆን መወሰን ነበረበት" አለ ብላቴናው።

"አሱንም አስቦት ነበር" አሉ አረጋዊው። "ሆኖም ዳቦ ጋጋሪዎች ከእረኞች ይልቅ ጠቃሚ ሰዎች ናቸው። ዳቦ ጋጋሪዎች ቤት አላቸው፤ እረኞች ግን



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

በየሚዳው ነው የሚያድሩት። ወላጆችም ሴቶች ልጆቻቸውን ከአረኛ ይልቅ ለዳቦ ጋጋሪ መዳርን ይመርጣሉ።"

ስለ ነጋዴው ሴት ልጅ ሲያስብ፣ ብላቴናው የሆነ ድንገተኛ ህመም ልቡ ላይ ተሰማው። መቼም እነሱ ከተማ ውስጥ ዳቦ ጋጋሪ መኖሩ አይቀርም።

አረጋዊው ቀጠሉ፣ "ወደፊት ሰዎች ስለ እረኞችና ዳቦ ጋጋሪዎች የሚያስቡት ነገር ከራሳቸው እጣፈንታዎች በልጠባቸው ይገኛል።"

አረጋዊው መጽሐፉን ገለጥ ገለጥ አድርገው አንዱን ገጽ ማንበብ ጀመሩ። ብላቴናው ሲጠብቃቸው ቆየና ልክ እሳቸው እንዳቋረጡት ሽማግሌውን አቋረጣቸው።

"ግን ለምንድነው ይሄን ሁሉ የሚነግሩኝ?"

"ምክንያቱም አንተ እጣፈንታህን እውን ለማድረግ እየሞከርክ ነው። አሁን ደግሞ ሁሉንም ነገር ወደ መተው ደረጃ እየደረስክ ነው።"

"እና ሁሌም በዚህ ጊዜ ነው ሰዎች ዘንድ የሚመጡት?"

"ሁሌም በዚህ መልኩ አገለጣለሁ። አንዳንዴ በመፍትሄ፣ በተለይ በወሳኝ ጊዜያት ነገሮች በቀላሉ እንዲከሰቱ አመቻቻለሁ። የምሰራቸው ሌሎች ሥራዎችም አሉ፤ ሰዎች ግን እኔ የሰራኋቸው መሆኑን አይገነዘቡም።"

አረጋዊው የማእድን አውጪውን ምሳሌ ነገሩት። ከሳምንት በፊት የሆነ ታሪክ ነው። ማእድን አውጪው ሁሉ - ነገሩን ትቶ ኤመራልድ የተባሉትን የከበሩ ድንጋዮች ቆፍሮ ለማውጣት ተነሳ። ለአምስት አመታት አንድ ወንዝ



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ውስጥ ኤመራልዶችን ፍለጋ በሺዎች የሚቆጠሩ ድንጋዮችን ሲመረምር ከረመ። አንድ ድንጋይ መመርመር ብቻ ሲቀረው ማእድን ቆፋሪው በጣም ተስፋ ቆርጦ ሙከራውን ሊተወው የሚወስንበት ደረጃ ላይ ደረሰ። ሰውየው ሁሉ - ነገሩን ለእጣፈንታው መስዋእት አድርጓልና አረጋዊው ጣልቃ ሊገቡ ወሰኑ። ራሳቸውንም ወደ ድንጋይነት ቀየሩና ቆፋሪው እግር ሥር ተንከባለው ወደቁ። ቆፋሪው አምስት አመት ያለፍሬ መልፋቱ አበሳጭቶት ነበርና ይህን እግሩ ሥር የወደቀ ድንጋይ በኃይል ሲወረውረው ይሄድና ያረፈበትን ድንጋይ ይሰብረዋል። በተሰበረው ድንጋይ ውስጥ በዓለም በውበቱ ወደር የማይገኝለት ኤመራልድ ተገኘ።

"ሰዎች ስለ መኖሪያ ዓላማቸው ምንነት ቶሎ ያውቃሉ" አሉ አረጋዊው በምሬት። "ለዚህ ይሆናል ቶሎ ተስፋ የሚቆርጡበት። ሆኖም እጣፈንታ ሁሌም እንዲሁ ነው።"

ብላቴናው ስለ ተደበቀው ሃብት አረጋዊው መናገራቸውን አስታወሳቸው።

"ስለራስህ ድብቅ ሃብት ማወቅ ከፈለግህ ከበጎችህ አንድ አሥረኛውን ልትሰጠኝ ይገባል።"

"የድብቅ ሃብቴ አንድ አስረኛስ?"

ሽማግሌው የተከፉ መሰሉ። "እጅህ ላይ ባላስገባኸው ነገር ቃል መግባት ከጀመርክ እሱን ፈልጎ የማግኘት መሻትህን ታጣዋለህ።"

ብላቴናው ከሃብቱ ከአሥር አንድ እጁን ለአንዲት ጂፕሲ ሊሰጣቸው ቃል መግባቱን ለአረጋዊው ነገራቸው።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ጂፕሲዎች ሰዎች ይህን እንዲያደርጉላቸው ማሳመን ይችሉበታል" አረጋዊው በረጅሙ ተነፈሱ። "ለማንኛውም፣ በህይወት ውስጥ እያንዳንዱ ነገር ዋጋ እንደሚያስከፍል ማወቅህም ጥሩ ነው። የብርሃን ሠራዊቶች ሊያስተምሩ የሚሞክሩት ይህንኑ ነው።"

አረጋዊው መጽሐፉን መለሱለት።

"ነገ በዚሁ ጊዜ የመንጋህን አንድ አሥረኛ አምጣልኝ። ከዚያ ድብቅ ሃብትህን እንዴት እንደምታገኝ እነግርሃለሁ። ደህናዋል።"

በአደባባዩ አንድ ጥግ በኩል ተሰወሩ።

ብላቴናው መጽሐፉን መልሶ ለማንበብ ሞከረ፤ ማተኮር ግን አቃተው። አረጋዊው ልክ መሆናቸውን በማወቁ ተጨንቋል፤ ተናዷልም። ወደ ዳቦ ቤቱ ሄዶ ቁራሽ ዳቦ ገዛ - አረጋዊው የነገሩትን ለጋጋሪው ልንገር አልንገር ብሎ እያመነታ። አንዳንድ ጊዜ ነገሮችን ባሉበት መተው ይሻላል ብሎ አሰበና ምንም ሳለመናገር ወሰነ። የሆነ ነገር ቢነግረው ኖሮ ጋጋሪው ሁሉንም ነገር ለመተው በማሰብ ተከታዮቹን ሶስት ቀናት ያጠፋቸው ነበር - ነገሮች የተቃኑለት ቢሆንም እንኳን። ብላቴናው ጋጋሪው ላይ እንዲህ ዓይነት ጭንቀት መፍጠር አልፈለገም። ስለዚህም ከተማው ውስጥ መዞር ጀመረና የከተማው መግቢያ መውጫ በሮች ጋር ደረሰ። በመስኮቷ በኩል ሰዎች ወደ አፍሪካ መሔጃ ትኬት የሚገዙባት ትንሽዬ ሕንፃ አለች። እሱ ደግሞ ግብጽ አፍሪካ ውስጥ መሆኗን ያውቃል።

"ምን ልታዘዝ?" በውስጥ በኩል ያለ አንድ ሰው በመስኮት ጠየቀው።

"ነገ ተመልሼ እመጣ ይሆናል" አለው ብላቴናው ከመስኮቱ እየራቀ። አንዷን በጉን ቢሸጥ እንኳን ለትኬት መግዣ ይበቃዋል። ሃሳቡ ፍርሃት ለቀቀበት።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ሌላ ህልመኛ" አለ ትኬት ሻጩ ለረዳቱ፣ እየራቃቸው የነበረውን ይህን እረኛ እየተመለከተ። "ለጉዞ የሚሆነው በቂ ገንዘብ የለውም።"

ብላቴናው ትኬት መሸጫው ጋር ቆሞ በጎቹን አስታውሶ ነበርና ወደ በግ እረኝነቱ መመለስ እንዳለበት ወስኗል። በሁለት ዓመት ውስጥ ስለ እረኝነት ሁሉን ነገር ተምሯል፦ የበጎችን አሸላለት፣ ለእርጉዞች እንክብካቤ መስጠትና በጎቹን ከተኩላዎች እንዴት መጠበቅ እንዳለበት አውቋል። በመላው አንዳሉዚያ በጎቹን የት እንደሚያሰማራቸውም ያውቃል፤ እያንዳንዱ በግ ምን ያህል እንደሚያወጣም ያውቃል።

በጣም ረጅሙን መንገድ መርጦ ወደ ጓደኛው ጋጣ ለመሄድ ወሰነ። የከተማውን ግንብ እያለፈ እያለ ጉዞውን አቋረጠና ወደ ግንቡ ጫፍ ወጣ። እዚህ ሆኖ አፍሪካን በርቀት ማየት ይቻላል። ሙሮች መላዋን ስፔንን ለመውረር የመጡት ከዚህ ሥፍራ መሆኑን የሆነ ሰው ነግሮታል።

እዚህ ከፍታ ላይ ሆኖ ከአረጋዊው ጋር የተቀመጠበትን ድድ ማስጫ ጨምሮ ከተማዋን ሙሉ በሙሉ ማየት ይችላል። አረጋዊውን ያገኘሁባት ሰዓት የተረገመች ትሁን ብሎ አሰበ። እዚህ ከተማ የመጣው ህልም ፈቺዋን አሮጊት ለማግኘት ብቻ ነበር። አሮጊቷም ሆኑ ሽማግሌው በእሱ እረኝነት አልተማረኩም። እነሱ በነገሮች ማመን ካቆሙ የቆዩ ነጠላ ግለሰቦች ናቸው፤ እረኞች ከበጎቻቸው ጋር ቁርኝት እንደሚፈጥሩ አልገባቸውም። እሱ ስለ እያንዳንዱ በግ ሁሉንም ነገር ያውቃል፦ የትኞቹ ሽባዎች እንደሆኑ፣ የትኛዋ ከሁለት ወር በፊት እንደወለደች፣ የትኛው ይበልጥ ሰነፍ እንደሆነ ሁሉ ያውቃል። እንዴት እንደሚሸልታቸው እና እንዴት እንደሚያርዳቸውም ያውቃል። ቢተዋቸው ይጎዳሉ።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ነፋሱ መንፈስ ጀመረ። ነፋሱ ሙሮችን በምሥራቅ ሜዲትራኒያን ከሚገኘው ሌቫንት ይዟቸው እንደመጣ ስለሚታመን ሰዎች ሌቫንተር ብለው የሚጠሩት ነፋስ መሆኑን አውቆታል።

የሌቫንተር ኃይል በረታ። ብላቴናው አሁን በበጎቼና በድብቅ ሃብቴ መሃል ሆኛለሁ ሲል አሰበ። ካለውና እንዲኖረው ከሚፈልገው አንዱን መምረጥ አለበት። ደግሞም የነጋዴው ልጅ አለች፤ እሷ የእሱ ጥገኛ አይደለችምና የበጎቹን ያህል አታሳስበውም። ምናልባትም እኮ አታስታውሰው ይሆናል። ከእሱ ጋር የተገናኙበት ቀን ለእሷ እያንዳንዱ ቀን ተመሳሳይ ነው፤ እያንዳንዱ ቀን ከቀጣዩ ቀን ጋር ተመሳሳይ የሚሆነው ደግሞ ሰዎች በህይወታቸው በየቀኑ ፀሐይ በወጣች ቁጥር የሚያጋጥሟቸውን ደግ ነገሮች ማወቅ ሲሳናቸው ነው።

አባቴን፣ እናቴንና የከተማዬን ግንብ ከኋላዬ ትቻቸዋለሁ። የእኔን መራቅ ለምደውታል፤ እኔም እንደዚያው። በጎቹም አብሬያቸው አለመሆኔን ይለምዱታል ሲል አሰበ - ብላቴናው።

እተቀመጠበት ሆኖ እዚያ የሕዝብ መሰብሰቢያ አደባባይ ላይ ሰዎች ዳቦ ቤት ሲገቡና ሲወጡ ይታየዋል። እሱና አረጋዊው ተቀምጠውበት የነበረው አግዳሚ ወንበር ላይ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ተቀምጠው አየ፤ ወጣቶቹ ሲሳሳሙም ተመለከተ።

"ያ ጋጋሪ..." አለ ለራሱ፤ ሃሳቡን ሳይጨርስ ተወው። የሌቫንተር ጉልበት እየጠነከረ ነው፤ ግፊቱ ፊቱ ላይ ተሰማው። ያ ነፋስ እምነ ሙሮችን አምጥቷቸዋል፤ ሆኖም የበረሃውንና በዓይነርግብ የተሸፈኑ ሴቶችን መዓዛም ይዞ ይመጣል። የማይታወቀውን ወይም ወርቅን ፍለጋ ወይም ለጀብድ



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

የተጓዙ ወይም ፒራሚዶችን ፍለጋ የሔዱ ወንዶችንም ሳብና ህልሞችም ይዞ መጥቷል። ብላቴናው በነፋሱ ነፃነት ቀና፤ ደግሞም እሱ ራሱም ተመሳሳይ አይነት ነፃነት ሊኖረው እንደሚችል ታየው። የነጋዴው ልጅ፣ እንዲሁም የአንዳሉዚያ መስኮች ወደ እጣፈንታው የሚመሩት ደረጃዎች ብቻ ናቸው።

ብላቴናው በተከታዩ ቀን እኩለ - ቀን ላይ ከአረጋዊው ጋር ተገናኘ። ስድስት በጎች ይዞላቸው መጥቷል።

"ገርሞኛል" አለ ብላቴናው። "ጓደኛዬ የቀሩትን በጎች በሙሉ ወዲያው ገዛኝ። ሁሌም እረኛ ለመሆን ያልም እንደነበርና ይሄም ጥሩ ንግር እንደሆነ ነገረኝ።"

"ሁሌም እንዲሁ ነው" አሉ አረጋዊው። "ለእንገዛ የመመረጥ መርህ ይባላል። ካርታ ለመጀመሪያ ጊዜ ስትጫወት ብዙ ጊዜ ታሸንፋለህ። የጀማሪ እድል ይባላል።"

"ለምን እንዲህ ይሆናል?"

"ምክንያቱም እንዲህ እጣፈንታህን እውን ታደርግ ዘንድ የሚሻ ኃይል አለ፤ ፍላጎትህን በስኬት ጣእም ይቀሰቅስብሃል።"

አረጋዊው በጎቹን መመርመር ጀመሩ፤ እናም አንደኛው በግ ሽባ መሆኑን ተረዱ። ብላቴናው በጉ ከመንጋው መሐል ብልሁና ብዙ ሱፍ የሚያስገኘው በግ በመሆኑ ሽባነቱ እንደማያሳስብ አብራራላቸው።

"ሃብቱ የት ነው ያለው?"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ግብጽ ውስጥ ነው፤ ፒራሚዶቹ አቅራቢያ።"

ብላቴናው ተናደደ። አሮጊቷም እንዲሁ ነበር ያሉት። እሳቸው ግን ምንም አላስከፈሉትም።

"ሃብቱን ለማግኘት ንግሮችህን መከተል አለብህ። እግዚአብሔር ለሁሉም ሰው ሊከተለው የሚገባውን መንገድ አዘጋጅቶለታል። እሱ ላንተ የተወልህን ንግሮችን ማንበብ ብቻ ነው ያለብህ።"

ብላቴናው ሊናገር ሲል አንዲት ቢራቢሮ በእሱና በሽማግሌው መሐል ብር ብላ አለፈች። ቢራቢሮዎች ጥሩ ንግሮች ስለመሆናቸው አያቱ የነገሩትን አስታወሰ - ልክ እንደዋዝንቢትና ተስፋ እንደማድረግ፣ ልክ እንደ እንሽላሊትና እንደ ባለአራት ቅጠሉ ሰንበሌጥ።

"ልክ ነው፣" አሉ አረጋዊው፤ የብላቴናውን ሃሳብ አንብበውበት። "ልክ አያትህ እንዳስተማሩህ። እነዚህ ጥሩ ንግሮች ናቸው።"

አረጋዊው ኮፍያቸውን አነሱት፤ ብላቴናው ባየው ነገር ክው አለ። አረጋዊው ከወርቅ የተሰራ፣ በከበረ ድንጋዮች ያጌጠ የደረት ጥሩር ለብሰዋል። ብላቴናው ትናንት ያየውን ብርሃን አስታወሰ።

እውነትም ንጉሥ ናቸው! ሌቦች እንዳያስቸግሯቸው ይሆናል ራሳቸውን የለወጡት።

"እንካ እነኚህን" አሉ አረጋዊው በጥሩሩ መሐል ላይ ተቀምጠው የነበሩትን አንድ ነጭና አንድ ጥቁር ድንጋዮች ለእሱ እያቀበሉ። "ዑሪምና ቱሚም



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ይባላሉ። ጥቂቱ አወንታን ነጩ፣ ደግሞ አሉታን ያመለክታሉ። ንግሮችህን ማገበብ ስትችገር እነዚህ ያግዙሃል። ሁሌም አንድ ተጨባጭ ጥያቄ ጠይቅ።

"ሆኖም፣ የምትችል ከሆነ የራስህን ውሳኔ ወስን። ሀብቱ ያለው ፒራሚዶቹ ጋር ነው፤ ይህን ታውቃለህ። ስድስቱን በጎች ያስከፈልኩህ ግን መወሰን እንድትችል ስለረዳሁህ ነው።"

ብላቴናው ድንጋዮቹን ቦርሳው ውስጥ ጨመራቸው። ከዚህ በኋላ ውሳኔው የራሱ ነው።

"የምትደራደረው ስለ አንድ እና አንድ ነገር ብቻ መሆኑን አትዘንጋ። የንግሮችንም ቋንቋ አትዘንጋ። ከሁሉም በላይ ደግሞ እጣፈንታህን እስከመደምደሚያው ድረስ መከተልን አትርሳ።

"ከመሄዱ በፊት ግን አንዲት ትንሽዬ ታሪክ ብነግርህ እወዳለሁ።

"አንድ የሱቅ ጠባቂ ልጁን ስለ የደስተኝነት ምስጢር ተምሮ እንዲመጣ ወደ አንድ ጠቢብ ጠቢባን ይልከዋል።

ልጅየውም በበረሃው ለአርባ ቀናት ከተዘዋወረ በኋላ በአንድ ተራራ ላይ ከፍ ብሎ የተገነባ ግዙፍ የቤተመንግስት አጥር ግቢ ደረሰ። እዚህ ነበር ጠቢቡ ሰው የሚኖረው።

"እናም በገድል በቅድሥና ራሱን የለየ ሰው በማግኘት ፈንታ ገና የግንቡን አጥር አልፎ ወደ ዋናው ክፍል ሲገባ የንቦች ቀፎ ውስጥ ያለውን ዓይነት ሽርጉድ አጋጠመው። ነጋዴዎች ይመጣሉ፣ ይሄዳሉ፤ በየጥጋጥጉ ሰዎች ያወራሉ፤ አነሥ ያለ ኦርኬስትራ ለስላሳ ሙዚቃ ይጫወታል፤ ደግሞም



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

በዚህ አካባቢ በጣፋጭነታቸው ወደር የማይገኝላቸውን ምግቦች በያዙ ትሪዎች የተሸፈነ ጠረጴዛም አለ። ጠቢቡ ከእያንዳንዱ ሰው ጋር ስለሚነጋገር፣ ልጁ እሱን የማናገር ተራ እስኪደርሰው ለሁለት ሰዓታት ያህል መጠበቅ ነበረበት።

"ጠቢቡ ልጁ ስለመጣበት ምክንያት ያቀረበለትን ገለጻ በጥሞና አዳመጠው፤ ነገር ግን የደስተኝነትን ምስጢር ለማስረዳት ለጊዜው ጊዜ እንደሌለው ነገረው። ልጁ ቤተመንግሥቱን ጎብኝቶ በሁለት ሰዓት ውስጥ እንዲመለስም ሃሳብ አቀረበለት።

"ጠቢቡ ሁለት ጠብታ ዘይት የያዘ የሻይ ማንኪያ ለልጁ እየሰጠው 'በጉብኝትህ ወቅት ታዲያ አንድ ነገር እንድታደርግልኝ እፈልጋለሁ› አለው። ‹በሄድክበት ሁሉ ይሄንን ማንኪያ ዘይቱን ሳታፈስ ይዘህ ተመለስ።'

"ልጁ አያሌዎቹን የቤተመንግስቱን የመወጣጫ ደረጃዎች ዓይኑን ከማንኪያው ላይ ሳይነቅል መውጣትና መውረድ ጀመረ። ከሁለት ሰዓታት በኋላ ጠቢቡ ወደ ነበረበት ክፍል ተመለሰ።

"'እሺ' አለ ጠቢቡ፤ 'በግብር አዳራሼ ውስጥ የተሰቀሉትን የፐርሺያ ጥልፎች አይተሃቸዋል? ቤተመጻሕፍቴ ውስጥ ያሉትን ውብ ብራናዎችስ ልብ ብለሃቸዋል?'

"ልጁ አፈረ፣ ምንም እንዳላስተዋለም ተናዘዘ። ሃሳቡ ሁሉ ያረፈው በአደራ የተሰጠውን ዘይት ከመደፋት ማዳን ላይ ነበረ።

"'እንግዲያውስ ሂድና በእኔ ዓለም ውስጥ ያሉትን አስደሳች ነገሮች ተመልከት፣' አለው ጠቢቡ። 'የአንድን ሰው ቤቱን ሳታይ ሰውየውን ማመን አትችልም።'



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ልጁ እሮይ ብሎ ማንኪያውን ይዞ ቤተመንግስቱን መዞር ጀመረ፤ አሁንስ በጣሪያዎቹና በግድግዳዎቹ ላይ ያሉትን የስነጥበብ ፍሬዎች አስተዋለ። የአትክልት ሥፍራውን፣ በዙሪያው ያሉትን ተራሮች፣ የአበቦቹን ማማር እንዲሁም ሁሉ ነገር የተመረጠበትን የማጣጣም ብቃት ሁሉ አስተዋለ። ወደ ጠቢቡ ሲመለስ ያየውን ነገር እያንዳንዱን በዝርዝር ለጠቢቡ ነገረው።

"'ታዲያ በአደራ የሰጠሁህ ዘይት የታል?' ብሎ ጠቢቡ ጠየቀው።

"የያዘውን ማንኪያ ሲመለከት ዘይቱ የለም።

"'እንግዲያው አንድ ምክር ብቻ ነው ልሰጥህ የምችለው' አለው ጠቢበ ጠቢባኑ። 'የደስተኝነት ምስጢሩ የዓለምን አስደሳች ነገሮች በሙሉ መመልከት፣ ነገር ግን ማንኪያው ላይ ያለውን ዘይት አለመዘንጋት ነው።'"

እረኛው ምንም አልተናገረም። አሃውንቱ ንጉሥ የነገሩት ታሪክ ገብቶታል። አንድ እረኛ መጓዝ ይፈልግ ይሆናል፤ ይጓዝ፤ ነገር ግን በጎቹን መዘንጋት የለበትም።

አረጋዊው ብላቴናውን ተመለከቱት፤ ሁለት እጆቻቸውን አቆላልፈው፤ ብዙ ያልተለመዱ እንቅስቃሴዎችን በብላቴናው ራስ ላይ አከናወኑ። ከዚያ በኋላ እረኛው በጎቹን ይዞ ሄደ።

በታሪፋ የመጨረሻው ከፍ ያለ ሥፍራ ላይ በሙሮች የተገነባ የድሮ ምሽግ አለ። ጫፉ ላይ የወጣ ሰው አፍሪካን ማየት ይችላል። መልከጼዲቅ፣ የሳሌሙ ንጉስ በዚህ ከሰዓት የምሽጉ ግንብ ላይ ተቀምጠው ስለነበር የሌቫንተር ግፊት ፊታቸው ላይ ይሰማቸዋል። ከአዲሱ ባለቤታቸውና



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ከአዲሱ ሁኔታ ጋር መላመድ ያቃታቸው በጎች ግራ ተጋብተዋል። እነሱ የሚፈልጉት ምግብና ውሃ ብቻ ነው።

መልከጼዲቅ ከወደቡ የምትወጣውን አንዲት ትንሽ መርከብ ተመለከቱ። ልክ አንድ አስረኛ ክፍያውን ከተቀበሉት በኋላ አብርሃምን ፈጽሞ እንዳላዩት ሁሉ ብላቴናውን ከእንግዲህ ፈጽሞ አያዩትም። ሥራቸው ይሄው ነው።

አማልክቱ እጣፈንታ የላቸውምና መሻቶችም ሊኖሯቸው አይገባም። እኒህ የሳሌም ንጉሥ ግን ብላቴናው እንዲቀናው አብዝተው ተመኙ።

ስሜን ቶሎ ሊረሳው መቻሉ ደግ አይደለም ሲሉ አሰቡ። ደግሜ ብነግረው ይሻል ነበር። ስለ እኔ በተናገረ ቁጥር እኔ መልከጻዴቅ ንጉሡ ሳሌም መሆኔን ይገልጽ ነበር።

ሰማያቱን ተመለከቱ፣ እፍረት ነገር እየተሰማቸው፤ እንዲህም አሉ፡- "ጌታዬ ሆይ እንደተናገርከው ዓለም ሁሉ የከንቱ ከንቱ መሆኑንስ አውቃለሁ። ነገር ግን ሽማግሌ ንጉሥ በመጠኑም ቢሆን በራሱ ሊኮራ የተገባ ነው።"

* * *

አፍሪካ የተለየች ናት ሲል አሰበ ብላቴናው።

በታንጊየር ጠባብ ጎዳናዎች ዳር ካያቸው ቡና ቤቶች ጋር የሚመሳሰል ቡና ቤት ውስጥ ተቀምጧል። አንዳንዶቹ ሰዎች እየተቀባበሉ ትላልቅ ፒፓዎችን ያጨሳሉ። በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ወንዶች እጅ ለእጅ ተያይዘው፣ ሴቶቹ ደግሞ ፊታቸውን ተሸፋፍነው ሲተላለፉ፣ ቀሳውስቱ ማማዎች ላይ እየወጡ



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ሲቀድሱ - በአቅራቢያው የነበሩት ሰዎች ሁሉ ተንበርክከው ግንባራቸውን መሬት ሲያስነኩ ተመለከተ።

"የአረማዊያን ልማድ" አለ ለራሱ። በልጅነቱ ቤተክርስቲያን ውስጥ ቅዱስ ሳንቲያጎ ማታሞሮስ ሰይፉን መዝዞ በነጩ ፈረሱ ላይ ተቀምጦ ከሥሩ እንደነዚህ ያሉ ሰዎች ተንበርክከው ማየቱን አስታወሰ። ብላቴናው ሆዱን ባር ባር አለው፤ ከፍተኛ ብቸኝነትም ተሰማው። የአረማዊያኑ መልክ ክፉዎች መሆናቸውን ነገረው።

ከዚህም በላይ ለጉዞው ሲጣደፍ አንድ ወሳኝ ጉዳይ ዘንግቷል፤ እዚህ አገር አረብኛ ብቻ ነው የሚነገረው፤ ይሄ ከሃብት ፍለጋ ጉዞው ሊያዘገየው የሚችል ጉዳይ ነው።

የቡና ቤቱ ባለቤት ወደ እርሱ ሲጠጋ ከጎን ያለው ጠረጴዛ ላይ ያለውን ዓይነት መጠጥ አዘዘ። ሲመጣ መጠጡ መራራ ሻይ ነው። ብላቴናው ወይን ይሻለኝ ነበር አለ።

ሆኖም ይሄ አሁን አያስጨንቀውም። የሚያሳስበው ድብቅ ሃብቱና እሱን የሚያገኝበት መንገድ ብቻ ነው። ከበጎቹ ሽያጭ በቂ ገንዘብ አግኝቷል፤ ደግሞም ገንዘብ ካለ የሆነ ተአምር እንደሚኖር ያውቃል፤ ገንዘብ ያለው ሰው ፈጽሞ ብቸኛ አይሆንም። ብዙ ሳይቆይ፣ ምናልባትም በጥቂት ቀናት ውስጥ ፒራሚዶቹ ጋር ሊደርስ ይችላል። ከወርቅ የተሰራ የደረት ጥሩር የለበሱ አዛውንት መቼም ለስድስት በግ ብለው አይዋሹም።

አረጋዊው ሰው ስለ ምልክቶችና ስለ ንግሮች ተናግረው ነበር። ብላቴናው መንገዱን ሲያቋርጥ ስለ ንግሮች አሰበ። አረጋዊው ስለሚናገሩት ነገር ያውቃሉ፡- ብላቴናው ራሱም ቢሆን በአንዳሉዚያ መስኮች ያሳልፍ በነበረ ጊዜ መሬቱንና ሰማዩን በማየት ብቻ የትኛውን አቅጣጫ መከተል እንዳለበት



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ያውቅ ነበር። የሆነች ወፍ አለች፣ የእሷ በአካባቢው መታየት እባብ በአቅራቢያው አለ ማለት ነው፤ የሆነ ባለ አበባ ተክል ደግሞ አለ፤ የእሱ መገኘት እዚያ አካባቢ ውሃ መኖሩን ያመለክታል። በጎቹ እንዲህ ያለውን መረዳታቸውን አስተምረውታል።

እግዚአብሔር በጎቹን የሚመራቸው ከሆነ ሰውንም ይመራዋል ብሎ አሰበ፤ ሃሳቡ ጥሩ ስሜት ፈጠረለት። የሻዩም ምሬት የቀነሰ መሰለው።

"ማነህ አንተ?" በስፓኒሽ ቋንቋ የሚጠይቅ ድምጽ ሰማ። ብላቴናው እፎይታ ተሰማው። ስለ ንግር እያሰበ እያለ የሆነ ሰው መጣለት።

"እንዴት ስፓኒሽ ልትናገር ቻልክ?" ጠየቀው። መጪው ሰው የምዕራባውያንን ልብስ የለበሰ ወጣት ነው። ከብላቴናው ጋር የዕድሜም የቁመትም እኩያው ይመስላል።

"አብዛኛው የዚህ አገር ሰው ስፓኒሽ ይናገራል። ከዚህ ስፔን የሁለት ሰዓት መንገድ ብቻ እኮ ነው የሚያስኬድህ።"

"ተቀመጥና የሆነ ነገር ልጋብዝህ" አለው ብላቴናው። "እስኪ ለእኔም አንድ ብርጭቆ ወይን እዘዝልኝ። ይሄን ሻይ አልወደድኩትም።"

"እዚህ አገር ወይን የለም" ወጣቱ ተናገረ። "ሃይማኖቱ ወይን መጠጣትን ይከለክላል።"

ከዚያም ብላቴናው ወደ ፒራሚዶቹ መሄድ እንዳለበት ለወጣቱ ነገረው። ስለ ሃብቱ ሊነግረው ብሎ ለጥቂት ነው ካፉ የመለሰው። ቢነግረው ኖሮ አረቡ ልውሰድህና የተወሰነውን አካፍለኝ ማለቱ አይቀርም ነበር። በእጅ ያልገባን ነገር ስለመስጠት አረጋዊው የነገሩትን አልረሳም።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"እምትችል ከሆነ ብትወስደኝ ደስ ይለኛል። የመሪነትህን ዋጋ እከፍላለሁ።"

"እዚያ እንዴት እንደሚኬድ ታውቃለህ?" አዲሱ ሰው ጠየቀ።

የቡና ቤቱ ባለቤት አጠገባቸው ቆሞ ንግግራቸውን በአንክሮ እንደሚያዳምጥ አስተዋለ። የሰውየው ሁኔታ ምቾት አልሰጠውም። ሆኖም መሪ አግኝቷልና እድሉን ለማስመለጥ አልፈለገም።

"የሰሃራ በረሃን ማቋረጥ ይኖርብሃል" አለ ወጣቱ። "ለዚያ ደግሞ ገንዘብ ያስፈልግሃል። በቂ ገንዘብ ይኑርህ አይኑርህ ማወቅ አለብኝ።"

ጥያቄው እንግዳ ሆነበት። ቢሆንም አረጋዊውን አምኗቸዋል፤ እሳቸው "የሆነ ነገር ስትፈልግ ዓለም ሁሉ ታሳካው ዘንድ ሊተባበርህ ይነሳል" ብለውታል።

ገንዘቡን ከቦርሳው አወጣና ለወጣቱ አሳየው። የቡና ቤቱ ባለቤትም ወደ እነሱ ቀርቦ ተመለከተ። ሁለቱ ሰዎች በአረብኛ ተነጋገሩ፤ ባለ ቡናቤቱ የተበሳጨ ይመስላል።

"እንውጣ" አለ አዲሱ ሰው። "እንድንወጣለት ይፈልጋል።" ብላቴናው እፎይታ ተሰማው። ሊከፍል ተነሳ፤ ባለቤቱ ግን ይዞት ብስጭትጭት እያለ ያናግረው ጀመር። ብላቴናው ጠንካራ ነው፤ ሊበቀለው ፈለገ፤ ሆኖም ያለው እሰው አገር ነው። አዲሱ ጓደኛው ባለቤቱን ወደ ጎን ገፋውና ብላቴናውን እየጎተተው ወጣ። "ገንዘብህን ሊወስድብህ ፈልጎ ነው" አለው። "ታንጊየር እንደተቀረው አፍሪካ አይደለችም። ወደብ ናት፤ ሁሉም ወደቦች ደግሞ የየራሳቸው ሌቦች አሏቸው።"

ብላቴናው አዲሱን ጓደኛውን አመነው። በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ ረድቶታል። ገንዘቡን አወጣና ቆጠረው።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ነገ ፒራሚዶቹ ጋር መድረስ እንችላለን" አለ ወጣቱ ገንዘቡን እየወሰደ። "ነገር ግን ሁለት ግመሎች መግዛት አለብኝ።"

በታንጊየር ጠባብ ጎዳናዎች አለፉ። በየቦታው የተለያዩ እቃዎች የሚሸጡባቸው መደብሮች አሉ። ትልቁ የመገበያያ ሜዳ ጋር ደረሱ። እልፍ አእላፍ ገበያተኞች ይከራከራሉ፤ ይገዛሉ፤ ይሸጣሉ። አትክልቶች ከዶማዎች ጋር፣ ምንጣፎች ከትንባሆ ጋር ለሽያጭ ቀርበዋል። ብላቴናው ግን ዓይኑን ከአዲሱ ጓደኛው ላይ ፈጽሞ አልነቀለም። ገንዘቡን ሰጥቶታላ። እንዲመልስለት ሊጠይቀው አሰበና ወዳጅነታቸውን እንዳያበላሸው ሰግቶ ተወው። ምክንያቱም የዚህን ባእድ አገር ሰዎች አመል አያውቀውም።

'በዓይኔ እከታተለዋለሁ' አለ ለራሱ። እሱ ከጓደኛው በጥንካሬ እንደሚሻል ያውቃል።

በድንገት፣ በዚያ ወከባ መሐል እስከዛሬ ካያቸው ሁሉ በውበቷ የምታስደንቅ ጎራዴ ተመለከተ። ስስ የብር ክፈፍ የተሰራላት፣ እጀታዋ ጥቁር ሆኖ በከበሩ ድንጋዮች ያጌጠ ነው። ብላቴናው ከግብጽ ሲመለስ እንደሚገዛት ለራሱ ቃል ገባ።

"እስኪ የዚያን መደብር ባለቤት የጎራዴዋን ዋጋ ጠይቀው" አለው ጓደኛውን። ጎራዴዋ ላይ ሲያተኩር ለጥቂት ሰከንዶች ፈዝዞ እንደነበረ ተገነዘበ። ድንገት ደረቱ የተጫናት ይመስል ልቡ ተጨነቀች። ዞሮ ማየት ፈራ፤ ምን እንደሚገጥመው ያውቃልና። ያቺን ውብ ጎራዴ መመልከቱን ቀጠለ፣ ወደ ኋላው መመልከት ድፍረት እስኪያገኝ ድረስ።

በዙሪያው ያለው ላይ ታች የሚሉ፣ የሚጮሁና የሚገበያዩ ሰዎች፣ የማያውቃቸው ምግቦች መዓዛ ያለበት ገበያ ነው። ጓደኛውን ግን የትም ሊያገኘው አልቻለም።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ከጓደኛው ጋር ባጋጣሚ እንደተጠፋፉ ማመን ፈለገ። ስለዚህም ባለበት ቆይቶ እስኪመጣ ድረስ ሊጠብቀው ወሰነ። እየጠበቀው እያለም አንድ ቄስ በአቅራቢያው ወዳለ ማማ ወጣና መቀደስ ጀመረ፤ ገበያተኛው ሁሉ በጉልበቱ ተንበርክኮ፣ በግንባሩ መሬት ላይ ተደፍቶ ቅዳሴውን ተቀበለው። ከዚያም ልክ እንደሰራተኛ ጉንዳኖች ሁሉም ጊዜያዊ መደብሮቻቸውን አፈራርሰው ሄዱ።

ፀሐይዋም እንደነሱ መሔድ ጀመረች። ብላቴናው ለጥቂት ጊዜ እንቅስቃሴዋን ተከታተለ - በገበያው ዙሪያ ባሉት ነጫጭ ቤቶች ጀርባ እስክትሰወር ድረስ። የዚያን ቀን፣ ማለዳ ጸሐይዋ ስትወጣ እሱ ስድሳ በጎች ያሉት፣ አንዲትን ኮረዳ ለማግኘት የጓጓ እረኛ ነበረ። በዚያ ማለዳ በለመዳቸው መስኮች ሲያልፍ ወደፊት ምን እንደሚያጋጥመው ያውቅ ነበር። አሁን ግን፣ ፀሐይዋ መጥለቅ ስትጀምር፣ እሱ ያለው በባእድ ምድር ባእድ ሆኖ ቋንቋውን እንኳን መረዳት በማይችልበት የሰው አገር ነው። እረኝነቱ አብቅቷል፤ ደግሞም ምንም የለውም፤ እንደገና ከአዲስ ልጀምር ቢል እንኳን ገንዘብ የለውም። —

'ይሄ ሁሉ የሆነው ጀንበር ወጥታ እስክትጠልቅ ባለው ጊዜ ነው' ብሎ አሰበ። ለራሱ አዘነ፤ ህይወቱ በድንገት በአስከፊ ሁኔታ በመለዋወጡም ሰቆቃው ከፋበት።

ማልቀስ በመፈለጉ እፍረት ተሰማው። በበጎቹ ፊት እንኳን አንብቶ አያውቅም። ነገር ግን ገበያው ባዶ ነው፤ ስለዚህም አነባ። ያነባው እግዚአብሔር ፍርዱን ስላለማስተካከሉና፣ በሕልማቸው የሚያምኑ ሰዎችን የሚቀጣው በዚህ መንገድ ስለመሆኑ ነው።

ከበጎቹ ጋር እያለሁ ደስተኛ ነበርኩ፤ በዙሪያዬ ያሉትንም አስደስታቸው ነበር። ስመጣ ያዩኝ ሰዎች በደስታ ይቀበሉኝ ነበር ብሎ አሰበ። አሁን ግን



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

የከፋኝ ብቸኛ ነኝ። አንድ ሰው ከድቶኛልና ምሬቴ ሲበዛና ሰው ማመኔም ሊጠፋ ነው። ድብቅ ሐብቴን አላገኘሁምና ድብቅ ሐብታቸውን ያገኙ ሰዎችን መጥላቴ ነው። ዓለምን መጨበጥ የሚያስችል አቅም ስለሌለኝ ባለኝ ትንሽ ነገር ተወስኜ ልቀርም ነው።

የተረፈውን ንብረቱን ለማየት ቦርሳውን ከፈተ፤ መርከቡ ላይ ሲበላው ከነበረው ሳንዱች የተረፈ ያገኝ ይሆናል። ማግኘት የቻለው ግን ከባዱን መጽሐፍ፣ ጃኬቱንና አረጋዊው የሰጡትን ሁለት ድንጋዮች ብቻ ነው።

ድንጋዮቹን ሲመለከት በሆነ ምክንያት እፎይታ ተሰማው። ስድስት በጎቹን ከወርቅ ከተሰራው የደረት ጥሩር ውስጥ በወጡ ሁለት ውድ ድንጋዮች ቀይሯቸዋል። ድንጋዮቹን ሸጦ የመመለሻ ትኬት መግዛት ይችላል። አሁን ግን የበለጠ ብልጥ መሆን አለብኝ ብሎ አሰበ ድንጋዮቹን ከቦርሳው አውጥቶ ኪሱ ውስጥ እየጨመራቸው። ይሄ የወደብ ከተማ ነው፤ እናም ጓደኛው የነገረው ብቸኛው ሐቅ እዚህ ከተማ ሌቦች መብዛታቸው ነው።

የቡና ቤቱ ባለቤት ለምን ተበሳጭቶ እንደነበረ አሁን ገባው፡- ያንን ሰው እንዳያምነው ሊነግረው እየሞከረ ነበር "እኔ እንደማንም ሰው ዓለምን የማየው በሆነው ሳይሆን እንዲሆንልኝ በምመኝበት ዓይን ነው።"

ጣቶቹን በድንጋዮቹ ላይ በዝግታ እያመላለሰ ሙቀት - ቅዝቃዜያቸውንና መለስለስ መሻከራቸውን ይመረምር ገባ። እነሱ ነበሩ ሃብቶቹ። እነሱን መያዙ ብቻ የተሻለ ስሜት ፈጠረለት። ድንጋዮቹ አረጋዊውን አስታወሱት።

"አንተ የሆነ ነገር ስትፈልግ ዓለም ሁሉ ሊተባበርህ ይነሳል" ብለውታል።

የአረጋዊው አባባል ውስጥ ያለውን እውነት ለመረዳት ሞከረ። አሁን ያለው የራሴ የሚለው አንድ ሳንቲም፣ የሚጠብቀው አንድ በግ እንኳን ሳይኖረው



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

የተራቆተ የገበያ ሥፍራ ላይ ነው። ድንጋዮቹ ግን ከንጉሥ ጋር የመገናኛቱ ማረጋገጫዎች ናቸው - የብላቴናውን ያለፈ ህይወት ጠንቅቆ ከሚያውቅ ንጉሥ ጋር።

"ዑሪምና ቱሚም ይባላሉ። ንግሮችህን ለማንበብ ይረዱሃል።" ብላቴናው በርሳው ውስጥ ከተታቸውና ሊፈትናቸው ወሰነ። አረጋዊው ጥያቄውን ግልጽ መሆን እንዳለበት ነግረውታል፤ ለዚህ ደግሞ መጀመሪያ የሚፈልገውን ማወቅ አለበት። ስለዚህም የአረጋዊው ባርኮት አሁንም አብሮት ስለመኖሩ ጠየቀ።

አንደኛውን ድንጋይ አወጣ። "አዎ" የሚል ሆነ።

"ሃብቴን አገኛለሁን?" ጠየቀ። እጁን ከቦርሳው ውስጥ ከትቶ አንዳቸውን ለማውጣት ዳሰሰ። በዚህ ጊዜ ሁለቱም ተገፍተው ቦርሳው ውስጥ ባለ አንድ ቀዳዳ መሬት ወደቁ። ብላቴናው እስከዛሬ ቦርሳው ቀዳዳ እንዳለው አያውቅም ነበር። ተንበርክኮ ዑሪምና ቱሚምን አነሳና ወደ ቦርሳው መለሳቸው። መሬት ሆነው ባያቸው ቅጽበት ግን ሌላ የአረጋዊው ንግግር ታወሰው።

"ንግሮችህን ለይተህ እወቅና ተከተላቸው" ብለውታል አዛውንቱ ንጉሥ።

አንድ ንግር። ብላቴናው ለራሱ ፈገግ አለ። ድንጋዮቹን ወደ ቦርሳው መለሳቸው። ቀዳዳውን መጠገን አላሳሰበውም፤ ድንጋዮቹ በፈለጉ ጊዜ ሊወድቁ ይችላሉ። ሰዎች ከእጣ ፈንታቸው እንዳያርቋቸው ሲባል ሊጠይቋቸው የማይገቡ ጥያቄዎች እንዳሉ ተምሯል። "የራሴን ውሳኔ ለመወሰን ቃል ገብቻለሁ" የራሱ ጆሮዎች ብቻ ሊሰሙት በሚችሉት ድምጽ ተናገረ።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ነገር ግን ድንጋዮቹ አረጋዊው አሁንም አብረውት እንዳሉ ነግረውታል፤ ይሄ ደግሞ የበለጠ ልበ ሙሉ አደረገው። ባዶውን የገበያ ሥፍራ በድጋሚ ተመለከተው፤ አሁን ተስፋ መቁረጡ ቀንሷል። ይሄ ባእድ ምድር ሳይሆን አዲስ ምድር ነው።

ለነገሩ እሱም ሁልጊዜ የሚፈልገው አዳዲስ ሥፍራዎችን ማወቅ ነው። ፒራሚዶቹ ጋር ባይደርስ እንኳን ከሚያውቃቸው ሁሉ እረኞች የበለጠ ርቆ ተጉዟል። ምነው ሁለት ሰዓት በመርከብ ተጉዘው የሚያጋጥሟቸውን የተለዩ ነገሮች ባወቁ። የእሱ ዓለም ለጊዜው ባዶ የገበያ ሥፍራ ቢሆንም፣ በህይወት ተሞልቶ አይቶታል፤ ያየውንም ፈጽሞ አይዘነጋውም። ጎራዴዋን አስታወሳት። ስለ እሷ ማሰብ በጥቂቱ ስሜቱን ጎዳው፤ ነገር ግን እሷን የመሰለ ጎራዴ ከዛሬ በፊት አይቶ አያውቅም። እነዚህን ሃሳቦች እያብሰለሰለ እያለ ራሱን እንደ አንድ በሌባ የተዘረፈ ምስኪን ወይም ሐብት ፍለጋ እንደሚጓዝ ጀብደኛ መቁጠር እንዳለበት ሲመርጥ እንደሚገባ ተገነዘበ።

"እኔ ሐብት ፍለጋ የወጣሁ ጀብደኛ ነኝ" አለ ለራሱ።

* * *

የሆነ ሰው ቀሰቀሰው። ገበያው መሐል እንቅልፍ ጥሎት ነበር፤ አሁን ደግሞ አካባቢው ነፍስ እየዘራ ነው። ቀና ብሎ ዙሪያውን ተመለከተ፣ በጎቹን በዓይኑ እየፈለገ፤ ወዲያው ግን አዲስ ዓለም ውስጥ እንዳለ አስተዋለ። በማዘን ፈንታ ተደሰተ። ለበጎቹ ምግብና ውሃ ፍለጋ መንከራተት አይጠበቅበትም፤ ይልቁንም ሐብት ፍለጋ ይሄዳል። ኪሱ ውስጥ ሽራፊ ሳንቲም ባይኖረውም እምነት አለው። በመጻሕፍት እንደሚያደንቃቸው ጀብደኞች ለመሆን ማታ ወስኗል።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

በገበያው መሐል ዝግ ብሎ ተጓዘ። ነጋዴዎቹ መደቦቻቸውን እያበጃጁ ነው፤ ልጁም አንዱን ከረሜላ ሻጭ በማበጃጀቱ ሥራ አገዘው። ከረሜላ ሻጩ ፈገግተኛ ነው፡- ደስተኛ ነው፤ የህይወቱ ዓላማ ገብቶታል፤ ስለዚህ ሥራ ለመጀመር ዝግጁ ነው።

የነጋዴው ፈገግታ ምስጢራዊውን አረጋዊ ንጉሥ አስታወሰው። "ይሄ ከረሜላ ሻጭ ከረሜላ የሚሰራው መሥራት የሚፈልገው ይህንኑ በመሆኑ ነው" ብሎ አሰበ ብላቴናው። አዛውንቱ እንዳደረጉት እሱም አንድ ሰው ወደ እጣፈንታው መቃረብ አለመቃረቡን መረዳት እንደሚችል ተገነዘበ - ሰውየውን በማየት ብቻ። ቀላል ነው፣ ሆኖም ከዚህ በፊት ሞክሬው አላውቅም ሲል አሰበ።

መደቡ ከተስተካከለት በኂላ ከረሜላ ሻጩ በዚያ ጠዋት መጀመሪያ የሠራትን ጣፋጭ ለብላቴናው ሰጠው። ብላቴናው አመስግኖት እየበላት ወደ መንገድ ገባ፤ ትንሽ ርቀት እንደሄደ የነጋዴውን መደብ እየዘረጉ እያለ ሁለት ሰዎች አንደኛው በስፓኒሽ ሌላኛው ደግሞ በአረብኛ ይነጋገሩ እንደነበር አስታወሰ።

ደግሞ ሙሉ በሙሉ ተግባብተው ነበር። የቃላት ጥገኛ ያልሆነ ቋንቋ መኖር አለበት ብሎ አሰበ ብላቴናው። እሱ ራሱ ከበጎቹ ጋር ሲያደርገው ኖሯል፤ አሁን ደግሞ ሰዎች ሲጠቀሙበት አጋጠመው።

ብዙ አዳዲስ ነገሮችን እየተማረ ነው። አንዳንዶቹን ቀድሞውኑ ቢያውቃቸውም አስበባቸው አያውቅም ነበር። አስበባቸው የማያውቀው ደግሞ ስለለመዳቸው ነው። እንዲህ አሰበ፡- ይህንን ቃላት የለሽ ቋንቋ መረዳት ከቻልኩ፣ ዓለምን መረዳት እችላለሁ።

ዘና - ረጋ ብሎ በታንጊየር ጠባብ ጎዳናዎች ለማለፍ ወሰነ፤ ንግሮችን ማንበብ የሚችለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው። ብዙ ትእግስት



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

እንደሚያስፈልገው ያውቃል፤ እረኞች ደግሞ መታገስን ተክነውታል። አሁንም በዚህ ባእድ መሬት የሚጠቀምበት እውቀት ከበጎቹ የተማረው መሆኑን አስተዋለ።

"ሁሉም ነገር አንድ ነው" ብለዋል አረጋዊው።

* * *

ክሪስታል ሻጩ ከእንቅልፉ ሲነቃ ዛሬም እንደሌላው ቀን ጨንቆት ነበር። እዚሁ ቦታ ሰላሳ ዓመት ቆይቷል፡- ጥቂት ሸማቾች ብቻ በሚያልፉበት ኮረብታማ መንገድ ላይ ባለች መደብሩ ውስጥ። አሁን ምንም ነገር ለመለወጥ ዘግይቷል - የሚያውቀው ብቸኛ ነገር ክሪስታል መሸጥና መግዛት ነው። መደብሩ የአረብ ነጋዴዎችን፣ የፈረንሳይና የእንግሊዝ የስነምድር ተመራማሪዎችን እንዲሁም የጀርመን ወታደሮችን በመሳሰሉ ባለጸጎች የሚጨናነቅበት ጊዜ ነበር። በነዚያ ጊዜያት ክሪስታል መሸጥ ሀሪፍ ተግባር ነበር፤ እሱም ባለፀጋ እንደሚሆንና ሲሸመግልም ቆንጆ ቆንጆ ወይዛዝርት ግራና ቀኝ እንደሚያጅቡት ያስብ ነበር።

ነገር ግን ቀስ በቀስ ታንጊየር ተለወጠች። ጎረቤቷ ሴዩታ ከተማ ከታንጊየር ፈጥና ተመነደገች፤ ስለዚህም ንግዱ ቀዘቀዘ። በአቅራቢያው ያሉ ነጋዴዎች ታንጊየርን ጥለው ሲሄዱ ጥቂት ትናንሽ ሱቆች ብቻ ኮረብታው ላይ ቀሩ። እነዚህን ጥቂት ትናንሽ መደብሮች ለመጎብኘት ብሎ ኮረብታውን የሚወጣ ገበያተኛ አልነበረም።

ክሪስታል ሻጩ ግን ምርጫ አልነበረውም። ከህይወቱ ላይ ሰላሳውን ዓመታት ያሳለፈው ክሪስታሎችን በመግዛትና በመሸጥ ነው፤ አሁን ደግሞ ሌላ ነገር ለማድረግ ዘግይቷል።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ሙሉ ጠዋቱን ያሳለፈው አልፎ አልፎ መንገዱ ላይ ሔድ-መጣ የሚሉትን ሰዎች እያስተዋለ ነው። ይህንንም ሲያደርግ አመታት ተቆጥረዋል፤ ስለሆነም አላፊ አግዳሚውን መንቀሰቀሻ ጊዜ አውቆታል። ሆኖም ልክ ከምሳ ሰዓት በፊት አንድ ልጅ መደብሩ ፊት ለፊት ተገተረ። አለባበሱ ደህና ነው፤ ክሪስታል ሻጩ ግን በልምድ ባካበተው ብቃት፣ ልጁ የሚገዛበት ምንም ገንዘብ እንደሌለው መረዳት ችሏል። ነገር ግን ነጋዴው ልጁ እስኪሄድለት ድረስ ምሳውን ለማዘግየት ወሰነ።

* * *

በሩ ላይ የተሰቀለ አንድ ካርቶን መደብሩ ውስጥ አያሌ ቋንቋዎች እንደሚነገሩ ያስታውቃል። ብላቴናው ገንዘብ መቀበያው ጀርባ አንድ ሰው ተመለከተ።

"መስኮቱ ላይ ያሉትን ጠርሙሶች ልወለውላቸው እችላለሁ፣" አለ ብላቴናው "በዚህ ሁኔታቸው ማንም ሊገዛቸው ፍላጎት አይኖረውም።"

ሰውየው በፀጥታ ተመለከተው።

"አንተ ደግሞ በለውጡ የሚበላ ነገር ትሰጠኛለህ።"

ሰውየው አሁንም አልተናገረም፤ ብላቴናው ግን ራሱ መወሰን እንዳለበት ገባው። በርሳው ውስጥ ጃኬቱ አለ - በረሃው ውስጥ ደግሞ ጃኬት አያስፈልገውም። ስለዚህ ከቦርሳው አወጣውና ጠርሙሶቹን መወልወል ጀመረ። በግማሽ ሰዓት ውስጥ መስኮቱ ላይ የነበሩትን ጠርሙሶች ወልውሎ ጨረሰ። እሱ እየወለወለ ሳለ ሁለት ገበያተኞች ወደ መደብሩ ገብተው ክሪስታል ገዝተው ወጥተዋል።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ማጽዳቱን ሲያጠናቅቅ ሰውየውን የሚበላ ነገር ጠየቀው። ክሪስታል ነጋዴውም "እንሂድና ምሳ እንብላ፣" አለው።

በሩ ላይ ምልክት አስቀምጠው ወደ አንድ ትንሽዬ ካፌ ሔዱ። ካፌ ውስጥ የነበረው ብቸኛ ጠረጴዛ ጋር እንደተቀመጡ፣ ክሪስታል ነጋዴው ሳቀ።

"መወልወል አልነበረብህም" ነጋዴው ተናገረ። "ቅዱስ ቁርአን የተራበን ሰው እንድንመግብ ያስገድደናል።"

"ታዲያ ስወለውል ለምን ዝም አልከኝ?" ጠየቀው ብላቴናው

"ምክንያቱም ክሪስታሎቹ ቆሽሸው ነበር። እኔ እና አንተ ደግሞ አእምሯችንን ከአሉታዊ ሃሳቦች ማጽዳት አለብን።"

እየበሉ እያለ ነጋዴው ወደ ብላቴናው ዞሮ፣ "መደብሬ ውስጥ ብትሰራ ደስ ይለኛል። አንተ እየሰራህ እያለ ሁለት ገዢዎች መጥተው ነበር ዛሬ፤ ይሄ ደግሞ ጥሩ ንግር ነው" አለው።

ብላቴናው በበኩሉ ሰዎች ስለንግር ብዙ ያወራሉ። ሆኖም የሚሉትን አያውቁም - ልክ እኔ ከበጎቼ ጋር በቃላት አልባ ቋንቋ መግባባቴን ሳልረዳ እንደቆየሁት ማለት ነው፤ ብሎ አሰበ።

"እኔ ጋር ተቀጥረህ መሥራት ትፈልጋለህ?" ነጋዴው ጠየቀ።

"ዛሬ ልሰራልህ እችላለሁ" ብላቴናው መለሰ። "ሌሊቱን ሙሉ ጎህ እስኪቀድ ድረስ መደብሩ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ክሪስታሎች አፀዳልሃለሁ። በምላሹ ነገ ግብጽ የምሔድበት ገንዘብ ያስፈልገኛል።"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ነጋዴው ሳቀ። "ክሪስታሎቹን ዓመት ሙሉ ብታጸዳ እንኳን... አያንዳንዱን ሸጠህልኝ ጥሩ ጉርሻ ብታገኝም እንኳን፣ ግብጽ ለመግባት ተጨማሪ ገንዘብ መበደር ይኖርብሃል። በዚህና በግብጽ መካከል በሺህ የሚቆጠሩ ኪሎሜትሮች የሚረዝም እልም ያለ በረሃ ይጠብቅሃል።"

ለጥቂት ጊዜ ያህል ከተማዋ ያንቀላፋች እስኪመስል ድረስ የሚከብድ ጸጥታ መሐላቸው ሰፈነ። ከገበያው ቦታ የሚመጡ ድምጾች፣ ከነጋዴዎቹ የሚሰማ ክርክር፣ ማማው ላይ ወጥተው የሚቀድሱ ሰዎች ዝማሬ የለም። ተስፋ የለም፤ ጉዞ የለም፤ አረጋዊ ንጉሥ ወይም እጣፋንታዎች የሉም፤ ድብቅ ሃብት የለም፤ ፒራሚዶችም የሉም። የብላቴናው ነፍስ ጭጭ ብላለችና ዓለም ሁሉ ጭጭ ያለ መሰለው። ብላቴናው ምነው በሞትኩና ሁሉ ነገር በዚያች ቅጽበት በተቋጨ ብሎ እያሰበ ዓይኖቹን በሩ ላይ ተክሎ ፈዝዟል።

ነጋዴው ብላቴናውን በጭንቀት ተመለከተው። ጠዋት ያየው ደስታ በሙሉ ድንገት ጠፍቷል።

"ወደ አገርህ መመለስ የሚያስችልህን ገንዘብ ልሰጥህ እችላለሁ" አለ ክሪስታል ነጋዴው።

ብላቴናውም ምንም አላለም። ተነሳና ልብሱን አስተካክሎ ቦርሳውን አነሳ።

"አብሬህ እሰራለሁ" አለ በመጨረሻ።

ከሌላ ረጅም ዝምታ በኋላ ደግሞ ቀጠለ፣ "ጥቂት በጎች ለመግዛት ገንዘብ ያስፈልገኛል።"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

# ክፍል ሁለት

ብላቴናው ለክሪስታል ነጋዴው ወር ገደማ ሰራለትና ሥራው የሚያስደስተው ዓይነት ሥራ አለመሆኑን ተረዳ። ነጋዴው ከገንዘብ መክፈያው ጀርባ ሆኖ ቀኑን ሙሉ ብላቴናውን ክሪስታሎቹን በጥንቃቄ እንዲይዛቸው፣ እንዳይሰብራቸው ለማስጠንቀቅ ሲያጉተመትም ይውላል።

ብላቴናው እዚህ ያቆየው ምንም እንኳን ነጋዴው ነዝናዛ ብጤ ቢሆንም ለእሱ ያለው ቀረቤታ ጥሩ መሆኑ ነው። ብላቴናው በየሸጠው ክሪስታል ጥሩ ጉርሻ ስለሚቀበል ገንዘብ ማጠራቀም ጀምሯል። ዛሬ ጠዋት ሂሳቡን አሰላ፦ እንደሰሞኑ በየቀኑ እንኳን ቢሰራ ጥቂት በጎች ለመግዛት ዓመት ያስፈልገዋል።

“ለክሪስታሎቹ ማሳያ ሳጥን ልሰራላቸው እፈልጋለሁ” አለው ብላቴናው ነጋዴውን። “እደጅ አስቀምጠነው በኮረብታው ሥር የሚያልፉትን ሰዎች መሳብ እንችላለን።”



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ኖሮኝ አያውቅም" ነጋዴው መለሰለት። "ሰዎች ሲተላለፉ ይጥሉትና ክሪስታሎቹ ይሰባበራሉ።"

"አየህ፣ በጎቼን ሳሰማራ እባብ ቢያጋጥመኝ አንዳቸው ሊሞቱብኝ ይችላሉ። ነገር ግን የበጎችና የእረኞች ህይወት ሁሌም እንደዚሁ ነው።"

ነጋዴው ሶስት ክሪስታሎችን መግዛት ወደሚፈልገው ገዢ ዞረ። አሁን ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ገበያ ኖሮታል፤ የኮረብታው መንገድ ከታንጊየር ዋነኛ መስህቦች አንዱ የነበረበት የጥንቱ ዘመን የተመለሰ ሁሉ ይመስለዋል።

"ንግዳችን ተሻሽሏል" አለው ብላቴናውን ገዢው ከሔደ በኋላ።

"የእኔ ገቢ ከፍ ብሏል፤ አንተም በቅርቡ ወደ በጎችህ መመለስ ትችላለህ። ከዚህ በላይ ምን አስመኘህ?"

"ለንግሮቹ ምላሽ መስጠት ስላለብን ነዋ" አለው ብላቴናው ያለውን ማለት ሳያስብ፤ ነጋዴው አረጋዊውን ንጉሥ አግኝቷቸው አያውቅም።

"ለእገዛ የመመረጥ መርህ ይባላል፤ የጀማሪ እድል። ምክንያቱም ህይወት እጣፈንታህን እንድታሳካ ትፈልጋለች" ብለዋል አረጋዊው ንጉሥ።

ሆኖም ነጋዴው ብላቴናው ያለው ገብቶታል። ከመነሻው የብላቴናው ወደ መደብሩ መምጣት በራሱ ንግር ነበር፤ ቀስ በቀስ ገንዘብ ካዝናውን እየሞላው ሲመጣ ደግሞ ብላቴናውን መቅጠሩ የሚያጸጽተው አልሆነም። ክሪስታሎቹ አይሸጡም ብሎ ለብላቴናው ቃል የገባለት ጉርሻ ትልቅ በመሆኑ አሁን ብላቴናው የማይገባውን ክፍያ እያገኘ እንደሆነ ግን ተሰምቶታል። ደግሞም ቶሎ ወደበጎቹ ይሄዳል ብሎ አስቦ ነበር።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ወደ ፒራሚዶቹ ለምን መሔድ ፈለግህ?" ሲል ጠየቀው የማሳያ ሳጥኑን ሃሳብ ለማረሳሳት፡፡

"በየጊዜው ስለ እነሱ እሰማ ስለነበር" ብሎ መለሰ ብላቴናው ስለህልሙ ምንም ሳያነሳ፡፡ ድብቁ ሃብት አሁን ስሜት የሚጎዳ ትዝታ ሆኖበታል፤ ስለዚህም እሱን ላለማሰብ ይሞክራል፡፡

"ፒራሚዶቹን ለማየት ብቻ ሲል በረሃውን ማቋረጥ የሚፈልግ ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም" አለ ነጋዴው፡፡ "እነሱ እኮ የድንጋይ ክምር ናቸው፡፡ አንተም ጓሮህ ልትሰራቸው ትችላለህ፡፡"

"የመጓዝ ህልም ኖሮህ አያውቅም" ሲል ብላቴናው፣ ነጋዴው ወደ መደብሩ ወደገባው ገበያተኛ ሄደ፡፡

ከሁለት ቀናት በኂላ ነጋዴው ብላቴናውን ስለማሳያው ሳጥን አዋራው፡፡

"ለውጥ ብዙም አልወድም" አለው፡፡ "እኔና አንተ እንደ ባለፀጋው ሐሰን አይደለንም፡፡ እሱ ሲገዛ ስህተት ቢሰራ ኪሳራው ብዙም አይጎዳውም፡፡ እኛ ግን በስህተታችን ምክንያት እንማቅቃለን፡፡"

'እውነቱን እኮ ነው' ብሎ አሰበ ብላቴናው በሃዘኔታ፡፡

"ማሳያው የሚያስፈልገን ለምን ይመስልሃል?"

"በፍጥነት ወደ በጎቹ መመለስ እፈልጋለሁ፡፡ እድል በቀናችን ሰዓት እድላችንን መጠቀም አለብን፤ እሷ ልትረዳን የምትሰራውን ያህል እኛም በመስራት ልናግዛት ይገባል፡፡ ለአገዛ የመመረጥ መርህ ይባላል፡፡ ወይም የጀማሪ እድል፡፡"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ነጋዴው ለአፍታ ዝም አለ። ከዚያም እንዲህ አለ፦ "ነቢያችን ቁርአንን ሰጡን፤ በሕይወት ዘመናችን ልናከናውናቸው የሚገባውን አምስት ግዴታዎችም ተዉልን። ከእነዚህ ዋነኛው በአንድ አምላክ ማመን ነው። ሌሎቹ በቀን አምስት ጊዜ መጸለይ፣ በረመዳን ወራት መጾም፣ ለድሆች መመጽወት።"

እዚሁ ላይ አቆመው። ስለ ነቢዩ ሲናገር ዓይኖቹ በእንባ ተሞሉ። ሃይማኖተኛ ሰው ነው፤ ትእግስት ባይኖረውም ከሙስሊም ሕግ ጋር ተስማምቶ መኖር ይፈልጋል።

"አምስተኛው ግዴታ ምንድነው?" ጠየቀ ብላቴናው።

"በቀደምለት የመጓዝ ህልም ኖሮህ አያውቅም ብለኸኝ ነበረ" መለሰ ነጋዴው። "የእያንዳንዱ ሙስሊም አምስተኛው ግዴታ ቅዱስ ጉዞ ነው። በህይወታችን ቢያንስ አንድ ጊዜ ቅድስት መዲናችንን መካን መጎብኘት እንገደዳለን።

"መካ ከፒራሚዶቹም በጣም ትርቃለች። ወጣት እያለሁ እመኘ የነበረው በቂ ገንዘብ ሰብስቤ ይህቺን መደብር መክፈት ነበር። አንድ ቀን ሀብታም ሆኜ ወደ መካ መሔድ የምችልም ይመስለኝ ነበር። ገንዘቡን ሳገኝ ይህን መደብር በአደራ የምሰጠው ሰው አጣሁ፤ ክሪስታሎች ጥንቃቄ የሚፈልጉ እቃዎች ናቸው። በዚያው ጊዜ ሰዎች በመደብሬ በኩል እያለፉ ወደ መካ ይጓዛሉ። አንዳንዶቹ ሃብታሞች በመሆናቸው በህብረት ሆነው ግመሎቻቸው ላይ ተቀምጠው፣ አገልጋዮቻቸውን አስከትለው ይሔዳሉ። አብዛኞቹ ተጓዦች ግን ከእኔ የባሱ ድሆች ነበሩ።

"መካ የሔዱ ሁሉ በመሔዳቸው ይደሰታሉ። የጉዟቸውን ትእምርቶች በቤቶቻቸው በሮች ላይ ያደርጋሉ። ከእነዚህ መሀል አንዱ የሆነው ጫማ



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ሰፊው መካ ለመድረስ ዓመት ያህል በበረሃው ውስጥ ተጉዟል፤ ነገር ግን ታንጊየር ቆዳ ለመግዛት እንደመንከራተት የሚያደክመኝ የለም ይላል።"

"ታዲያ አሁን መካ ለምን አትሔድም?" ብላቴናው ጠየቀው። በህይወት ያቆየኝ ስለ መካ ማሰቤ ነው። እሱ ነው ሁሉ ነገር ተመሳሳይ በሆነብኝ ዘመን፣ ከነዚህ አፍ የለሽ ክሪስታሎች ጋር፣ ምሳና ራቴን መቀየሪያ በሌለው አስቀያሚ ሻይ ቤት እየተመገብኩ እንድቆይ የረዳኝ። ህልሜ እውን ከሆነ በኋላ በህይወት የምቆይበት ምክንያት እንዳላጣ እሰጋለሁ።

"አንተ ስለበጎችህና ስለ ፒራሚዶች ታልማለህ፤ አንተ ግን ከእኔ ትለያለህ፤ ምክንያቱም ህልሞችህን እውን ማድረግ ትፈልጋለህ። እኔ ስለመካ ማለም ብቻ ነው የምፈልገው። በረሃውን ስለማቋረጥ፣ የቅድስ አለት አደባባይ ጋር ስለመድረስ፣ እሱንም ከመዳሰሴ በፊት በዙሪያው ሰባት ጊዜ ስለመዞር ሺ ጊዜ አስቤያለሁ። ከጎኔ እና ከፊቴ ስለሚሆኑ ሰዎች፣ ስለምንለዋወጣቸው ሐሳቦችና ስለጸሎቶቻችን ብዙ ጊዜ አስቤያለሁ። ሆኖም እንዳያስከፋኝ ስለምፈራ ሳልመው መኖርን መርጫለሁ።

የዚያኑ ቀን ነጋዴው ማሳያውን ሳጥን ይሰራ ዘንድ ለብላቴናው ፈቀደለት። የሁሉም ሰው ህልም በተመሳሳይ መንገድ እውን አይሆንም።

* * *

ሌሎች ሁለት ወራት አለፉ፤ ማሳያው መደርደሪያ ብዙ ገዢዎችን ወደ መደብሩ ሳበ። ብላቴናው በተጨማሪ ስድስት ወራት ከሰራ ወደ ስፔን ተመልሶ ስድሳ በጎች፣ እንደገናም ስድሳ በጎች መግዛት እንደሚችል ገመተ። ከዓመት ባነሰ ጊዜ የበጎቹን ቁጥር እጥፍ ያደርጋል፤ ከዚያም አሁን ባእድ



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ቋንቋቸውንም ስለሚናገር ከአረቦች ጋር በጋራ መነገድ ይጀምራል። ገበያ ውስጥ ከእንቅልፍ ከነቃበት ማለዳ ወዲህ ዑሚምና ቱሪም አልተጠቀመባቸውም፤ ምክንያቱም መካ ለነጋዴው የራቀችውን ያህል ግብጽም ለእሱ ሩቅ ህልሙ ሆናለች። ለማንኛውም አሁን በሥራው ደስተኛ ሆኗል፤ የሚያስበውም ስኬታማ ሆኖ የታሪፋን መሬት መልሶ ስለሚረግጥበት ጊዜ ብቻ ነው።

"ምንጊዜም የምትፈልገውን ነገር ምንነት ማወቅ አለብህ" ብለውታል አረጋዊው ንጉሥ። የሚፈልገውን አውቆታል፤ እሱንም ለማግኘት እየተጋ ነው። በዚህ ባእድ ምድር መርጋት፣ ከሌባ ጋር መገናኘት፣ አንድ ሳንቲም ሳያወጣ የመንጋውን ቁጥር እጥፍ ማድረስ ይሆናል የእሱ ድብቅ ሃብት።

በራሱ ይኮራል። ክሪስታል ለመሸጥ መዋዋልንና ንግግር የለሹን ቋንቋ የመሳሰሉ ጠቃሚ ትምህርቶችን ቀስሟል - ስለ ንግሮችም ጭምር። አንድ ከሰዓት በኋላ የሆነ ሰው ኮረብታው ላይ ተቀምጦ ኮረብታውን ወጥቶ እንዲያ ደክሞት የሚጠጣ ነገር ባለማግኘቱ ነጋዴውን አናገረው።

"ወደ ኮረብታው ለሚወጡ ሰዎች ሻይ እንሸጥላቸው።"

"ምን እዚህ ሰፈር ሁሉም ባለ ሻይ ቤት ነው" አለ ነጋዴው።

"እኛ ግን ሻዩን በክሪስታል ብርጭቆዎች መሸጥ እንችላለን። ሰዎች ሻዩን ይወዱልናል፤ ብርጭቆዎቹንም የመግዛት ፍላጎት ያድርባቸዋል። ውበት ትልቁ የሰዎች አማላይ ኃይል መሆኑን ሰምቻለሁ።"

ነጋዴው አልመለሰለትም ነበር። ሆኖም የዚያኑ ቀን ከሰዓት ጸሎቶቹን ካደረሰና መደብሩን ከዘጋ በኋላ ሁቃህ የሚባለውንና ያንን አረቦቹ ሲጠቀሙበት ያየውን አስገራሚ ፒፓ ሲያጋራው ብላቴናውን ጋበዘው።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ምንድነው የምትሻው?" ጠየቀ ነጋዴው።

"ነግሬሃለሁ እኮ። መልሼ በጎቼን መግዛት እፈልጋለሁ፤ ስለዚህም ገንዘብ ማግኘት አለብኝ።"

ነጋዴው ሁቃሁ ውስጥ አዳዲስ ከሰሎች ጨመረበትና በኃይል ሳበለት።

"በዚህ መደብር ሰላሳ ዓመት በላይ ሰርቻለሁ። መጥፎውን ከጥሩው ክሪስታል መለየት እችላለሁ፤ ስለ ክሪስታል የማላውቀው የለም። ቅርፆቹንም ባህሪያቱንም አውቃቸዋለሁ። ሻይ በክሪስታል ከሸጥን መደብሩ መስፋፋቱ ነው።"

"ታዲያ ይሄ ጥሩ አይደለም?"

"ካለሁበት ሁኔታ ጋር ተላምጃለሁ። አንተ ከመምጣትህ በፊት፣ ወዳጆቼ በኪሣራም ይሁን በብልጽግና ሲለዋወጡ እኔ ግን እዚህ ተመሳሳይ ስፍራ ምን ያህል ጊዜ እንዳሳለፍኩ እያሰብኩ ነበር። አሁን ያን ያህል መጥፎ እንዳልሆነ ገብቶኛል። መደብሩ ሁሌም እንዲሆን በምፈልገው መጠን ነው ያለው። ምንም ነገር መለወጥ አልፈልግም፤ ምክንያቱም ለውጥን እንዴት መቀበል እንደምችል አላውቅም። ኑሮዬን ለምጄዋለሁ።"

ብላቴናው ምን መናገር እንዳለበት አላወቀም። ነጋዴው ቀጠለ፤ "አንተ እውነተኛ በረከቴ ነህ። ዛሬ ከዚህ በፊት ያላየሁትን ነገር ተረዳሁ፦ ችላ የተባለ ቡራኬ እርግማን ይሆናል። በህይወቴ ሌላ ነገር አልፈልግም። አንተ ግን ወደ ብልጽግናና ፈጽሞ ወዳላየኋቸው አድማሳት እንዳይ እያስገደድከኝ ነው። አሁን አየኋቸው፤ አማራጮቼ እንዴት ብዙ እንደሆኑ ተረዳሁ፤ ከመምጣትህ በፊት ከተሰማኝ የከፋ ነገር እየተሰማኝ ነው። ምክንያቱ



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ልፈጽማቸው የሚገቡ ነገሮችንና ሳከናውናቸው ግን አስመፈለጌን ማወቁ ነው።"

ለታሪፋው ዳቦ ጋጋሪ ምንም ከመናገር መቆጠቤ ደግ ነበር ሲል አሰበ ብላቴናው።

ጀንበር መጥለቅ ስትጀምርም ፒፓውን እየተቀባበሉ ማጨስ ቀጥለዋል። የሚያወሩት በአረብኛ ነበር፤ በዚህ ደግሞ ብላቴናው ኩራት ተሰምቶታል። በጎቹ ስለዚህ ዓለም ማንኛውንም ነገር ሊያስተምሩት እንደሚችሉ የሚያምንበት ጊዜ ነበረ። አረብኛ ግን ፈጽሞ ሊያስተምሩት አይችሉም ነበረ።

ነጋዴውን እያሰበ በዚህ ዓለም ላይ በጎቹ ሊያስተምሩኝ የማይችሏቸው ሌሎች ነገሮችም ሳይኖሩ አይቀሩም ብሎ አሰላሰለ። እምን፣ የሚያደርጉት ነገር ቢኖር ምግብና ውሃ መፈለግ ብቻ ነው። ደግሞም እኔ እየተማርኩባቸው እንጂ እነሱ እያስተማሩኝ አልነበሩ ይሆናል።

"መክቱብ" አለ ነጋዴው፣ በመጨረሻ።

"ምን ማለት ነው?"

"ይህን ለመረዳት አረብ ሆነህ መወለድ ነበረብህ" መለሰለት። "ምናልባት በእናንተ ቋንቋ ተጽፏል እንደማለት ይሆናል።"

ሁቃሁ ውስጥ ያለውን ከሰል እየቆሰቆሰ ሻይ በክሪስታል መሸጥ መጀመር እንደሚችል ነገረው። አንዳንዴ ወንዙን መገደቢያ መላ ይጠፋል።

* * *



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ሰዎች ከረብታውን ወጡ፤ ጫፍ ሲደርሱ ደከማቸው። ሆኖም መንፈስ ወስጋ የሚያድስ የሜንታ ሻይ የሚሸጥበት የክሪስታል መደብር ተመለከቱ። በቆንጆ ቆንጆ የክሪስታል ብርጭቆዎች የሚሸጠውን ሻይ ለመጠጣት ወደ መደብሩ ገቡ።

"ሚስቴ እንዲህ ያለውን ነገር ፈጽሞ አስባው አታውቅም" አለና አንደኛው ክሪስታሎችን ገዛ- ያን ለት ማታ ቤቱ የጋበዛቸው እንግዶች በክሪስታሎቹ ይደነቁለታል። ሌላኛው ሰውዬ በክሪስታል ብርጭቆ የቀረበ ሻይ ምንጊዜም ጣፋጭ ነው፤ ምክንያቱም ክሪስታሉ መዓዛውን ያቆየዋል ብሎ ተናገረ። ሶስተኛው ሰው ደግሞ ምትሃታዊ ኃይል አለው ተብሎ ስለሚታመን በምስራቃዊያን ዘንድ ሻይን በክሪስታል ብርጭቆ መጠጣት የተለመደ እንደነበረ ገለጸ።

ብዙም ሳይቆይ ዜናው ተሰራጨ፤ አያሌ ሰዎችም በጥንቱ ንግድ ላይ አዲስ ጣእም የፈጠረውን መደብር ለማየት ወደ ኮረብታው በብዛት ይወጡ ጀመር። ሻይ በክሪስታል ብርጭቆ የሚሸጡ ሌሎችም መደብሮች ተከፍተዋል፤ እነሱ ግን የኮረብታው ጫፍ ላይ አልነበሩም፤ ስለዚህም የረባ ገበያ አልነበራቸውም።

ኋላ ላይ ነጋዴው ሁለት ተጨማሪ ሰራተኞችን ለመቅጠር ተገደደ። ከክሪስታሎቹ ጋር ብዙ ሻይ ቅጠል ማስመጣትም ጀመረ። መደብሩም አዲስ ነገር በተጠሙ ወንዶችና ሴቶች የሚፈለግ ሆነ።

በዚህ ሁኔታም ወራት ተቆጠሩ።

* * *



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ብላቴናው ጎህ ከመቅደዱ በፊት ነቃ። እግሩ የአፍሪካን አፈር ከረገጠ አስራ አንድ ወር ከዘጠኝ ቀናት ሆነው።

ለዚህ ቀን ብሎ የገዛውን ናይለኑን ነጭ የአረብ ልብሱን ለበሰ። ጥምጣሙን በወጉ አደረገና እንዳይፈታበት ከግመል ቆዳ የተሰራውን ቀለበት ከጥምጣሙ በላይ አጠለቀ። ሰንደል ጫማዎቹን ተጫምቶ በጸጥታ ደረጃዎቹን ወረደ።

ከተማዋ ገና እንዳንቀላፋች ናት። ለራሱ ሳንዱዊች አዘጋጀና በክሪስታል ብርጭቆው ትኩስ ሻይ ጠጣ። ከዚያ ፀሐይ ባረፈበት መግቢያ መውጫ ላይ ሁታሁን እያጨሰ ተቀመጠ።

የሚያጨሰው በፀጥታ ነው - ስለምንም ነገር ሳያስብ፣ የበረሃውን ጠረን ተሸክሞ የሚመጣውን ንፋስ እያዳመጠ። አጭሶ ሲጨርስ እጁን ወደ አንደኛው ኪሱ ሰደደ፤ ከኪሱ ስላወጣው ነገር እያሰበ ለጥቂት ሰከንዶች ባለበት ቆየ።

የገንዘብ መአት ነበር። አንድ መቶ ሃያ በጎችና የመመለሻ ትኬት ለመግዛት እና ሸቀጦችን ከአፍሪካ ወደ አገሩ የሚያስገባበት ፈቃድ ለማውጣት የሚበቃ ገንዘብ።

ነጋዴው ነቅቶ መደብሩን እስኪከፍት በትእግስት ጠበቀው። ከዚያ ሁለቱም ሻይ ሊጠጡ ሄዱ።

"ዛሬ መሄዴ ነው" አለ ብላቴናው። "በጎች መግዛት የምችልበት ገንዘብ አለኝ። አንተም መካ ለመሄድ የሚያስፈልግህ ገንዘብ አለህ።" ሽማግሌው ነጋዴ ምንም አላለም።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

“ቡራኬህን ትሰጠኛለህን?” ጠየቀው ብላቴናው። “ረድተኸኛል።” ሰውየው ቃል ሳይተነፍስ ሻዩን ማዘጋጀት ቀጠለ። ከዚያ ወደ ብላቴናው ዞረ።

“እኮራብሃለሁ” አለው። “ክሪስታል መደብሬ ውስጥ አዲስ ስሜት ዘርተሃል። ሆኖም እኔ ወደ መካ እንደማልሄድ ታውቃለህ። ልክ አንተ በጎችህን እንደማትገዛ እንደምታውቀው።”

“ማን ነገረህ?” ጠየቀ ብላቴናው እየተገረመ።

“መክቱብ” አለ ክሪስታል ነጋዴው።

ከዚያም ብላቴናውን መረቀው።

* * *

ብላቴናው ወደ ክፍሉ ገብቶ ንብረቶቹን ሸካከፈ። ሶስት ከረጢት ሞሉ። እየወጣ እያለ በክፍሉ ጥግ ላይ አሮጌዋን የእረኝነት ቦርሳውን አያት። ለረጅም ጊዜ አስታውሷት አያውቅም። ጃኬቱን ለተቸገረ ሰው ለመስጠት አስቦ ከቦርሳው ውስጥ ሲያወጣ ሁለቱ ድንጋዮች ወለሉ ላይ ወደቁ። ዑሪም እና ቱሚም።

አረጋዊውን ንጉስ አስታወሱት፤ ስለ እርሳቸው ካሰበ ረጅም ጊዜያት ማለፉን ሲያስተውል ተደነቀ። ለዓመት ያህል ገንዘብ አጠራቅሞ ወደ ስፔን ስለመመለስ ብቻ እያሰበ ያለመታከት ሲሰራ ነበር።

“ማለምህን አትተው” ብለውት ነበር አዛውንቱ ንጉስ። “ንግሮቹን ተከተል።”



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ብላቴናው ዑሚምና ቴሪምን አነሳቸው፤ አሁንም አረጋዊው ንጉስ አጠገቡ እንዳሉ ተሰማው፡፡ ለዓመት ያህል ለፍቷል፤ ንግሮቹ የሚያሳዩት አሁን የመሄጃው ጊዜ መሆኑን ነው፡፡

"ወደ አገሬ የምመለሰው በፊትም እሰራው የነበረውን ነገር ለመስራት ነው" ሲል አሰበ ብላቴናው "በጎቹ አረብኛ ባያስተምሩኝም፡፡"

ሆኖም በጎቹ ከዚህ ይበልጥ የሚጠቅም ነገር አስተምረውታል፤ ሁሉም ሰው የሚረዳው የዓለም ቋንቋ መኖሩን፣ ብላቴናው መደብሩን ለማሻሻል ይጠቀምበት የነበረውን ቋንቋ፡፡ የመሻትና በፍቅርና በዓላማ የተሳኩ ነገሮች ቋንቋ፣ እንዲሁም ያመኑበትንና የቋመጡለትን ነገር የመፈለግ ሂደት አንድ አካል ነው፡፡ የታንጊየር ባእድ ከተማነት አክትሟል፤ እሷን መያዝ እንደቻለው ሁሉ ዓለምንም መቆጣጠር እንደሚችል ተሰማው፡፡

"አንድ ነገር ስትፈልግ ዓለም ሁሉ ሲያግዝህ ይነሳል" ብለዋል አረጋዊው ንጉስ፡፡

ነገር ግን ንጉሱ ስለመዘረፍ፣ ወይም መጨረሻ ስለሌላቸው በረሃዎች፣ ወይም ህልሞቻቸውን እያወቁ ሊያሳኳቸው ስለማይፈልጉ ሰዎች አልነገሩትም፡፡ ፒራሚዶቹ ተራ የድንጋይ ካቦች መሆናቸውን ወይም ማንም ሰው ጓሮው ሊያቆማቸው መቻሉንም ቢሆን ንጉሱ አልነገሩትም፡፡ ረስቶት ያልጠቀሰውም ነገር አለ፡- በቁጥር ከነበሩህ የሚበልጡ በጎችን የምትገዛበት ገንዘብ ካለህ ልትገዛ ይገባል፡፡

ብላቴናው ቦርሳውን ከጓዙ ጋር ቀላቀለው፡፡ ደረጃውን ሲወርድ ነጋዴው ፀጉረ ልውጥ ጥንዶችን ሲያስተናግድ፣ ሁለት ሌሎች ተጠቃሚዎች በክሪስታል



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ብርጭቆዎች ሻይ እየጠጡ በመደብሩ በኩል ሲያልፉ ተመለከተ፡፡ በዚህ ማለዳ ዛሬ የታየው እንቅስቃሴ ከሌላው ቀን የተለየ ነው፡፡ በቆመበት ስፍራ እያለ የነጋዴው ጸጉር ከአረጋዊው ንጉስ ፀጉር ጋር በጣም እንደሚመሳሰል ለመጀመሪያ ጊዜ አስተዋለ፡፡ ታንጊየር በመጣበት በመጀመሪያው ቀን የሚበላውም የሚጠጋበትም በሌለ ሰዓት ያየውን የከረሜላ ሻጩን ፈገግታ አስታወሰ፤ ያ ፈገግታ ራሱ ከሽማግሌው ፈገግታ ጋር በጣም ይመሳሰላል፡፡

ንጉሱ እዚህ የነበሩና አሻራቸውን ጥለው ያለፉ ይመስላል ብሎ አሰበ፡፡ ነገር ግን ከእነዚህ ሰዎች አንዳቸውም ንጉሱን አግኝተዋቸው አያውቁም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እሳቸው እጣፈንታውን ሲያሳካ የሚሞክረውን ሰው ሁሉ ለመርዳት ሁሌም እንደሚገለጡ ተናግረዋል፡፡

ክሪስታል ነጋዴውን ሳይሰናበት ሄደ፡፡ እዚያ ካሉት ሌሎች ሰዎች ጋር መላቀስ አልፈለገም፡፡ አገሩንና የተማራቸውን መልካም ነገሮች ሁሉ ጥሎ መሄዱ ነው፡፡ ሆኖም የበለጠ በራስ በመተማመን መንፈስ ተሞልቷል፤ ዓለምን መግዛት እንደሚችል ዓይነት ሁሉ ይሰማዋል፡፡

"ነገር ግን ድጋሚ በጎቼን ልንከባከብ ወደማውቃቸው መስኮች መመለሴ ነው፡፡" ይህንን ለራሱ የተናገረው በእርግጠኝነት ነበር፤ ሆኖም በውሳኔው ደስተኛ ሆኖ አልቆም፡፡ ዓመቱን ሙሉ የለፋው ህልሙን እውን ለማድረግ ነበር፤ ያ ህልሙ ግን ከደቂቃ ደቂቃ አስፈላጊነቱ እየቀነሰ እየቀነሰ መጥቷል፡፡ ምናልባት እንግዲህ ያ የእውነት ህልሙ ባይሆን ነው፡፡

ማን ያውቃል... እንደ ክሪስታል ሻጩ መሆን ይሻል ይሆናል፡- "ወደ መካ አለመሄድ፣ ለመሔድ ሲፈልጉ ብቻ መኖር" ብሎ አሰበ ራሱን ለማሳመን እየሞከረ፡፡ ዑሪምና ቱሚምን በእጁ ሲይዛቸው ግን፣ ድንጋዮቹ የአረጋዊውን



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ንጉስ ብርታትና ፈቃድ አስተላለፉበት፡፡ በአጋጣሚ - በልጁ ግምት ንግርም ሊሆን ይችላል - ታንጊየር የመጣ የመጀመሪያው ቀን የገባበት ቡና ቤት ደጃፍ ደረሰ፡፡ ሌባው አልነበረም፤ ባለቤቱ ግን ሻይ አቀረበለት፡፡

"ወደ እረኝነቴ መቼም ቢሆን መመለስ እችላለሁ" ብሎ አሰበ ብላቴናው፡፡ "በጎችን እንዴት መንከባከብ እንዳለብኝ ተምሬያለሁ፤ አሁንም አልረሳሁትም፡፡ ነገር ግን ግብጽ ወዳሉት ፒራሚዶች የምሄድበት እድል ፈጽሞ አላገኝ ይሆናል፡፡ አዛውንቱ የወርቅ የደረት ጥሩር ለብሰዋል፤ ደግሞም የኋላ ታሪኬን ያውቁታል፡፡ እውነትም ንጉስ ነበሩ፤ አዋቂ ንጉስ፡፡"

የአንዳሉዚያ ኮረብታዎች ከዚህ የሁለት ሰዓት መንገድ ብቻ ነው የሚርቁት፤ ሆኖም በእርሱና በፒራሚዶቹ መሐል አንድ ሙሉ በረሃ አለ፡፡ ያለበትን ሁኔታ በሌላም መልኩ ማየት እንዳለበት ተሰማው፡- አሁን ድብቅ ሐብቱን በሁለት ሰዓታት ቀርቦታል፤ ሁለቱ ሰዓታት ወደ ዓመት የመለጠጣቸው እውነት አያሳስብም፡፡

"ወደ በጎቼ ለምን መመለስ እንደፈለግሁ አውቃለሁ" ብሎ አሰበ፡፡ በጎችን አውቃቸዋለሁ፤ ከዚህ በኋላ ችግር አይሆኑብኝም፤ ጥሩ ጓደኞች ይሆኑኛል፡፡ በሌላ ወገን ግን በረሃው ጓደኛ ሊሆነኝ እንደሚችል ወይም ድብቅ ሃብቴን በረሃው ውስጥ መፈለግ እንዳለብኝ አላውቅም፡፡ ካላገኘሁት በማንኛውም ጊዜ ወደ ቤቴ መመለስ እችላለሁ፡፡ በቂ ገንዘብና የምፈልገውን ያህል ጊዜ ኖሮኛል፡፡ ታዲያ ለምን አላደርገውም?

በድንገት በጣም ደስተኝነት ተሰማው፡፡ ምንጊዜም ወደ እረኝነት መመለስ ይችላል፤ ምንጊዜም የክሪስታል ሽያጭ ሰራተኛ መሆን ይችላል፡፡ ምናልባትም ዓለም ሌሎች የተሰወሩ ሃብቶች ሳይኖሯት አይቀርም፤ እሱ



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ግን ህልም አይቷል፤ ከንጉስም ጋር ተገናኝቷል። ይሄ ዝም ብሎ ማንንም ሰው አያጋጥምም!

እያቀደ ነው ከቡና ቤቱ የወጣው። ከክሪስታል ሻጩ አቅራቢዎች አንዱ ክሪስታሎቹን የሚያጓጉዘው በረሃውን ከሚያቋርጡ ሲራራ ነጋዴዎች ጋር መሆኑን አስታወሰ። ዑሪም እና ቱሚምን አሁንም በእጆቹ ያዛቸው፤ በእነርሱ ምክንያት በድጋሚ ወደ ድብቅ ሃብቱ ሊያመራ ነው።

"ሰዎች እጣፈንታቸውን እውን ሊያደርጉ በፈለጉ ጊዜ ሁሉ ከእነሱው ጋር እገኛለሁ" ብለው ሽማግሌው ንጉሥ ነግረውታል።

ወደ ክሪስታል አቅራቢው መጋዘን ሄደ። በእርግጥ ፒራሚዶቹ የተባለሳቸውን ያህል ሩቅ መሆናቸውን ማጣራት ምን ይጎዳል?

* * *

እንግሊዙ በከፊል መጋዘን፣ በከፊል ደግሞ በረት በሆነውና እንስሳ እንስሳ፣ ላብ ላብ እንዲሁም አቧራ አቧራ በሚሸተው ቤት ነገር ውስጥ አግዳሚ ወንበር ላይ ተቀምጧል። የያዘውን ስለኬሚካሎች የሚያወራ መጽሔት እየገላለጠ "መጨረሻዬ እንዲህ ባለ ስፍራ ይሆናል ብዬ አልገመትኩም ነበር" ብሎ አሰበ። "ዩኒቨርሲቲ አስር ዓመት ቆይቼ ዛሬ እዚህ በረት ውስጥ ተገኘሁ።"

ቢሆንም መቀጠል ነበረበት። በንግሮች ያምናል። ህይወቱም ምርምሮቹም ሙሉ በሙሉ የሁለንታን አንድ እውነተኛ ቋንቋ ማግኘትን ዓላማ ያደረጉ ነበሩ። መጀመሪያ ኤስፔራንቶን አጠና፤ ከዚያም የዓለምን ሃይማኖቶች፤



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

አሁን ደግሞ አልኬሚን። ኢስፔራንቶን መናገር ችሏል፤ ሁሉንም ዋና ዋና ሃይማኖቶችም ተረድቷቸዋል፤ ነገር ግን እስካሁን አልኬሚስት አልሆነም። ወሳኝ ከሚባሉ ጥያቄዎች በስተጀርባ ያሉ ሃቆችን ፈልፍሎ አውጥቷል፤ ምርምሮቹ ሁሉ ግን የማይሻገረው ወደሚመስለው ነጥብ ነው ያደረሱት። ከአንድ አልኬሚስት ጋር ግንኙነት ለመፍጠር በከንቱ ሞክሯል። ሆኖም አልኬሚስቶች ያልተለመደ ባህሪይ ያላቸው፣ ስለራሳቸው ብቻ የሚያስቡና ሁልጊዜም ማለት ይቻላል እሱን ለመርዳት የማይፈቅዱ ሰዎች ናቸው። ማን ያውቃል የታላቁን ሥራ የፈላስፋውን ጠጠር ምስጢር ገና ስላላወቁት ይሆናል እውቀታቸውን ማካፈል የማይፈልጉት።

አባቱ ካወረሱት ገንዘብ አብዛኛውን ፍሬ ቢስ ለሆነው የፈላስፋውን ድንጋዮች ፍለጋው አፍስሶታል። እጅግ ብዙ ጊዜውን በዓለም ታላላቅ አብያተ መጻሕፍት አሳልፏል፤ ከገበያ ላይ የጠፉ ጠቃሚ የአልኬሚ መጻሕፍትን ገዝቷል። በአንዱም መጽሐፍ ላይ ከብዙ ዓመታት በፊት አንድ ዝነኛ አረብ አልኬሚስት አውሮጳን ጎብኝቶ እንደነበረ አንብቧል። እድሜው ከሁለት መቶ ዓመት በላይ እንደሆነ እና፤ የፈላስፋውን ድንጋይና ዘላለማዊ ሕይወት የሚሰጠውን ምትሐታዊ ፈሳሽ እንዳገኘ ይነገራል። እንግሊዙ በዚህ ታሪክ በጣም ተማርኳል። ቢሆንም ግን ነገርዬው ከተረት ያለፈ ይሆናል ብሎ አያምንም ነበር፤ በረሃው ውስጥ የአርኪዮሎጂ ምርምር ሲያደርግ ቆይቶ የተመለሰው ጓደኛው በረሃው ውስጥ የተለየ ኃይል የተሰጠው አንድ አረብ መኖሩን ባይነግረው ኖሮ።

"የሚኖረው በአል-ፋዩም ኦሲስ ነው" ብሎታል ጓደኛው። "ሁሉም ሰዎች እሱ ሁለት መቶ ዓመቱ መሆኑንና ማንኛውንም ዓይነት ብረት ወደ ወርቅ እንደሚለውጥ ይነግሩሃል።"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

እንግሊ.ዙ ስሜቱን መደበቅ አልቻለም ነበር። ሁለነገሩን ተወና፣ ወሳኝ ወሳኝ መጻሕፍቱን ሸክፎ እዚህ ተገኘ፤ አባ.ራማና ከፉ ጠረናም መጋዘን ውስጥ። ከውጪ፣ ግዙፍ የሲ.ራራ አጀብ በአል-ፋዩም በኩል ሰሃራ በረሃን ለማቋረጥ እየተዘጋጀ ነበር።

'ያንን እርጉም አልኬሚስት ሳገኘው ነው' ሲል አሰበ እንግሊ.ዙ። የእንስሳቱም ጠረን በጥቂቱም ቢሆን ከፋቱን እየቀነሰ መጣ።

ጓዙ የበዛ ወጣት አረብ ገባና እንግሊ.ዙን ሰላም አለው። "ወዴት ነው የምትሔደው?" ወጣቱ ጠየቀ።

"ወደ በረሃው መሔዶ ነው" መለሰ ሰውየው ወደ ንባቡ እየተመለሰ። በዚህ ጊዜ ምንም አይነት ንግግር ማድረግ አልፈለገም። የሚያስፈልገው ባለፉት ዓመታት ያወቃቸውን ነገሮች መከለስ ነው፤ ምክንያቱም አልኬሚስቱ እንደሚፈትነው እርግጠኛ ነው።

ወጣቱ አረብም መጽሐፍ አውጥቶ ማንበብ ጀመረ። መጽሐፉ በስፓኒሽ ቋንቋ የተጻፈ ነው። "ጥሩ ነው" ብሎ አሰበ እንግሊ.ዙ። ከአረብኛ ይበልጥ ስፓኒሽ ይችላል፤ ይሄ ልጅ ወደ አል-ፋዩም የሚሄድ ከሆነ ደግሞ የሚሰራው ጠቃሚ ጉዳይ በሌለው ሰዓት የሚያዋራው ሰው አገኘ ማለት ነው።

* * *

"የማይታመን ነው" አለ ብላቴናው፣ መጽሐፉ መጀመሪያ ላይ ያለውን የቀብር ሥነ ስርዓት በድጋሚ ለማንበብ እየሞከረ። "ይሄንን መጽሐፍ



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ለማንበብ ስታገል ሁለት ዓመት ሆነኝ፣ ግን እነዚህን ጥቂት የመጀመሪያ ገጾች በፍጹም አልፌያቸው አላውቅም።" ንጉሥ ባያቋርጠውም እንኳን መጽሐፉ ላይ ማተኮር አልቻለም።

አሁንም ውሳኔው ላይ ጥርጣሬ አለው። አንድ ነገር ግን መረዳት ችሏል፡ መወሰን የነገሮች መነሻ ብቻ መሆኑን። አንድ ሰው የሆነ ነገር ለማድረግ ሲወስን ውሳኔውን ለመጀመሪያ ጊዜ በወሰነ ሰዓት ፈጽሞ አልሟቸው ወደማያውቃቸው ስፍራዎች የሚወስደው ውሃ ውስጥ ተወርውሮ እንደገባ ነው የሚቆጠረው።

"ድብቅ ሃብቴን ለማሰስ ስወስን፣ የክሪስታል መገበያያ መደብር ውስጥ እከርማለሁ የሚል ግምት አልነበረኝም" ብሎ አሰበ። አሁንም ይሄንን የሲራራ አጀብ መቀላቀል የእኔ ውሳኔ ይሆን ይሆናል፤ ሲራራዉ የሚሄድበት ሥፍራ ግን ለእኔ ምስጢር ነው።

በአቅራቢያው እንግሊዙ መጽሐፉን ያነባል። ከሰው መቀላቀል የማይፈልግ ዓይነት ነው፤ ደግሞም ብላቴናው ሲገባ ሲያየው የተናደደ ይመስል ነበር። ወደፊት ጓደኞች ሊሆኑም ይችሉ ነበር፤ እንግሊዙ ግን ማውራት እንኳን አይፈልግም።

ልጁ መጽሐፉን ከደነ። እንግሊዙን የሚያስመስለውን ማንኛውንም ነገር ማድረግ እንደማይፈልግ ተሰማው። ዑሪምና ቱሚምን ከቦርሳው አውጥቶ ይጫወትባቸው ጀመር።

ጸጉረ ልውጡ ጮኸ፣ "ዑሪምና ቱሚም!"

ከመቅጽበቱ ዓይን ልጁ ወደ ቦርሳው መለሳቸው።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"አይሸጡም!" አሉ።

"ያን ያህልም አያወጡም" እንግሊዙ መለሰ። "ከአለት ከሚገኝ ክሪስታል ነው የሚሰሩት፤ በዚህ ምድር ላይ ደግሞ እጅግ ብዙ የአለት ክሪስታሎች አሉ። ስለ እንደነዚህ ያሉ ነገሮች የሚያውቁ ሰዎች እነዚህ ዑሪምና ቱሚም መሆናቸውን ሰይተው ያውቋቸዋል። የእነዚህ አካባቢ ሰዎች እነዚህ ድንጋዮች እንዳሏቸው አላውቅም ነበር።"

"ከአንድ ንጉስ በስጦታነት የተሰጡኝ ናቸው" አለ ብላቴናው። ፀጉረ ልውጡ አልመለሰለትም፤ በዚያ ፈንታ ከኪሱ ውስጥ ከብላቴናው ድንጋዮች ጋር የሚመሳሰሉ ሁለት ድንጋዮች አወጣ።

"ንጉስ ነበር ያልከኝ?" ጠየቀው።

"አንድ ንጉስ ከእንደኔ ዓይነት እረኛ ጋር መነጋገሩን ያመንከልኝ አልመሰለኝም" አለው ጭውውታቸውን ለማቋረጥ እየፈለገ።

"በፍጹም! ዓለም ሁሉ ያልተቀበለውን ሰው ንግስና መጀመሪያ የተቀበሉትና ያወጁት'ኮ እረኞች ነበሩ። ስለዚህ ነገስታት ከእረኞች ጋር መነጋገራቸው አያስደንቅም።"

ንግግሩ ብላቴናውን ያልገባው ስለመሰለው ማብራራት ቀጠለ። "መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተጽፏል። ስለ ዑሪምና ቱሚም ያስተማረኝ መጽሐፍ ላይ። እነዚህ ድንጋዮች በእግዚአብሔር የተፈቀዱ ብቸኞቹ ወደፊት የሚመጣውን ነገር ማወቂያ መንገዶች ናቸው። ካህናቱ በወርቃማ የደረት ጥሩራቸው ይይዟቸዋል።"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ልጁ በድንገት እዚህ መጋዘን ውስጥ በመገኘቱ ደስ አለው። "ይሄ ምናልባት ንግር ይሆናል" አለ እንግሊዙ ድምጹን ዝቅ አድርጎ።

"ስለ ንግሮች ማን ነገረህ?" በዚህ ቅጽበት የልጁ ፍላጎት እየጨመረ መጥቷል።

"በህይወታችን የሚያጋጥመን ነገር ሁሉ ንግር ነው" አለ እንግሊዙ ሲያነበው የነበረውን መጽሔት እየዘጋ። "አንድ የሁለንታ ቋንቋ አለ፤ ሁሉም ሰው የሚረዳው፣ ነገር ግን የተረሳ ቋንቋ። እኔ ያንን ቋንቋ በመፈለግ ላይ ነኝ። ለዚህ ነው እዚህ የተገኘሁት። ያንን የሁለንታ ቋንቋ የሚያውቀውን ሰው - አልኬሚስቱን ማግኘት አለብኝ።"

ጭውውታቸው በመጋዘኑ ካቦ ተቋረጠ።

"እናንተ ሁለታችሁ እድለኞች ናችሁ" አለ ወፍራሙ አረብ። "ዛሬ ወደ አል-ፋዩም ለመሔድ የሚነሳ ሲራራ አለ።"

"እኔ ግን ወደ ግብጽ ነው የምሔደው" ልጁ ጣልቃ ገባ።

"አል-ፋዩም ግብጽ ውስጥ ነው ያለው" አለ አረቡ። "አንተ እንዴት ያለኸው አረብ ነህ ባክህ?"

"ይሄ የጥሩ እድል ንግር ነው" አለ እንግሊዙ ወፍራሙ አረብ ከሔደ በኋላ። "ብችል ኖሮ እድል እና አጋጣሚ ስለሚባሉ ቃላት ብቻ አንድ ኢንሳይክሎፒዲያ አዘጋጅ ነበር። በእነዚህ ቃላት ነው የሁለንታ ቋንቋ የተጻፈው።"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ሁሪምና ቱሚም፣ ይዘው መገናኘታቸው ያጋጣሚ ነገር ሆኖ እንዳልሆነ ለብላቴናው ነገረው፡፡ ከዚያም ብላቴናውም አልኬሚስቱን እየፈለገ እንደሆነ ጠየቀው፡፡

"ድብቅ ሃብት እየፈለግሁ ነው" አለና፤ ወዲያውኑ ይህን በመናገሩ ተጸጸተ፡፡ እንግሊዙ ግን ይህንን ከጉዳዩ የጣፈው አይመስልም፡፡

"በአንድ በኩል እኔም እንዳንተው ነኝ" አለ፡፡

"አልኬሚ ምን እንደሆነ እንኳን አላውቅም" እያለ ነበር ብላቴናው፣ የመጋዘኑ ካቦ እንዲወጡ ሲጠራቸው፡፡

* * *

"እኔ የዚህ ሲራራ መሪ ነኝ" አለ ጥቁር ዓይን ያለው ጺማም ሰውዬ፡፡ "ከእኔ ጋር በሚሔደው በእያንዳንዱ ሰው ህይወትና ሞት ላይ ሥልጣን አለኝ፡፡ በረሃዋ አመሏ የማይጨበጥ ሴት ነች፤ አንዳንዴ ሰዎች ታሳብዳለች፡፡"

በሥፍራው ሁለት መቶ የሚሆኑ ሰዎችና አራት መቶ ገደማ እንስሳት - ግመሎች፣ ፈረሶች፣ በቅሎዎችና ለመብል የሚሆኑ አእዋፍ - ተሰባስበዋል፡፡ በአጀቡ ውስጥ ሴቶች፣ ሕፃናት፣ እንዲሁም ሰይፋቸውን ቀበቷቸው ውስጥ የታጠቁ፣ ጠብመንጃዎቻቸውን በትከሻቸው ያነገቱ አያሌ ወንዶች አሉ፡፡ እንግሊዙ በመጻሕፍት የተሞሉ ብዙ ሻንጣዎች ይዟል፡፡ ጫጫታ ከመብዛቱ የተነሳ መሪው የሚናገረውን ነገር ብዙ ጊዜ መደጋገም ነበረበት፡፡

"እዚህ መሐል በርካታ የተለያዩ ሰዎች አሉ፣ ሁላቸውም የየራሳቸው አምላክ አላቸው፡፡ እኔ የማገለግለው አምላክ ግን አላህ ብቻ ነው፡፡ ከበረሃው በሰላም



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

እንወጣ ዘንድ የምችለውን ሁሉ ለማድረግም በአላህ ስም እምላለሁ። ነገር ግን በረሃው ውስጥ ምንም ቢያጋጥመን የእኔን ትእዛዝ እንደምትቀበሉ በየምታምኑበት አምላክ ስም እንድትምሉልኝ እፈልጋለሁ። በረሃ ውስጥ አለመታዘዝ ሞት ነው።"

አጀቡ ውስጥ ጉርምርምታ ተሰማ። እያንዳንዱ ሰው በየእግዜሩ ስም በእርጋታ እየማለ ነው። ብላቴናው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ማለ። እንግሊዙ ምንም አላለም። ጉርምርምታው ከቀላል ቃለ መሃላ የረዘመ ሆነ። ሰዎቹ ጠብቀን እያሉ ወደ ሰማይ እየጸለዩ ነበር።

ጡሩምባ ሲነፋ ሁሉም ሰዎች መጓጓዣዎቹ እንስሳት ላይ ወጡ። ብላቴናውና እንግሊዙ የገዟቸው ግመሎች ላይ ተቀመጡ። ብላቴናው ሸክም ለበዛበት የእንግሊዙ ግመል አዘነለት።

"አጋጣሚ የሚባል ነገር የለም" አለ እንግሊዙ መጋዘኑ ውስጥ የጀመሩትን ወሬ ካቆሙበት እየቀጠለ። "እዚህ የመጣሁት ጓደኛዬ ስለ አንድ አረብ ሰምቶ..."

ሲራራው ጉዞ በመጀመሩ እንግሊዙ የሚናገረውን መስማት አልሆነለትም። እንግሊዙ ስለምን ሊያስረዳው እንደፈለገ ግን ብላቴናው ገብቶታል፡- አንድን ነገር ከሌላው ጋር ስለሚያስተሳስረው ምስጢራዊ ሰንሰለት፤ እራሱንም እረኛ ያደረገው፣ ደጋግሞ አንድ ህልም ያሳየው፣ ንጉሥ ለማግኘት፣ ለመዘረፍና፣ ከክሪስታል ነጋዴው ጋር ለመገናኘት ለአፍሪካ ወደቀረበች ከተማ ያመጣው... ይኸው ሰንሰለት ነው።

ሰው እጣፈንታውን እውን ለማድረግ በተቃረበ መጠን እጣፈንታው እውነተኛ የመኖሪያ ዓላማው እየሆነ ይመጣል ብሎ አሰበ - ብላቴናው።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ሲራራው ወደ ምሥራቅ ተንቀሳቀሰ። ጠዋት ጠዋት እየተጓዘ፣ ጸሐይዋ ስትከር ያርፍና መሸትሸት ሲል እንደገና ጉዞውን ይቀጥላል። ብላቴናው አብዛኛውን ጊዜ ከመጻህፍቱ ጋር ከሚያሳልፈው ከእንግሊዙ ጋር ያወራው ለጥቂት ጊዜ ብቻ ነው።

ብላቴናው በዝምታ የሰዎቹንና የእንስሳቱን የበረሃ ጉዞ አስተዋለ። አሁን ሁሉም ነገር ሰጉዞ የተነሱ እለት ከነበረበት በጣም ተለይቷል፦ ያኔ ግራ መጋባትና ጩኸት፣ የህፃናት ለቅሶና የእንስሳቱ ጩኸት፣ ካልተረጋጉት የመሪዎቹና የሲራራ ነጋዴዎቹ ትእዛዞች ጋር ተደበላለቆ ነበር።

በረሃው ውስጥ ግን ያለው የነፋሱና የእንስሳቱ ኮቴዎች ድምጽ ብቻ ነው። መሪዎቹ እንኳን እርስ በርሳቸው ብዙ ጊዜ አይነጋገሩም።

"ይህን አሸዋ ምድር ብዙ ጊዜ አቋርጬዋለሁ" አለ አንድ ምሽት ከግመል ነጂዎቹ አንዱ። "ግና በረሃው ግዙፍ አድማሳቱም ሩቅ በመሆናቸው ሰውን ትንሽነትና ጸጥ የማለት ግዴታ እንዳለበት እንዲሰማው ያደርጉታል።"

ብላቴናው ይህን በረሃ ከዚህ ቀደም በእግሮቹ ረግጦት ባያውቅም ሰውየው የተናገረውን ነገር ተረዳው። እሱ ራሱ ባህር ወይም እሳት ባየ ቁጥር በተፈጥሯዊ ሃይላቸው ተደምሞ በዝምታ ይዋጣል።

"ነገሮችን ከበጎቹ ተምሬያለሁ፤ ከክሪስታልም ተምሬያለሁ" ብሎ አሰበ። ከበረሃውም የሆነ ነገር መማር እችላለሁ። አንጋፋና አዋቂ ይመስላል።

ነፋሱ አልቆመም፤ በታሪፋ ምሽግ ተቀምጦ ይኸው ነፋስ ፊቱ ላይ ሲነፍስበት የነበረውን ቀን አስታወሰ። የበጎቹን ፀጉር አስታወሰው...



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

እንደወትሯቸው አሁንም በአንዳሉዚያ መስኮች ምግብና ውሃ እየፈለጉ ያሉትን በጎቹንም።

"አሁንማ የእኔ በጎች መሆናቸው ቀርቷል" አለ ለራሱ፣ ናፍቆት ውል ሳይለው። "እስካሁን ከአዲሱ እረኛቸው ጋር መላመድ አለባቸው፤ እኔንም ረስተውኝ ይሆናል። ይሄ መልካም ነው። እንደበጎች ያሉ ጉዞ የለመዱ ፍጡራን ጉዟቸውን ስለመቀጠል ያውቃሉ።"

ስለ ነጋዴው ሴት ልጅ እና እስካሁን ሳትዳር ስላለመቅረቷም አሰበ። ምናልባትም ለዳቦ ጋጋሪ ወይም ማንበብና አስደሳች ታሪኮች ሲያወራላት ለሚችል ሌላ እረኛ ተድራ ይሆናል - ለነገሩ እሱ ብቸኛው ላይሆን ይችላል። ሆኖም የግመል ነጂውን አስተያየት መረዳት በመቻሉ ተደስቷል፦ ምናልባትም የሰውን ሁላ የኋላና ያሁን ታሪክ የሚመለከተውን ሁለንታዊ ቋንቋም እየተማረም ይሆናል። ብላቴናው፣ ደመነፍሳዊው መረዳት የነፍስ የሁሉም ሰው ታሪኮች ወደ ተሳሰሩበት የሁለንታ የህይወት ጅረት ውስጥ ድንገት መጥለቅና፣ ሁሉም ነገር እዚያ ተጽፏልና ሁሉንም ነገር ማወቅ መቻል መሆኑን መገንዘብ እየጀመረ ነው።

"መክቱብ" አለ ብላቴናው፣ ክሪስታል ሻጩን እያስታወሰ። በረሃው አንዴ አሸዋማ ከዚያም አለትማ ይሆናል። ሲራራው ግዙፍ ድቡልቡል አለት መንገድ ሲዘጋበት አለቱን ለመዞር ይገደዳል፤ አለታማነቱ የከፋ መንገድ ሲገጥመው ደግሞ መንገድ ይቀይራል። አሸዋው ልም ሆኖ እንስሳቱን አላራምድ የሚላቸው ሲሆን ሻል ያለ አሸዋ ወዳለበት አቅጣጫ ያመራል። በአንዳንዱ ሥፍራ ከደረቁ ሃይቆች የተነሳ በጨው የተሸፈኑ መሬቶች ያጋጥማሉ። እንሰሳቱ እንዲህ ያሉ ሥፍራዎች ሲደርሱ ግመል ነጂዎቹ ከግመሎቹ ላይ ወርደው የእንሰሳቱን ሸክም ያቀሉላቸዋል። ነጂዎቹ ያን



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

አስቸጋሪ ሥፍራ እስኪያልፉ ድረስ ጭነቶቹን ራሳቸው ተሸክመው ይጓዙና የተሻለ መንገድ ሲደርሱ መልሰው ግመሎቹን ይጭኗቸዋል፡፡ አንድ የሲራራ መሪ ቢታመም ወይም ቢሞት፣ ግመል ነጂዎቹ እጣ ይጥሉና አንድ አዲስ ሰው ይሾማሉ፡፡

ይሄ ሁሉ የሚሆነው ግን በአንድ መሰረታዊ ምክንያት ነው፡- ምንም ያህል መንገዶች ቢለዋወጡ ወይም የጉዞ ማስተካከያዎች ቢደረጉ እንኳን ሲራራ አጀቡ ያንኑ የተነሳበትን አቅጣጫ አይስትም፡፡ እንቅፋቶቹን ካለፈ በኋላ የለምጌውን አቅጣጫ በምትጠቁመው ኮከብ እየተከተለ ወደ መስመሩ ይገባል፡፡ ሰዎች በማለዳው ሰማይ ላይ ያቺ ኮከብ ስታበራ ሲያዩ ውሃ፣ የወይራ ዛፎች፣ መጠለያና ሌሎች ሰዎችን በሚያገኙበት ትክክለኛ አቅጣጫ ላይ መሆናቸውን ይረዳሉ፡፡ እንግሊዙ ብቻ ነው ይህን ሁሉ የማያስታውሰው፤ ምክንያቱም አብዛኛውን ጉዞውን መጻሕፍቱን ተመስጦ በማንበብ ነበር ያሳለፈው፡፡

ብላቴናውም መጽሐፍ ይዟል፤ በጉዞው የመጀመሪያ ቀናትም ሊያነብሞክሮ ነበር፡፡ በኋላ ግን ሲራራውን መመልከትና ነፋሱን ማዳመጥ የበለጠ አስደሳች እንደሆነ ገባው፡፡ የራሱን ግመል ይበልጥ እንደተረዳውና ከእሱ ጋር ወዳጅነት መፍጠር መቻሉ እንደገባው መጽሐፉን ጨርሶ ተወው፡፡ ብላቴናው ምንም እንኳን መጽሐፉን በገለጠ ቁጥር የሆነ ጠቃሚ ነገር እንደሚማር እያመነ ቢመጣም አሁን ግን አላስፈላጊ ሸክም ሆነበት፡፡

ከጎን ጎኑ ከሚጓዘው ግመል ነጂ ጋር ተወዳጁ፡፡ ማታ ማታ በእሳቱ ዙሪያ ይቀመጡና ብላቴናው ስለእረኝነት ጀብዱዎቹ ያወራለታል፡፡

ከእነዚህ ጨዋታዎቻቸው በአንዱ ነጂው የራሱን ታሪክ ነገረው፡፡



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"በኤል ካይሩም አቅራቢያ ነበር የምኖረው" አለው። "የማርስባት መሬት፣ ልጆችና እስክሞት ድረስ የማይለወጥ ኑሮ ነበረኝ። ምርቱ ከመቼውም ጊዜ የተሻለ በሆነበት አንድ ዓመት ሁላችንም ወደ መካ ተጓዝን፤ እኔም በህይወቴ ሳላሟላው የኖርኩትን ብቸኛ ግዴታዬን አሳካሁ። ከዚህ በኋላ ሞቴ እረፍቴ ነው፤ ያ ደግሞ ደስ አሰኘኝ።

"አንድ ቀን መሬት መናወጥ ጀመረች፤ አባይም አካባቢውን አጥለቀለቀው። እንዲህ ያለው ነገር ሌሎች ላይ እንጂ እኔ ላይ የሚደርስ አይመስለኝም ነበር። ጎረቤቶቼ ላይ እንጂ እኔ ላይ የሚደርስ አይመስለኝም ነበር። ጎረቤቶቼ የቴምር ዛፎቻቸውን በጎርፍ ምክንያት እንዳያጡ ሰጉ፣ ሚስቴ ደግሞ ጎርፉ ልጆቻችንን እንዳያሳጣን ፈራች። የእኔ የሆነው ነገር ሁሉ እንደሚጠፋ አሰብኩ።

"መሬቱ ተበላሽቷልና ገቢ የማገኝበት ሌላ ዘዴ ማግኘት ነበረብኝ። እናም ይኸው ግመል ነጂ ሆንኩ። ያ አደጋ ግን የአላህን ቃል አስተምሮኝ አለፈ:- ሰዎች የሚያስፈልጋቸውንና የሚፈልጉትን ማግኘት እስከቻሉ ድረስ የማያውቁትን ነገር መፍራት የለባቸውም።

"ያለንን እንዳናጣ እንሰጋለን። ይሄ ፍርሃት ግን የእኛ የህይወት ታሪክና የዓለም ታሪክ በአንድ እጅ መጻፉን ስንረዳ ይተንናል።"

አንዳንዴ የእነሱ ሲራራ ከሌላ ሲራራ ጋር ይገናኛል። ሁሌም አንዳቸው ለሌላቸው የሚያስፈልግ የሆነ ነገር ይኖራቸዋል - ልክ ሁሉም ነገር በእርግጥም በአንድ እጅ እንደተጻፈ ሁሉ። በእሳቱ ዙሪያ እንደተቀመጡ ግመል ነጂዎቹ ስለ አውሎነፋሶች መረጃ ይለዋወጣሉ፤ ስለበረሃውም ያወራሉ።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

አንዳንዶ ደግሞ የተለዩ፣ ከአይኖቻቸው በቀር ምናቸውም የማይታይ ሰዎች ያጋጥሟቸዋል፤ መንገድ የሚቃኙት ቤድዊኖች ናቸው። ስለሌቦችና ስለ አረመኔ ጎሳዎች ማስጠንቀቂያዎችን ይሰጣሉ። እነኚህ ጥቁር ለባሾች በጸጥታ መጥተው በመጡበት ጸጥታ ይመለሳሉ። አንድ ምሽት የሆነ ግመል ነጂ ብላቴናውና እንግሊዙ ወደሚሞቁት እሳት መጥቶ፤ "የጎሳ ጦርነቶች ሊቀሰቀሱ ነው እየተባለ ነው" ሲል ነገራቸው።

ሶስቱም በጸጥታ ተዋጡ። ማናቸውም ምንም ባይናገሩም አየሩ ላይ የፍርሃት ስሜት እንደረበበ ብላቴናው ተገነዘበ። አሁንም በቃል አልባው … የሁለንታ ቋንቋ እየተጠቀመ ነው።

እንግሊዙ አደጋ ላይ ስለመሆን አለመሆናቸው ጠየቀ።
"በረሃው ውስጥ ከገባህ ወዲያ መመለሻ የለህም" አለ ግመል ነጂው። "መመለስ ካልቻልክ ደግሞ መጨነቅ ያለብህ ወደፊት መጓዝ ስለምትችልበት የተሻለ ዘዴ ብቻ ነው። ቀሪው፣ አደጋውን ጨምሮ፣ የአላህ ጉዳይ ነው።"
ከዚያም ምስጢራዊውን ቃል በመናገር ደመደመ:- "መክቱብ።"
"ሲራራው ላይ ብታተኩር ይሻላል፣" አለው ብላቴናው፣ ግመል ነጂው ከሄደ በኋላ። "አያሌ ተለዋጭ መንገዶችን ተጠቅመናል፤ ሁሌም ግን ወደ አንድ መድረሻ እያመራን ነው።"

"አንተ ደግሞ ስለ ዓለም ብዙ ማንበብ አለብህ" መለሰለት እንግሊዙ። "በዚህ ረገድ መጻሕፍትም እንደሲራራ አጀብ ናቸው።"

ግዙፉ የሰዎችና የእንስሳት ስብስብ በፍጥነት መጓዝ ጀመረ። የቀኑ ጉዞ ሁሌም ጸጥታ የሰፈነበት ነበር፤ አሁን ግን ማታ ማታ በእሳት ዙሪያ የሚደረገውም ጭውውት ቆሟል። እንዲያውም አንድ ቀን የሲራራው መሪ



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ወደ ሲራራው ትኩረት ላለመሳብ በሚል የማታ ማታ አሳት ማብራት እንዲቆም ወሰነ።

ተጓገሮቹ ማታ ማታ በእንስሳቱ አማካይነት ክብ ሰርቶ መሐሉ ላይ ተሰባስቦ መተኛትንና የማታ ማታውን ብርድ መከላከልን ለመዱት። መሪውም የታጠቁ ወታደሮችን ዋርድያ አሰማራ።

አንድ ሌሊት እንግሊዙ መተኛት አቃተው። ብላቴናውን ጠራውና በሰፈሩ ዙሪያ ወዳሉት የአሸዋ ጋሪዎች አመሩ። ጨረቃዋ ሙሉ ነበረች፤ ብላቴናው የህይወቱን ታሪክ ለእንግሊዙ ነገረው። ብላቴናው እዚያ መስራት በመጀመሩ ክሪስታል መሸጫው ውስጥ የታየው ለውጥ እንግሊዙን ደነቀው።

"ያ ሁሉን ነገር የሚገዛ መርህ ነው" አለ። "በአልኬሚ የሁለንታ ነፍስ ይባላል። የሆነ ነገር በሙሉ ልብህ ስትሻ፣ ከሁለንታ ነፍስ ጋር በጣም የቀረብክ ትሆናለህ። ሁሌም አወንታዊ ኃይል ነው።"

ይሄ የሰው ልጅ ብቻ ስጦታ አለመሆኑና፣ በምድር ላይ ያለ ነገር ሁሉ ማእድኑም፣ አትክልቱም፣ እንስሳውም ወይም ደግሞ ቀላሉ ሃሳብ ሳይቀር ነፍስ አላቸው።

"በምድር ያለው ነገር ሁሉ ያለማቋረጥ በገቢረ ውላጤ ያልፋል፤ ምክንያቱም ምድር ህያው ናት... ስለዚህም ነፍስ አላት። እኛ የዚያ ነፍስ ክፋዮች ስለሆንን ነው ለኛ እንደሚሰራ ብዙ ጊዜ የማናስተውለው። በክሪስታሉ መደብር ውስጥ ግን ብርጭቆዎቹ ሳይቀሩ ላንተ ስኬት እየተባበሩህ እንደነበር ልብ ሳትል አትቀርም።"

ብላቴናው ጨረቃዋንና የነጣ የገረጣውን አሸዋ እየተመለከተ ስለዚህ ነገር ጥቂት አሰላሰለ። "ሲራራው በረሃውን ሲያቋርጥ ተመልክቼዋለሁ" አለ።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ሲራራውና በረሃው አንድ ቋንቋ ይናገራሉ፤ በዚህም ምክንያት በረሃው ማቋረጡን ፈቀደ። የሲራራውን እያንዳንዱን እርምጃ በጊዜው መከናወኑን ሊፈትነው ነው፤ በጊዜ ከተከናወነ ወደ ኦሲሱ እንደርሳለን።"

"ከመካከላችን አንደኛችን ይህንን ሲራራ የተቀላቀልነው ከግል ድፍረታችን የተነሳ ብቻ እንጂ ያንን ቋንቋ ሳንረዳ ቢሆን ኖሮ ይሄ ጉዞ ከዚህ እጅግ የባሰ አስቸጋሪ ጉዞ በሆነ ነበር።"

ጨረቃዋን እየተመለከቱ ባሉበት ቆሙ።

"ይሄ የንግሮች ምትሀት ነው" አለ ብላቴናው፣ "መሪዎቹ የበረሃውን ትእምርቶች እንዴት እንደሚያነቡ፣ እንዴትም የሲራራው ነፍስ ከበረሃው ነፍስ ጋር እንደሚነጋገሩ አይቻለሁ።"

እንግሊዙም አለ፡- "ለሲራራው ትኩረት መስጠት ነበረብኝ።"

"እኔ ደግሞ ለመጻሕፍትህ ትኩረት መስጠት ነበረብኝ" አለ ብላቴናው በበኩሉ።

* * *

የተለዩ መጻሕፍት ናቸው። ስለ ሜርኩሪ፣ ስለ ጨው፣ ስለ ድራጎኖችና ስለነገሥታት ያወራሉ፤ እሱ ደግሞ ከእነዚህ አንዳቸውም አልገቡትም። ሆኖም በሁሉም መጻሕፍት የሚደጋገም አንድ ሃሳብ ያለ መሰለው፡- ሁሉም ነገሮች የአንድ ነገር ብቻ መከሰቻዎች ናቸው።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ከመጻሕፍቱ በአንዱ በአልኬሚ ጽሑፎች ውስጥ በጣም ጠቃሚውና አስፈላጊው ምንባብ በጥቂት መስመሮች ብቻ የተጻፈውና በኤመራልድ ላይ የተቀረጸው ምንባብ ነው።

"የኤመራልድ ጽላት ነው" አለ እንግሊዙ፣ ይህን ብላቴና የሆነ ነገር ማስተማር በመቻሉ ኩራት እየተሰማው።

"ታዲያ እነዚህ ሁሉ መጻሕፍት ለምን ያስፈልጉናል?" ብላቴናው ጠየቀ።

"እነዚያን ጥቂት መስመሮች መረዳት እንድንችል" መለሰ እንግሊዙ የተናገረውን ከልቡ የሚያምንበት ባይመስልም።

ብላቴናው ከሁሉ ይበልጥ የማረከው መጽሐፍ የዝነኛ አልኬሚስቶችን ታሪኮች የሚናገረው ነው። አልኬሚስቶቹ ሙሉ ህይወታቸውን በአቢያተ ሙከራቸው ብረቶችን ለማንጻት ተግባር የሰጡ ነበሩ፤ አንድ ብረት ለብዙ አመት ከቀለጠ ከግል ባህርያቱ ሁሉ ይወጣና የሚቀረው ነገር የሁለንታ ነፍስ ይሆናል ብለው ያምኑ ነበር። የሁለንታ ነፍስ በገጸ ምድር ላይ ያለውን ነገር ሁሉ እንዲረዱ ፈቅዶላቸዋል፤ ምክንያቱም ተግባቦት ሁሉ የሚከወንበት ቋንቋ እርሱው ነውና። ይህን ግኝት ዓቢይ ስራ ብለው ይጠሩታል - እርሱም ከፊል ፈሳሽ፣ ከፊል ጠጣር ነው።

"ቋንቋውን ለመረዳት ለመረዳትማ፣ ሰዎችንና ንግሮችን መመልከት አይበቃም?" ጠየቀ ብላቴናው።

"አንተ ደግሞ ሁሉንም ነገር የማቅለል አባዜ አለብህ" አለ እንግሊዙ በንዴት። "አልኬሚ ቀልድ አይደለም። እያንዳንዱን ሙያውን የተካኑ አልኬሚስቶች ያለፉበትን ደረጃ መከተል ያስፈልጋል።"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

በዓቢዩ ሥራ ፈሳሹ ክፍል እድሜ ቀጥል ማየ ህይወት እንደሚባልና ከሁሉም አይነት በሽታ እንደሚፈውስ አወቀ፤ አልኬሚስቱንም እንዳያረጅ ይረዳዋል። ጠጣሩ ክፍል ደግሞ የፈላስፋው ጠጠር ይባላል።

"የፈላስፋውን ጠጠር ማግኘት ቀላል አይደለም" አለ እንግሊዙ። "አልኬሚስቶቹ ብረቱን የሚያነጻቸውን እሳት እየተመለከቱ ብዙ ዓመታት አቢያተ ሙከራቸው ውስጥ ያሳልፋሉ። እሳቱን ተጠግተው ብዙ ሲቆዩ የዓለምን ከንቱ ነገር ሁሉ ይተዋሉ ማለት ነው። የብረቶቹ መንጻት ወደ እነሱ ወደ ራሳቸውም መንጻት እንደሚመራቸው አውቀዋል።"

ብላቴናው ስለ ክሪስታል ሻጩ አሰላሰለ። ብላቴናው ከእሱ ታዊ እሳቤዎች ይጸዳ ዘንድ ክሪስታሎቹን ቢያጸዳቸው መልካም እንደሆነ ነግሮት ነበር። ብላቴናው አልኬሚ በአንድ ሰው የእለት ተእለት ህይወት ውስጥ ሊማሩት የሚቻል መሆኑን ይበልጥ እያመነ መጥቷል።

"ደግሞም" አለ እንግሊዙ፣ "የፈላስፋው ጠጠር አስገራሚ ባህርይ አለው። የጠጠሩ ትንሽዬ ብር ማእድን በጣም ብዙ ብረቶችን ወደ ወርቅ መለወጥ ትችላለች።"

ብላቴናው ይህን ሲሰማ በአልኬሚ ይበልጥ እየተሳበ መጣ። በትንሽ ትእግስት ሁሉንም ነገር ወደ ወርቅ መለወጥ እንደሚችል አሰበ። በዚህ ረገድ የተሳካላቸውን የብዙ ሰዎችን ታሪክ አንብቧል፦ ሄልቬሺያስ፣ ኤሊያስ፣ ፉልካኔሊ እና ገበር። አስደሳች ታሪኮች ነበሩ፦ ሁላቸውም እጣፈንታቸውን እስከመጨረሻው ኖረውታል። ተጉዘዋል፤ ከጠቢባን ጋር ተነጋግረዋል፤ ተአምራትን ሰርተዋል፤ የፈላስፋውን ጠጠርና የእድሜ ቀጥል ማየ ህይወት ባለቤትም ሆነዋል።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ነገር ግን ዓቢዩን ሥራ ለመረዳት በፊለገ ጊዜ ብላቴናው ሙሉ በሙሉ ግራ ተጋባ። መስመሮች፣ በምስጢር ቋንቋ የተጻፉ መመሪያዎችና የተሰወሩ ጽሑፎች ብቻ ነበሩ።

*  *  *

"ለምን ነገር ያወሳስባሉ?" አንድ ምሽት እንግሊዙን ጠየቀው። እንግሊዙ በሆነው ባልሆነው እንደሚበሳጭና መጻሕፍቱም እንደናፈቁት ብላቴናው ልብ ብሏል።

"የመረዳት ኃላፊነት ያለባቸው እንዲረዱት ታስቦ" አለው። "እስኪ ሁሉም ሰው እየተነሳ ብረት ወደ ወርቅ ሲለውጥ ይታይህ። ወርቅ ዋጋውን ያጣ ነበር።

"ነገሮችን በጥልቀት ለማጥናት ጽናትና ፈቃደኝነት ያላቸው ብቻ ናቸው ዓቢዩን ሥራ መረዳት የሚችሉት። ምስጢሮቹን የሚፈታልኝ እውነተኛ አልኬሚስት እየፈለግሁ ነው።"

"እነዚህ መጻሕፍት መቼ ነበር የተጻፉት?" ጠየቀ ብላቴናው።

"ከብዙ መቶ አመታት በፊት"

"ያኔማ ማተሚያ ቤቶቹ አልነበሩም" ብላቴናው ሞገተ።

"ሰዎች ስለ አልኬሚ የሚያውቁበት ምንም ዘዴ አልነበረም። ይህንን በብዙ ምስሎች የተሞላ የማይገባ ቋንቋ ለምን ተጠቀሙ?"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

እንግሊዙ በቀጥታ መልስ አልሰጠውም፡፡ ባለፉት ሶስት ቀናት ሲራራውን በትኩረት እያስተዋለ የነበረ ቢሆንም ምንም አዲስ ነገር እንዳላወቀ ተናገረ፡፡ ያስተዋለው ብቸኛ ነገር ቢኖር የጦርነቱ ወሬ በየጊዜው እየጨመረ መምጣቱን ነው፡፡

* * *

አንድ ቀን ብላቴናው መጻሕፍቱን ለእንግሊዙ መለሰለት፡፡ "ምን ተማርክ?" ብሎ ጠየቀው የመልሱን ምንነት ለመስማት የጓጓው እንግሊዝ፡፡ ጦርነት ሊያጋጥማቸው የመቻሉን ሃሳብ ለመርሳት የሆነ ሰው እንዲያዋራው ይፈልጋል፡፡

"ዓለም ነፍስ እንዳላት፣ ያን ነፍስ የተረዳ ሁሉ የነገሮችን ቋንቋ መረዳት እንደሚችል ተምሬያለሁ፡፡ ብዙ አልኬሚስቶች እጣፈንታቸውን እውን ስለማድረጋቸውና በመጨረሻም የዓለምን ነፍስ፣ የፈላስፋውን ጠጠር፣ እንዲሁም እድሜ ቀጥሉን ማየ ሕይወት ስለማግኘታቸው አውቂያለሁ፡፡

"ከሁሉም በላይ ግን እነዚህ ነገሮች በሙሉ ቀላል እንደሆኑና በኤመራልድ ላይ ሊጻፉ እንደሚችሉ ተምሬያለሁ፡፡"

እንግሊዙ ተበሳጨ፡፡ በምርምር ያሳለፋቸው ዓመታት፣ ምትሃታዊዎቹ ትእምርቶች፣ እንግዳዎቹ ቃላትና የቤተሙከራ እቃዎች... አንዳቸውም የብላቴናውን ቀልብ አልሳቡም፡፡ ነፍሱ ምናልባትም ይሄን ለመረዳት ገና አልሰለጠነች ይሆናል ብሎ አሰበ፡፡

መጻሕፍቱን ተቀብሎ በየቦርሳዎቻቸው አስገባቸው፡፡ "ሲራራውን ወደመመልከትህ ተመለስ" አለው፡፡ "እሱም እኔን ምንም አላስተማረኝም፡፡"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ብላቴናው በበረሃው ጸጥታና በእንስሳቱ በሚነሳው አሸዋ ላይ ወደ መመሰጥ ተመለሰ። "ሁሉም ሰው ትምህርት የሚቀስምበት የየራሱ መንገድ አለው" አለ ለራሱ። "የእሱ መንገድ ከእኔ ጋር አይመሳሰልም፤ የእኔም የእሱን አይመስልም። ሆኖም ሁለታችንም አጣፈንታዎቻችንን እያሰስን ነው፤ በዚህ ምክንያት አከብረዋለሁ።"

* * *

ሲራራው ሌትና ቀን መጓዝ ጀመረ። የተሸፋፈኑት ቤድዊኖች በጣም በተደጋጋሚ ይከሰቱም ነበር። የብላቴናው ጥሩ ጓደኛ የሆነው ግመል ነጂ በጎሳዎቹ መካከል እንዳይነሳ የተሰጋው ጦርነት መጀመሩን ገለጸ። ሲራራው ወደ ኦሲሱ ከደረሰ እድለኛ ነው።

እንስሶቹ ደክመዋል፤ ሰዎቹም እርስ በርስ ማውራታቸውን ቀንሰዋል። ጸጥታው በተለይ የሌሊቱ አስፈሪ ገጽታ ሆኗል፤ በፊት ከግመል ጩኸትነቱ የተለየ ነገር ያልነበረው ድምጽ አሁን ወራሪዎችን እንዳይጠራ ተሰግቶበታል።

"በህይወት አለሁ" አለው ብላቴናውን፣ በአንድ እሳት ባልተያያዘበት፣ ጨረቃም ባልወጣችበት ምሽት እንደ እንጀራ የሚዘወተረውን የበረሃ ቴምር እየበሉ። "ስበላ የማስበው ቴምሩን ብቻ ነው። ሰልፍ ላይ ስሆን፣ ሰልፉ ላይ ብቻ አተኩራለሁ፤ መዋጋት ካለብኝ ደግሞ ያ ቀን ለመሞት የሌላውን ቀን ያህል ጥሩ ነው።

"ምክንያቱም ያለፈውን ወይም የወደፊቱን ህይወቴን አልኖርም። አሁን ብቻ ነው የሚያስደስተኝ። ምን ጊዜም በአሁን ላይ ማተኮር ከቻልክ ደስተኛ ሰው ትሆናለህ። በረሃው ውስጥ ህይወት መኖሩን፣ ከዋክብት በሰማየ ሰማያት



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

መኖራቸውን፣ የጎሳዎቹ አባላት የሚዋጉት የሰው ዘር አካላት በመሆናቸው እንደሆነ ትረዳለህ። ህይወት ላንተ የጭፈራ ድግስ፣ ቃላት በዓልም ትሆንልሃለች፤ ምክንያቱም ህይወት አሁን እየኖርናት ያለችው ቅጽበት ናት።"

ከሁለት ምሽቶች በኋላ ብላቴናው ለመተኛት እየተዘጋጀ እያለ በየምሽቱ የሚከተሏትን ኮከብ ፈለጋት። አድማሱ ከወትሮው ዝቅ እንዳለ አሰበ፤ ምክንያቱም ከዋክብቱን ራሱ በረሃው ላይ ያያቸው መስሎታል።

"እሲሱ ነው" አለ ግመል ነጂው።

"ከሆነ ታዲያ ለምን አሁን ወደ እሱ አንሄድም?" ብላቴናው ጠየቀ።

"ምክንያቱም መተኛት አለብን።"

ብላቴናው ጸሐይ እንደወጣች ከእንቅልፉ ነቃ። ከፊት ለፊቱ፣ ማታ ትናንሽ ከዋክት በነበሩበት ስፍራ የቴምር ዛፎች በረሃውን ሞልተው በመደዳ ተሰልፈዋል።

ብላቴናው ግን ጸጥ ብሏል። የበረሃውን ጸጥታ ተላምዶታል፤ ዛፎቹን በማየት ተመስጧል። ወደ ፒራሚዶቹ ለመድረስ ገና ብዙ መንገድ ይቀረዋል፤ እናም ይህቺ ማለዳ አንድ ቀን ትውስታው ሆና ትቀራለች። ሆኖም ይቺ የአሁን ቅጽበት ናት - ግመል ነጂው ያላት የጭፈራ ቅጽበት - እናም ያለፈ ታሪኩ ትምህርት፣ የመጪው ኑሮው ህልም አድርጎ ሊኖራት ፈለገ። እነዚህን ዛፎች ማየት አንድ ቀን ትዝታ ቢሆንም አሁን ግን ጥላን፣ ውሃን፣ ከጦርነት መደበቂያ መጠጊያ ማግኘትን ይወክላል። ትናንት የግመል ድምጽ አደጋን ያመለክት ነበር፤ ዛሬ ደግሞ የዛፎቹ ሰልፍ ተአምራትን ሊያበስር ይችላል።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ዓለም ብዙ ቋንቋ ትናገራለች ሲል አሰበ - ብላቴናው።

* * *

ጊዜያቱ በፍጥነት ተጓዙ፤ ሲራራዎቹም እንዲሁ ብሎ አሰበ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎችና እንስሳት ወደ ኦሲሱ ሲቃረቡ እየተመለከተ ያለው አልኬሚስቱ። ሰዎች ወደ እንግዶቹ ሰዎች ይጮሃሉ፤ የበረሃዋን ጸሐይ አቧራ ደብቋታል፤ የኦሲሱ ህፃናት የማያውቋቸው ሰዎች ወደ አካባቢያቸው በመምጣታቸው ተደስተው ይቦርቃሉ። አልኬሚስቱ የጎሳ አለቆች ለሲራራው መሪ ሰላምታ ሰጥተውት ለረጅም ደቂቃ ሲያዋሩት አየ።

ከእነዚህ አንዳቸውም ለአልኬሚስቱ ግድ አልሰጡትም። ብዙ ሰዎች ሲመጡ ሲሄዱ፣ በረሃውም ባለበት ሲቀር ተመልክቷል። ነገስታትና ለማኞች በበረሃው አሸዋ ላይ ሲጓዙ ተመልክቷል። ነፋስ ሰራሾቹ የአሸዋው ጋራዎች ያለማቋረጥ በነፋሱ አማካይነት ይቀያየራሉ፤ አሸዋዎቹ ግን ከህፃንነቱ ጀምሮ የሚያውቃቸው አሸዋዎች ናቸው። ተጓዦቹ በቢጫው አሸዋ ላይ ከሰማያዊ ሰማይ በታች ለሳምንታት ሲጓዙ ቆይተው ለመጀመሪያ ጊዜ አረንጓዴዎቹን ዛፎች ሲያዩ የሚሰማቸውን ደስታ ማየት ያስደስተዋል። እግዚአብሔር በረሃውን የፈጠረው ሰዎች የቴምር ዛፎችን እንዲያደንቁ ይሆናል ብሎ አሰበ።

ይበልጥ ተግባራዊ ጉዳዮች ላይ ለማተኮር ወሰነ። ሲራራው ውስጥ ከምስጢሮቹ ጥቂቶቹን አልኬሚስቱ የሚያስተምረው አንድ ሰው እንዳለ አውቋል። ንግሮቹ ነግረውታል። ሰውየውን እስካሁን አላወቀውም፤ ነገር ግን በልምምድ የሰለጠኑት ዓይኖቹ ገና ብቅ ሲል ይለዩታል። አልኬሚስቱ ይሄኛውም እንደ ከዚህ በፊቱ ደቀመዝሙሩ ብቃት ያለው እንዲሆንለት ተመኘ።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

እነዚህ ነገሮች ለምን በቃል መስተላለፍ እንዳለባቸው አላውቅም አለ በሃሳቡ። በትክክልም ምስጢርነት ኖሯቸው አይደለም፤ እግዚአብሔር ምስጢራቱን ለሁሉም ፍጡራን በቀላሉ ነው የገለጻላቸው።

ለዚህ እውነታ አንድ ማብራሪያ ብቻ ነው ያለው፡- ነገሮቹ በዚህ መንገድ መስተላለፍ ያለባቸው ከንጹሁ ሕይወት በመሰራታቸውና እንዲህ ያለው ህይወት ደግሞ በጽሑፍ ወይም በስእል ሊወከል ባለመቻሉ ነው።

ሰዎች በተጻፉ ቃላትና በስእሎች ይደነቁና የሁለንታን ቋንቋ ዘንግተውት ያርፋሉ።

* * *

ብላቴናው የሚያየውን ነገር ማመን አልቻለም። አሲሱ ልክ የጂኦግራፊ መጽሐፍ ላይ እንዳየው በጥቂት ዛፎች የተከበበ ጉድጓድ በመሆን ፋንታ ስፔን ውስጥ ካሉ በርካታ ከተሞች ሳይቀር ይተልቃል። ሶስት መቶ ጉድጓዶች፣ ሃምሳ ሺ የቴምር ዛፎች እና ቁጥር ስፍር የሌላቸው ባለቀለም ድንኳኖች አሉት።

"አንድ ሺ አንድ ሌሊትን ይመስላል" አለ እንግሊዙ፣ አልኬሚስቱን ለማግኘት እየተቅበጠበጠ።

እንስሳቱንና መጨዎቹን ሰዎች ለማየት በጓጉ ሕጻናት ተከበቡ። የአሲሱ ወንዶች ስለጦርነቱ መስማት ፈለጉ፤ ሴቶቹ ደግሞ ነጋዴዎቹ ያመጧቸውን አልባሳትና የከበሩ ድንጋዮች ለመውሰድ ተሻሙ። የበረሃው ፀጥታ የሩቅ ህልም ሆኗል፤ የሲራራው ተጓገሮች ያለማቋረጥ እየተሳሳቁና እየተጯጯሁ



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ያወራሱ - ልክ የሆነ መንፈሳዊ ዓለም ውስጥ ቆይተው አሁን ሰዎች ወዳሉበት ዓለም የተመለሱ ይመስላሉ፡፡ አሁን መንፈሳቸው አርፏል፤ እነሱም ተደስተዋል፡፡

በረሃው ውስጥ በጣም ከፍተኛ ጥንቃቄዎችን ያደርጉ ነበር፤ እሲሶች ግን፣ ግመል ነጂው ሰብሳቢናው እንዳስረዳው፣ ምን ጊዜም ነፃ ቀጣናዎች ተደርገው ይወሰዳሉ፤ ምክንያቱም ብዙሃኑ ነዋሪዎቻቸው ሴቶችና ህፃናት ናቸው፡፡ በረሃው ውስጥ እሲሶች ሞልተዋል፤ የጎሳ ጦረኞች ግን በረሃ በረሃውን እየተፋለሙ እሲሶቹን የመንገደኞች መጠለያ አድርገው ይተዋቸዋል፡፡

ትንሽ ቢቸገርም የሲራራው መሪ ተጓገሮችን አንድ ላይ ሰብስቦ መመሪያዎቹን ሰጣቸው፡፡ ቡድኑ በጎሳዎቹ መካከል የተነሳው ግጭት እስኪጠናቀቅ ባለበት ሥፍራ ይቆያል፡፡ እንግዶች እንደመሆናቸው መጠን ተጓገሮቹ ከእሲሱ ነዋሪዎች ጋር የመኖሪያ ሥፍራን መጋራት ይኖርባቸዋል፤ ጥሩ ጥሩ ነገርም ይቀርብላቸዋል፡፡ የራሱን ወታደሮች ጨምሮ ሁሉም ሰው የያዘውን የጦር መሳሪያ በጎሳው አለቆች ለተመረጡት ሰዎች እንዲያስረክብ ጠየቀ፡፡

"እነኚህ የጦርነት ደንቦች ናቸው" መሪው አስረዳ፡፡

"እሲሶች ለሰራዊቶች መጠለያ አይሆኑም፡፡"

የእንግሊዙ ከቦርሳው ውስጥ ሪቮልቨር አውጥቶ ማስረከብ ብላቴናውን አስገረመው፡፡

"ሪቮልቨር ምን ያደርግልሃል?" ጠየቀው፡፡



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ሰዎችን እንዳምናቸው ይረዳኛል" እንግሊዙ መለሰ።

በመሐል ብላቴናው ስለ ድብቅ ሃብቱ አሰላሰለ። ህልሙን እውን ለማድረግ በተቃረበበት መጠን ነገሮች ይበልጥ አስቸጋሪ እየሆኑበት ይመጣሉ። አረጋዊው ንጉስ "የጀማሪ እድል" ያሉት ነገር መስራት ያቆመ ይመስላል። ሕልሙን እውን ለማድረግ ሲተጋ ጽናቱንና ወኔውን የሚፈትኑ ሁኔታዎች ያለማቋረጥ አጋጥመውታል። ስለዚህ ችኩልም ትእግስት የለሽም መሆን አይችልም። እንዲሁ ወደፊት ቢጓዝ እግዚአብሔር በመንገዱ ላይ የተወለትን ንግሮችና ምልክቶች ማየት አይችልም።

እግዚአብሔር በመንገዱ ላይ አስቀምጧቸዋል። ይሄ ሃሳቡ ራሱን አስደነቀው። እስከዚያ ቅጽበት ድረስ ንግሮች የዚህ ዓለም ጣጣዎች ይመስሉት ነበር። ልክ እንደመብላት ወይም እንደመተኛት፣ ወይም ፍቅርን እንደመሻት ወይም ሥራ እንደማግኘት። እግዚአብሔር ማድረግ የሚገባው፣ ሊጠቁመው የሚጠቀምባቸው ቋንቋዎች ስለመሆናቸው አስቦ አያውቅም።

"ትእግስት የለሽ አትሁን" ለራሱ ደገመለት። "ልክ ግመል ነጂው እንዳለው ነው፦ የመብያ ጊዜህ ከሆነ ብላ፤ መጓዣ ጊዜህ ከሆነ ደግሞ ተጓዝ።"

በዚያ የመጀመሪያ ቀን እንግሊዙን ጨምሮ ሁሉም ሰው ደክሞ ነበርና ተኛ። ብላቴናው ከጓደኛው ርቆ፣ አምስት የእድሜ እኩዮቹ ያሉበት ድንኳን ውስጥ ተመደበ። በረኸኞች በመሆናቸው እሱ ስለ ታላላቅ ከተሞች በሚያወራቸው ታሪኮች ይደነቁ ነበር።

ብላቴናው የበጎች እረኝነት ህይወቱን ተረከላቸው፣ በክሪስታል መደብሩ ውስጥ ያሳለፈውን ጊዜ ሊነግራቸው ሲል እንግሊዙ ወደ ድንኳኑ ገባ።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ስፈልግህ አረፈድኩ" አለው ብላቴናውን ወደ ውጭ እየመራው፡፡ "አልኬሚስቱ የሚኖርበትን በማፈላለግ እንድትረዳኝ በጣም እፈልጋለሁ፡፡"

በመጀመሪያ በራሳቸው ሊፈልጉት ሞከሩ፡፡ አልኬሚስቱ ሊኖርበት ይችላል ብለው የገመቱትን ድንኳን ሁሉ ሲያስሱ ዋሉ፡፡

"ሙሉውን ቀን ልናባክነው እኮ ነው" አለ እንግሊዙ ከብላቴናው ጋር አንድ የውሃ ጉድጓድ አጠገብ ተቀምጦ፡፡

"ሰው መጠየቅ ሳይሻለን አይቀርም" ብላቴናው ሃሳብ አቀረበ፡፡ እንግሊዙ እዚህ የመጣባቸውን ምክንያቶች ሌሎች ሰዎች እንዲሰሙበት አልፈለገም ነበር፡፡ በመጨረሻ ግን ከእሱ የተሻለ አረብኛ የሚናገረው ብላቴና ሰዎች እንዲጠይቅለት ተስማማ፡፡ ብላቴናውም የፍየል ቆዳ ስልቻዋን በውሃ ልትሞላ ወደ ጉድጓድ የመጣችውን ሴት ቀረባት፡፡

"እንደምን ዋልሽ እናቴ፡፡ እዚህ ሥፍራ የአልኬሚስቱን መኖሪያ ለማግኘት እየሞከርኩ ነበር፡፡"

ሴትየዋ እንደሱ የሚባል ሰው እንደማታውቅ ነግራው በፍጥነት ከአጠገቡ ሔደች፡፡ ከመብረሯ በፊት ግን ጥቁር የለበሱ ሴቶችን ባያናግር እንደሚሻለው መከረችው፤ ምክንያቱም ጥቁር የሚለብሱት ያገቡ ሴቶች ናቸዋ፡፡ እሱም ባህሉን ማክበር አለበት፡፡

እንግሊዙ ተናድዷል፡፡ ረጅም ጉዞው በከንቱ የሚቀር መስሎ ታየው፡፡ ብላቴናውም አዝኗል፤ ጓደኛው እጣፈንታውን እየተከተለ ነው፡፡ አንድ ሰው እጣፈንታውን ሲከተል ደግሞ እንዲሳካለት ዓለም ሁሉ ሊያግዘው ይጥራል ነበር ያሉት አረጋዊው ንጉሥ፡፡ እሳቸው ሊሳሳቱ አይችሉም፡፡



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ከዚህ በፊት ስለ አልኬሚስቶች ሰምቼ አላውቅም" አለ ብላቴናው። "ምናልባትም እዚህም ማንም ሰምቶ አያውቅ ይሆናል።"

የእንግሊዙ ዓይን በራ። "ልክ ነው! ምናልባት ማንም አልኬሚስት ምን እንደሆነ አያውቅ ይሆናል! የህዝቡን በሽታዎች የሚፈውስላቸው ማን እንደሆነ ጠይቅልኝ!"

ጥቁር የለበሱ አያሌ ሴቶች ውሃ ፍለጋ ወደ ጉድጓዱ መጥተው ነበር፤ ብላቴናው ግን እንግሊዙ ቢገፋፋውም አንዳቸውንም አልጠየቃቸውም። ከዚያ አንድ ሰው ወደ እነሱ ቀረበ።

"የሰዎችን በሽታ የሚያድነውን ሰው ታውቀዋለህ?" ሲል ብላቴናው ጠየቀው።

"አላህ ነው ከህመማችን የሚፈውሰን" አለ ሰውየው፤ በጉረ ልውጦችን መፍራቱ በግልጽ እያስታወቀበት። "ጠንቋዮችን ነው የምትፈልጉት።" ከቅዱስ ቁርዓን የሆኑ ቃላትን አነበነበና መንገዱን ቀጠለ።

ሌላ ሰውዬ መጣ። እድሜያቸው ገፋ ያለ ነው፤ ትንሽዬ ባልዲ ይዘዋል። ብላቴናው ጥያቄውን ለእሳቸውም ደገመላቸው።

"እንዲህ ዓይነቱ ሰው ለምን ማግኘት ፈለግህ?" አረቡ መልሰው ጠየቁት።

"ምክንያቱም ይሄ ጓደኛዬ ብዙ ወራት ተጉዞ እዚህ የመጣው ያንን ሰው ለማግኘት ብሎ ነው" አለ ብላቴናው።

"እንደሱ ያለ ሰው እዚህ ኦሲስ ውስጥ ካለ በጣም ኃያል መሆን አለበት" አሉ ሽማግሌው ጥቂት አሰብ ካደረጉ በኋላ። "የጎሳው አለቆች እንኳን ሊያገኙት ሲፈልጉ ሊያገኙት አይችሉም። እሱ ሲፈልግ ብቻ ነው የሚገኘው።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ጦርነቱ እስኪቆም ጠብቁ። ከዚያም ከሲራራው ጋር ከዚህ ሂዱ። በኦሲሱ ሕይወት ውስጥ ጥልቅ ማለት አትሞክሩ" አሉና ሄዱ።

እንግሊዙ በጣም ተደሰተ። ትክክለኛ አቅጣጫ ላይ ናቸው። በመጨረሻም ጥቁር ያልለበሰች ወጣት መጣች። በትከሻዋ ውሃ መቅጃዋን ተሸክማለች፤ ራሷን ብትከናነብም ፊቷ አልተሸፈነም። ስለ አልኬሚስቱ ሊጠይቃት ብላቴናው ቀረብ አላት።

በዚህች ቅጽበት ራሱ መንቀሳቀስ ያቆመ መሰለ፤ የሁለንታ ነፍስ ውስጡ ተሰራጨ። ጥቋቁር ዓይኖቿን ሲመለከትና በሳቅና በዝምታ መሐል ያሉትን ከናፍሯን ሲያይ፤ ዓለም ሁሉ ከሚናገረው ቋንቋ ሁሉ በጣም በጣም ወሳኝ የሆነውን ቋንቋ፣ በምድር ላይ ያሉ ሰዎች ሁሉ በልባቸው የሚረዱትን ቋንቋ ተማረ - ፍቅርን። ከሰብአዊ ፍጡራን በእድሜው የሚተልቅ፣ ከበረሃውም ይበልጥ ጥንታዊ የሆነ ነገር። ልክ በብላቴናውና በልጅቱ ዓይኖች መሐል እንደሆነው፣ ሁለት ጥንድ አይኖች ሲገናኙ አንድ ዓይነት ኃይል የሚረጭ። ፈገግ አለች፣ ይሄ ደግሞ በእርግጠኝነት ንግር ነው - ሳይታወቀው እድሜውን ሙሉ ሲጠብቀው የኖረው ንግር። ከበጎቹና መጻሕፍቱ ውስጥ፣ ክሪስታል መደብሩ ውስጥና በበረሃው ጸጥታ ውስጥ ሲፈልገው የኖረው ንግር።

ንፁህ የዓለም ቋንቋ ነው። ማብራሪያ አያሻውም፤ ዓለሙ በማያቋርጥ ጊዜ ለመጓዙ ምንም ማብራሪያ እንደማያሻው ሁሉ። በዚያች ቅጽበት ብላቴናው የተሰማው በእርሱ ሕይወት ውስጥ ልትኖር ከምትችለው ብቸኛ ሴት ጋር መሆኑ ነው፤ እሷም ያለምንም የቃላት ልውውጥ ይሄው ሁኔታ ታውቋታል።

ፍቅር ሲይዘው እንደሚገባና ከሴቷ ጋር ለመጣመር ከመወሰኑ በፊት ግን ሊያጠናት እንደሚገባ በወላጆቹ ተነግሮታል። ሆኖም እንደዚህ የሚያስቡ



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ሰዎች የሁለንታን ቋንቋ ተረድተውት አያውቁ ይሆናል። ምክንያቱም ያንን ቋንቋ ስታውቅ በረሃም ውስጥ ይሁን የሆነ ትልቅ ከተማ ውስጥ የሆነች ሴት አንተን እንደምትጠብቅህ መረዳት ቀላል ይሆንልሃል። እናንተ ሁለት ሰዎች ስትገናኙና ዓይኖቻችሁ ሲገጣጠሙ ትናንትና ነገ አላስፈላጊ ይሆናሉ። ያቺ ቅጽበት፣ እንዲሁም ከጸሐይ በታች ያለ ነገር ሁሉ በአንድ እጅ ስለመጻፉ የማይታመን እርግጠኝነት ብቻ ይቀራሉ። ያ እጅ ፍቅርን የሚቀሰቅሰውና በምድር ላለው ሰው ሁሉ መንትያ ነፍስ የሚፈጥርለት እጅ ነው። ከዚህ ፍቅር ውጭ የሰው ልጅ ህልሞች ትርጉም የላቸውም።

መክቱብ፣ ሲል አሰበ ብላቴናው።

እንግሊዙ ብላቴናውን ወዘወዘው፣ "ጠይቃት እንጂ!"

ብላቴናው ኮረዳዋን ይበልጥ ቀረብ አላት፤ ፈገግ ስትል እሱም ፈገግ አለላት።

"ማነው ስምሽ?" ጠየቃት

"ፋጡማ" አለች ኮረዳዋ ዓይኖቿን እያሸሸች።

"በእኔም አገር አንዳንድ ሴቶች የሚጠሩበት ስም ነው።"

"የነቢያችን ሴት ልጅ ስም ነው" አለች ፋጡማ። "ወራሪዎቹ ስሙን በየደረሱት ያደርሱታል።" ይህች ቆንጆ ኮረዳ ስለወራሪዎቹ በኩራት ተናገረች።

እንግሊዙ ሲጎተጉተው ብላቴናው የሰዎችን በሽታ ስለሚፈውሰው ጠየቃት።

"እሱማ የዓለምን ምስጢራት ጠንቅቆ የሚያውቀው ሰው ነው" አለች። "ከበረሃው ጂኒዎች ጋር ይገናኛል።"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ጂኒዎች ደግ እና ክፉ መናፍስት ናቸው። ልጅቷ ያ አስገራሚ ሰውዬ የሚኖርበትን የደቡብ አቅጣጫ ጠቆመቻቸው። ከዚያም ውሃዋን ቀድታ ሄደች።

እንግሊዙም የለም፤ አልኬሚስቱን ፍለጋ ሔዷል። ልጁ ግን አንድ ቀን ሊቫንተር የዚህችን ሴት ሽቶ ይዞለት መጥቶ እንደ ነበረ እያስታወሰና መኖሯን እንኳን ሳያውቅ በፊት እንደወደዳት እያሰበ ከውሃው ጉድጓድ አጠገብ ለረጅም ሰዓት ተቀመጠ። ለእሷ ያለው ፍቅር በምድር ያለውን አዱኛ ሁሉ ለማግኘት እንደሚያስችለው አውቋል።

በማግስቱ ኮረዳዋን መልሶ እንደሚያገኛት ተስፋ አድርጎ ወደ ውሃው ጉድጓድ ሄደ። የሚደንቀው ነገር እንግሊዙንም እዚያው ሥፍራ በረሃውን ሲመለከከት አገኘው።

"ሙሉውን ከሰዓት በኋላና ምሽቱን ጠበቅሁት" አለ። "ከምሽቱ የመጀመሪያዎቹ ከዋክብት ጋር ብቅ አለ። ምን እየፈለግሁ እንደሆነ ነገርኩት፤ እሱም እርሳስን ወደ ወርቅ ለውጬ አውቅ እንደሆነ ጠየቀኝ። ልማር የመጣሁት ይህንን እንደሆነ ነገርኩት።

"‹መሞከር አለብህ› አለኝ። ይሄንኑ ብቻ ነው ያለኝ፦ 'ሂድና ሞክር።'"

ብላቴናው ምንም አልተናገረም። ምስኪኑ እንግሊዝ ይህን ሁሉ መንገድ የተጓዘው ብዙ ጊዜ የሰራውን ነገር ደግሞ እንዲሰራው ሊነገረው ብቻ ነው።

"ታዲያ ሞክረዋ" አለው እንግሊዙን።

"የማደርገው እንደሱ ነው። አሁኑኑ እጀምረዋለሁ።"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

እንግሊዙ ሄደ፤ ፋጡማ መጥታ ውሃዋን በመቅጃዋሞላች።

"አንድ ነገር ልነግርሽ ነው የመጣሁት" አለ ብላቴናው። "ሚስቴ እንድትሆኚ እፈልጋለሁ። እወድሻለሁ።"

ኮረዳዋ ውሃ መቅጃዋን ጣለችው፤ ውሃውም ተደፋ።

"እዚሁ በየቀኑ እየመጣሁ እጠብቅሻለሁ። በረሃውን አቋርጬ የመጣሁት ፒራሚዶቹ አቅራቢያ ያለ ሃብት ፍለጋ ነው፤ እናም ለኔ ጦርነቱ እርግማን መስሎኝ ነበር። አሁን ግን ምርቃት ሆኖልኛል፤ ምክንያቱም ወደ አንቺ አምጥቶኛልና።"

"ጦርነቱ የሆነ ጊዜ ማብቃቱ አይቀርም" አለች ኮረዳዋ። ብላቴናው በዙሪያው ያሉትን የቴምር ዛፎች ተመለከተ። የበጎች እረኛ እንደነበረና አሁንም ተመልሶ እረኛ መሆን እንደሚችል ለራሱ ነገረው። ፋጡማ እሱ ከሚፈልገው ሃብት ትበልጣለች።

"የጎሳው ወንዶች ሁሌም ሐብት ፍለጋ እንደተጓዙ ናቸው" አለች ኮረዳዋ፣ ልክ የሚያስበውን እንደገመተች ሁሉ። "ሴቶቹም በእነዚህ የጎሳው ወንዶች ኩራት ይሰማቸዋል።"

ውሃውን መልሳ ሞላችና ሄደች።

ልጁ በየቀኑ ፋጡማን ለማግኘት ወደ ጉድጓዱ ይሄዳል። ስለ እረኝነት ህይወቱ፣ ስለ ንጉሱ እንዲሁም ስለ ክሪስታል መደብሩ አውርቶላታል። ጓደኛሞቾች ሆነዋል፤ ደግሞም ከእሷ ጋር ከሚያሳልፋት አስራ አምስት ደቂቃ ውጭ ያለው ጊዜ የማይመሽ የማይነጋ እስኪመስለው ድረስ



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ይረገዘምበታል። በኦሲሱ ለአንድ ወር ያህል እንደቆዩ የሲራራው መሪ አብረውት የተጓዙትን ሁሉ ስብሰባ ጠራቸው።

"ጦርነቱ መቼ እንደሚያበቃ ስለማናውቅ ጉዟችንን መቀጠል አንችልም" አለ። "ፍልሚያዎቹ ረጅም ጊዜ፣ ምናልባትም ዓመታትን ሊወስዱ ይችላሉ። በሁለቱም ወገን ኃያል ጦሮች ናቸው ያሉት፣ ድሉ ለሁለቱም ወሳኝ ነው። የክፉ እና የደግ ጦርነት አይደለም። ለሃይል ሚዛን ሲሉ ሁለት ኃይሎች የሚፋለሙበት ጦርነት ነው፤ እንዲህ ያለው ጦርነት ከተጀመረ ከሌላው ዓይነት ጦርነት የረዘመ ጊዜ ይወስዳል - ምክንያቱም አላህ በሁለቱም ወገን አለ።"

ሰዎቹ ወደ የመኖሪያቸው ሲመለሱ ብላቴናው ግን ፋጡማን ሊያገኛት ሄደ። ስለጠዋቱ ስብሰባ ነገራት። "እንደምታፈቅረኝ ነገርከኝ። ከዚያም ስለ ሁለንታዊ ቋንቋና ስለየሁለንታ ነፍስ አስተማርከኝ። በዚያም ምክንያት የማንነትህ አንድ አካል ሆኛለሁ።"

ብላቴናው የድምጿን ስልትና ቃና አዳመጠና በቴምሮቹ መሐል ከሚነፍሰው ነፋስ ድምጽ ይበልጥ እንደሚያምር አሰበ።

"እዚሁ ሆኜ ለረጅም ጊዜ ስጠብቅህ ነበር። ትናንቴን፣ ባህሌን፣ የበረሃው ወንዶች ከሴቶች የሚጠብቁትን ምግባር ዘንግቼያለሁ። ከህፃንነቴ ጀምሮ በረሃው የሆነ ድንቅ ስጦታ እንደሚያመጣልኝ አልም ነበር። አሁን ስጦታዬ መጥቷል፤ አንተው ነህ ስጦታዬ።"

ብላቴናው እጇን ሊይዛት አማረው። የፋጡማ እጆች ግን የጀጉን መያዣ ይዘዋል።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ስለ ህልሞችህ፣ ስለ አረጋዊው ንጉሥ፣ ስለ ድብቅ አዱኛህም ነግረኸኛል፡፡ ስለ ንግሮችም ነግረኸኛል፡፡ ስለዚህ አሁን ምንም አልፈራም፤ ምክንያቱም እነዚያ ንግሮች ናቸው አንተን ወደ እኔ ያመጡህ፡፡ እኔም የህልምህ፣ አንተ እንደምትለው የእጣፈንታህ አንድ አካል ሆኛለሁ፡፡

"ስለዚህም ወደ ግብህ መቀጠልህን ነው የምፈልገው፡፡ ጦርነቱ እስከሚቆም እጠብቃለሁ ካልክ፤ ጠብቅ፡፡ ከዚያ በፊት መሄድ ካለብህ ግን ህልምህን ፍለጋ ሂድ፡፡ የአሸዋው ቁልሎች በነፋሱ ቢለዋወጡም፣ በረሃው ግን ፈጽሞ አይለወጥም፡፡ አንዳችን ላንዳችን ያለን ፍቅርም እንዲሁ ነው የሚሆነው፡፡

"መክቱብ" አለች፡፡ "እውነትም የህልምህ ክፋይ ከሆንኩ፤ አንድ ቀን ወደ እኔ ትመለሳለህ፡፡"

ብላቴናው ያን ቀን ከእሷ ሲለይ አዝኖ ነበር፡፡ የሚያውቃቸውን ባለትዳር እረኞች አስታወሰ፡፡ ራቅ ወዳለ መስክ ሲሄዱ ሲሉ ሁሌም ሚስቶቻቸውን ማሳመን ይቸገሩ ነበር፡፡ ፍቅር ከሚያፈቅሯቸው ሰዎች ጋር እንዲቆዩ ይጠይቃቸዋል፡፡

በቀጣዩ ቀን ይህንን ለፋጡማ ነገራት፡፡

"በረሃው ወንዶቻችንን ወስዶብናል፣ ደግሞም ሁሌም አይመለሱም" አለችው፡፡ "ያንን እናውቃለን፣ ለምደነዋልም፡፡ እነዚያ በወጡበት የሚቀሩት ደመናቱን፣ በየሰርጓጉጡ የሚደበቁትን እንስሳት፣ ከከርሰምድር የሚፈልቀውን ውሃ ይሆናሉ፡፡ የሁሉም ነገር ክፋዮች ይሆናሉ፤... የሁለንታ ነፍስ ይሆናሉ፡፡

"አንዳንዶቹ ይመለሳሉ፡፡ እናም ሌሎቹም ሴቶች ይደሰታሉ፣ ምክንያቱም ባሎቻቸው አንድ ቀን እንደሚመለሱላቸው ያምናሉ፡፡ እነዚህን ሴቶች እያየሁ



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

እቀናባቸው ነበር። አሁን ደግሞ እኔ ራሴም ከሚጠብቁት ሴቶች አንዷ እሆናለሁ።"

"እኔ የበረሃ ሴት ነኝ፤ በዚህም እኮራለሁ። ባሌ የአሸዋውን ቀለሉች እንደሚለዋውጠው ነፋስ በነፃነት እንዲሄሂርልኝ እፈልጋለሁ። ማድረግ ካለብኝ ደግሞ የደመናቱ፣ የእንስሳቱና የበረሃው ውሃ አካል መሆኑንም እቀበላለሁ።"

ብላቴናው እንግሊዙን ፍለጋ ሔደ። ስለ ፋጡማ ሊነግረው ፈልጓል። እንግሊዙ የሚኖርበት ድንኳን ደጃፍ ላይ የራሱን ብረት ማቅለጫ መስራቱን ሲያይ ተደነቀ። ማቅለጫው በማገዶ እንጨት የሚሰራ አናቱ ላይ ብርሃን አስተላላፊ ጠርሙስ ነገር ያለው ያልተለመደ ዓይነት ማቅለጫ ነው። በረሃው ላይ ያተኩሩት የእንግሊዙ ዓይኖች መጽሐፍ ሲያነብ ከሆኑት በላይ እጅግ ደምቀው ነበረ።

"ይሄ የሥራው የመጀመሪያ ደረጃ ነው" አለ። "ዲኚውን ለይቼ ማውጣት አለብኝ። ለዚህ ደግሞ 'አይሳካልኝ ይሆን' የሚል ስጋት ሊኖረኝ አይገባም። ዓቢዩን ሥራ ከመሞከር ቀድሞውኑም ያገደኝ ባይሳካልኝስ የሚለው ስጋቱ ነበር። አሁን ከአሥር ዓመት በፊት ላደርገው እችል የነበረውን ነገር እየጀመርኩ ነው። ሆኖም ሌላ ሃያ ዓመት ባለመቆየቱ ደስ ብሎኛል።"

እሳቱን ማገዶ መመገቡን ቀጠለ፤ ብላቴናውም ጀንበር እየጠለቀች የበረሃው ሰማይ ሐምራዊ እስኪሆን ድረስ እዚያው ቆየ። የበረሃው ዝምታ ለጥያቄዎቹ ምላሽ ይሰጠው እንደሆነ ለማወቅ ወደ በረሃው የመጓዝ ግፊት ተሰማው።

የአሲሱን የቴምር ዛፎች ከእይታው ሳያርቅ ዞር ዞር አለ። ነፋሱን አዳመጠው፤ እግሩ ሥር ያሉትም ድንጋዮች ተሰሙት። በየቦታው ሼሎችን



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

አገኘና በረሃው ጥንት ባህር እንደነበረ አስተዋለ። አንድ ድንጋይ ላይ ተቀምጦ ማሰላሰል ጀመረ። የፍቅርን እሳቤ ከባለቤትነት እሳቤ ለይቶ ለማሰብ ሞከረ፤ ሆኖም ሁለቱን ማለያየት ሳይሳካለት ቀረ። ፋጡማ ግን የበረሃ ሴት በመሆኗ፣ ሁኔታውን ይገነዘብ ዘንድ የሚረዳው ነገር ካለ፤ ያ ነገር በረሃው ነው።

ተቀምጦ እያሰበ ሳለ ከበላዩ እንቅስቃሴ መኖሩ ተሰማው። ቀና ሲል ጭልፊቶች በጣም ከፍ ብለው ሲበሩ ተመለከተ።

ጭልፊቶች የንፋሱን አቅጣጫ ሲከተሉ አያቸው። በረራቸው ሥርዓት ያለው ባይመስልም ብላቴናው ላይ የሆነ ስሜት አሳድሮበታል። ምን ማለት እንደሆነ ብቻ ነው ያልገባው። ሲያነበው እየጣረ የአእዋፋን እንቅስቃሴ ተከታተለ። ምናልባትም እነዚህ የበረሃ አእዋፍ ፍቅር ያለ ባለቤትነት ምን ማለት እንደሆነ ያስረዱት ይሆናል።

እንቅልፍ እንቅልፍ አለው። በልቡ ነቅቶ የመቆየትም፣ የመተኛትም ፍላጎት አደሩበት። "የሁለንታን ቋንቋ እየተማርኩ ነው፤ ደግሞም በዓለም ያለ ነገር ሁሉ ትርጉም እየሰጠኝ ነው፤... የጭልፊቶች በረራ እንኳን ሳይቀር" አለ ለራሱ። በዚህም መንፈሱ፣ ፍቅር ውስጥ መግባቱ በራሱ አስደሰተው። ፍቅር ሲይዝህ ነገሮች የበለጠ ትርጉም እየሰጡህ ይመጣሉ ብሎም አሰበ።

በድንገት፣ ከጭልፊቶቹ አንዱ በፈጣን እንቅስቃሴ ሌላኛውን ጭልፊት ያጠቃው ጀመር። በዚህ ጊዜ ብላቴናው የሆነ ቅጽበታዊ ትእይንት ተገለጠለት፦ የሆነ ጦር ሰራዊት፣ የተመዘዙ ጎራዴዎች፣ ወደ ኦሲሱ የሚጋልብ ሰራዊት። ራእዩ በፍጥነት ቢጠፋም አንቀጥቅጦታል። ሰዎች ስለ ሚራዥ ሲያወሩ ሰምቷል፤ እሱ ራሱም ታይቶት ያውቃል፦ አብዝተው



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

የሚፈልጉት ነገር ሳይሆን የሆነ መስሎ በበረሃው አሸዋ ላይ እንደማየት ያለ ነገር ነው። ሆኖም ብላቴናው አንድ ጦር ኦሲሱን እንዲወረው ምንም አይነት ፍላጎት በልቡ እንዳልነበረ እርግጠኛ ነው።

ራእዩን ለመርሳትና ወደ ተመስጦው ለመመለስ ሞከረ። መልሶ በበረሃው ሐምራዊ ጥላና በአለቶቹ ላይ ለማተኮር ሞከረ። ነገር ግን ይህን ከማድረግ የሚከለክለው ነገር ልቡ ውስጥ አለ።

"ምንጊዜም ንግሮቹን ተከተል" ብለውታል አረጋዊው ንጉሥ። ብላቴናው በራእዩ የታየውን አስታወሰ፤ ነገርየው በትክክልም ሊከሰት እንደሆነ ተረዳ።

ተነሳና ወደ ቴምር ዛፎቹ መመለስ ጀመረ። አሁንም የራሱን ጉዳዮች በተመለከተ የተለያዩ ልሳኖችን አሰላሰለ፦ ይሄኔ በረሃው አደጋ የለበትም፤ ኦሲሱ ነው አደገኛ ሥፍራ መሆን የጀመረው።

ግመል ነጂው ከአንድ የዘንባባ ዛፍ ሥር ተቀምጧል። "የሆነ ጦር እየመጣ ነው" አለው ብላቴናው። "ራእይ ታይቶኛል።"

"በረሃው የሰውን ሁሉ ልብ በራእይዎቹ ይሞላዋል" ግመል ነጂው መለሰ።

ብላቴው ግን ስለጭልፊቶቹና ድንገት ከሁለንታ ነፍስ ጋር መገናኘቱ እንደተሰማው ነገረው።

ግመል ነጂው ብላቴናው ምን እያለው እንደሆነ ገባው። በገጸ ምድር ላይ ያለ ማንኛውም ነገር የሁሉንም ነገሮች ታሪክ መግለጥ እንደሚችል ያውቃል። አንድ ሰው መጻፍ ሊያነብ ይችላል፤ ካርታ ማየት፣ ወይም የወፎችን በረራ ሊያጤን ይችላል... የሚያየው ነገር ምንም ይሁን ምን፣ አንድ ሰው ከዚያች



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ቅጽበት ገጠመኙ ጋር የሚያገናኘው መሥመር ሊኖረው ይችላል። በርግጥ የሚታዩት ነገሮች አይደሉም ምንም ነገር የሚገልጡት፤ ምን እየተፈጸመ እንዳለ የሚያዩት ሰዎች ናቸው ወደ ሁለንታ ነፍስ መዝለቅ የሚያስችል መንገድ የሚያገኙት።

በረሃው በሁለንታ ነፍስ ውስጥ መግባት በመቻላቸው ላይ ኑሯቸው በተመሰረተ ሰዎች የተሞላ ነው። አዋቂዎች ይባላሉ፤ በሴቶችና በአዛውንቶች ዘንድ ይፈራሉ። ወንዶችም እነሱን ከማማከር ይቆጠባሉ፤ ምክንያቱም እንደምትሞት ተነግሮህ ውጊያ ገብተህ በብቃት ልትፋለም አትችልም።

የጎሳው ወንዶች ውጤቱን ሳያውቁ ፍልሚያውን መቅመስን ይመርጣሉ፤ ነገማ በአላህ ተጽፏል፤ እሱ የጻፈው ደግሞ ምን ጊዜም ለበጎ ነው። ስለዚህም እነኚህ ሰዎች ዛሬን ብቻ ነው የሚኖሩት፤ ምክንያቱም ዛሬ ራሱ በአስደናቂ ነገሮች የተሞላ ነው። ግመል ነጂው ተዋጊ አይደለም፤ ስለዚህ አዋቂዎቹን አማክሮ ያውቃል። አብዛኞቹ የነገሩት ልክ ነው፤ አንዳንዶቹ ግን ይሳሳታሉ። እናም አንድ ቀን በጣም የሚፈሩትና ከሁሉም ሽምገል የሚሉት አዋቂ ግመል ነጂውን ስለነገ ለማወቅ ለምን እንደፈለገ ጠየቁት።

"እ... አንዳንድ ነገሮችን ማድረግ እንድችል" አላቸው። "እንዲሆኑብኝ የማልፈልጋቸውን ነገሮች መሰወጥ እንድችል ብዬ ነው።"

"የነገህ ገጽታዎች ላይሆኑ ነዋ" አሉት አዋቂው።

"ምናልባትም ነገዬን ማወቅ የፈለግሁት ለሚመጣብኝ ነገር ራሴን ለማዘጋጀት ብዬ ይሆናል።"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"በጎ በጎ ነገሮች ቢመጡ አስደሳች መደነቅን ይሰጡሃል። ክፉ ነገሮች ቢኖሩና ቀድመህ ብታውቃቸው፣ ከመከሰታቸው በፊት በጣም ትሰቃያለህ።"

"ስለ ወደፊቴ ማወቅ የምፈልገው ሰው ስለሆንኩ ነው" አላቸው ግመል ነጂው። "ሁሉም ሰው ሁሌም የሚኖረው በነገው ላይ ተመስርቶ ነው።"

አዋቂው ጠጠር በመጣል አወዳደቃቸውን በማየት መተንበይን ነው የተካኑት። ያን ቀን ግን አልተነበዩም። ጠጠሮቹን በጨርቅ ጠቅልለው ቦርሳቸው ውስጥ አስቀመጧቸው።

"የምተዳደረው ለሰዎች ወደፊት የሚያጋጥማቸውን በመንገር ነው" አሉት። "የጠጠሮችን ጥበብ፣ በእነሱም አማካይነት ሁሉ ነገር ወደ ተጻፈበት ሥፍራ እንዴት እንደምገባ አውቃለሁ። እዚያም የትናንቱን ማንበብ፣ የተረሳውን ማወቅና አሁን ያሉትን ንግሮችን መረዳት እችላለሁ።

"ሰዎች ሲጠይቁኝ ነገን አላነብላቸውም፤ ነገን እገምትላቸዋለሁ እንጂ። ነገ የአምላክ ነው፣ በሚያስደንቅ ሁኔታ ውስጥ የሚገልጠውም እሱው ብቻ ነው። ነገን እንዴት እገምታለሁ? በዛሬ ንግሮች ላይ ተመስርቼ። ምስጢሩ ያለው ዛሬ ውስጥ ነው። ዛሬን ልብ ካልከው እሱው ላይ ልትሻሻል ትችላለህ። ዛሬህን ካሻሻልከው ደግሞ ነገህም የተሻለ ይሆናል። የወደፊቱን እርሳውና እያንዳንዱን ቀን በአላህ አስተምህሮት እየተመራህ፣ ለልጆቹ ባለው ፍቅርም እየተማመንህ ኑር። እያንዳንዱ ቀን በራሱ ዘላለማዊነትን ይዞልህ ይመጣል።"

ግመል ነጂው አላህ የወደፊቱን ያይ ዘንድ የሚፈቅድለት በምን ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ እንደሆነ ጠየቃቸው።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"እሱው ራሱ ሲገልጠው፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ ነገን የሚገልጠው ከስንት ጊዜ አንዴ ነው፡፡ የሚገልጠውም ስለ አንድ ምክንያት ብቻ ነው፡- ይለወጥ ዘንድ የሚቻለው ነገ ብቻ በመሆኑ ነው፡፡"

እግዚአብሔር ለብላቴናው ነገን በከፊል አሳይቶታል፣ ብሎ አሰበ ግመል ነጂው፡፡ መሳሪያው ይሆነው ዘንድ ብላቴናውን ለምን መረጠው?

"ሂድና የጎሳውን መሪዎች አናግራቸው" አለው ግመል ነጂው፡፡ "እየተቃረቡ ስላሉት ሰራዊቶች ንገራቸው፡፡"

"ይስቁብኛል፡፡"

"እነሱ በረኸኞች ናቸው፤ በረኸኞች ደግሞ ንግሮችን እንዴት ማየት እንዳለባቸው ያውቃሉ፡፡"

"እንግዲያውስ እስካሁን አውቀውት ይሆናል፡፡"

"በዚህ ሰዓት እሱ አያሳሰባቸውም፡፡ አላህ ያውቁት ዘንድ የፈለገውን ነገር ማወቅ ካለባቸው የሆነ ሰው እንደሚነግራቸው ያምናሉ፡፡ ከዚህ በፊት ብዙ ጊዜ እንዲሁ ሆኗል፡፡ አሁን ግን ያ ሰው አንተ ነህ፡፡"

ልጁ ስለ ፋጡማ አሰበ፡፡ የጎሳዎቹን መሪዎች ለማግኘት ሊሄድም ወሰነ፡፡

* * *

ብላቴናው በኦሲሱ መካከለኛ ሥፍራ ላይ ከተተከለ አንድ ትልቅ ነጭ ድንኳን ፊት ለፊት የቆመውን ዘብ ቀረበው፡፡



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"የጎሳ መሪዎቹን ማናገር እፈልጋለሁ። ከበረሃው ንግሮችን ይገሮ መጥቻለሁ።"

ምንም ሳይመልስለት ዘቡ ወደ ውስጥ ገብቶ ጥቂት ቆየ። ሲወጣ ነጭና ወርቃማ ልብስ ከለበሰ ወጣት አረብ ጋር ተመለሰ። ብላቴናው ያየውን ነገር ለወጣቱ ሲነግረው ወጣቱ ጠብቅ ብሎት ድንኳኑ ውስጥ ገብቶ ጠፋ።

መሸ፣ የሚጣሉ ሰዎችና ነጋዴዎች ስብስብ ስብስብ እያሉ ወደ ድንኳኑ ይገባሉ፣ ይወጣሉ። እደጅ እየነደዱ የነበሩት እሳቶች አንድ በአንድ ጠፉ፤ ኦሲሱም የበረሃው ዓይነት ጸጥታ ነገሰበት። በታላቁ ድንኳን ውስጥ የነበሩት መብራቶች ብቻ እንደበሩ ቀሩ። በዚህ ሁሉ ጊዜ ብላቴናው ስለ ፋጡማ እያሰበ ነበር፤ ለመጨረሻ ጊዜ የተነጋገሩት ነገር እስካሁንም አልገባውም።

በመጨረሻ፣ ከስንት ሰዓታት በኋላ ዘቡ እንዲገባ ፈቀደለት። ብላቴናው ውስጥ በሚያየው ነገር ተደነቀ። በዚህ ጭልጥ ያለ በረሃ መሃል እንዲህ አይነት ድንኳን ይኖራል ብሎ ፈጽሞ አስቦ አያውቅም። ወለሉ እስከዛሬ ከረገጣቸው ምንጣፎች ሁሉ ይበልጥ ውብ በሆኑ ምንጣፎች ተሸፍኗል፤ በድንኳኑ አናት በኩል በሻማ አማካይነት የበሩ የወርቅ አምፑሎች ተሰቅለዋል። የጎሳ መሪዎቹ በድንኳኑ ጓዳ በጥልፍ ካጌጡ የሐር ፍራሾች ላይ በግማሽ ክብ ቅርጽ ጋደም ጋደም ብለዋል። አሽከሮቹ በብር ትሪዎች ላይ ጣፋጮችና ሻይ ሞልተው ሽር-ጉድ ይላሉ። ሌሎቹ ይተጋሉ። የከፍሉ አየር በጭሳጭስ ጣፋጭ መዓዛ ታውዷል።

የጎሳ መሪዎቹ ስምንት ናቸው፤ ብላቴናው ግን ወሳኙ የትኛው እንደሆነ ማወቅ ችሏል፦ ነጭና ወርቃማ ልብስ የለበሰ አረብ ከግማሽ ክቡ መሐል ተቀምጧል። ከጎኑ ቅድም ብላቴናውን ያነጋገረው ወጣት አረብ አለ።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ስለ ንግሮች የሚናገረው ፀጉሬ ልውጥ ማነው?" ብሎ ጠየቀ፣ አንደኛው የጎሳ መሪ ብላቴናውን እያየ።

"እኔ ነኝ" መለሰለት ብላቴናው። ያየውንም ተናገረ።

"በረሃው እኛ ለስንት ትውልድ እዚህ መኖራችንን እያወቀ ለምን ሲል ነው እንዲህ ያሉ ነገሮችን ለጸጉሬ ልውጥ የሚገልጠው?" አለ ሌላኛው።

"ምክንያቱም የእኔ ዓይኖች ከበረሃው ጋር አልተላመዱም" አለ ብላቴናው። "ከበረሃው ጋር የተላመዱ ዓይኖች ላያዩዋቸው የሚችሉ ነገሮችን ማየት እችላለሁ።"

'በዚያ ላይ ደግሞ ስለ የሁለንታ ነፍስ አውቃለሁ' ሲል አሰበ ለራሱ።

"አሲሱ ገለልተኛ መሬት ነው። ስለዚህ አሲስን የሚያጠቃ የለም" ሶስተኛው ተናገረ።

"እኔ ያየሁትን ልነግራችሁ ብቻ ነው የምችለው። ልታምኑኝ ካልፈለጋችሁ፣ ይህን ጉዳይ በተመለከተ ምንም ማድረግ አይኖርባችሁም።"

ሰዎቹ የሞቀ ክርክር ውስጥ ገቡ። የሚያወሩት ብላቴናው በማይገባው የአረብኛ ዘዬ ነበር። ሊወጣ ሲል ግን ዘበኛ እንዲቆይ ነገረው። ብላቴናው ፍርሃት ገባው፤ ንግሮቹ የሆነ ችግር መኖሩን ነግረውታል። በረሃው ውስጥ ስላየው ነገር ለግመል ነጂው ማውራቱ ቆጨው።

በድንገት መሐል ላይ ያለ ሽምግል ያለ ሰው ፈገግ አለ፤ ይሄኔ ብላቴናው በጥቂቱ አረጋጋ ተሰማው። ሰውየው በክርክሩ አልተሳተፉም፤ እውነቱን



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ለመናገር እንዲትም ቃል አልተናገሩም ነበር። ነገር ግን ብላቴናው የሁለንታ ቋንቋ ይገባው ጀምሯል፣ በድንኳኑ ውስጥ የተሰራጨው የሰላም መንፈስ ይሰማዋል። አሁን መምጣቱ ልክ መሆኑ ገባው።

ውይይታቸው አበቃ። የጎሳ መሪዎቹ የሽማግሌውን ንግግር ሲያዳምጡ ለጥቂት ደቂቃዎች ጸጥ አሉ። ከዚያ ሽማግሌው ወደ ብላቴናው ዞሩ፡- በዚህ ግዜ ግን ፊታቸው ላይ የሚነበበው ቅዝዝ ቅዝቅዝ ያለ ስሜት ሆነ።

"ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት፣ በአንድ ሩቅ አገር፣ አንድ በህልም የሚያምን ሰው ወደ ጭለማ እስር ቤት ተጣለ፤ በኋላም በባርነት ተሸጠ" አሉ ሽማግሌው ልጁ በሚገባው ዘዬ። "የእኛ ነጋዴዎች ያንን ሰው ገዙትና ወደ ግብጽ አመጡት። በህልሞች የሚያምን ሁሉ ህልሞቹን መፍታትም እንደሚችል ሁላችንም እናውቃለን።"

ሽማግሌው ቀጠሉ፤ "ፈርኦን ከሲታና ወፋፍራም ስለነበሩ ላሞች ሲያልም፣ ይሄ ያልኩት ሰው ግብጽን ከረሃብ ታደጋት። ስሙ ዮሴፍ ይባላል። እርሱም እንዳንተ በባእድ ምድር ላይ የተገኘ ባእድ ነበር፣ እድሜውም ያንተን ያህል ሳይሆን አይቀርም።"

ንግግራቸውን ገቱ፤ ዓይኖቻቸው ግን አሁንም የወዳጅነት ስሜት አይነበብባቸውም።

"ይህን ትውፊት ሁሌም እናከብረዋለን። ትውፊቱ ያኔ ግብጽን ከረሃብ ታድጎ ግብጻዊያንን በብልጽግና የላቁ ህዝቦች አድርጓቸዋል። ትውፊቱ ሰዎችን እንዴት በረሃውን ማቋረጥ እንደሚችሉ፣ ልጆቻቸውንም እንዴት ማግባት እንዳለባቸው ያስተምራቸዋል። ትውፊቱ አንድ ኦሲስ ገለልተኛ ድንበር ነው



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ይላል፤ ምክንያቱም ሁለቱም ወገኖች ኦሲሶች አሏቸው፤ ስለዚህም ለአደጋ የተጋለጡ ናቸው።"

ሽማግሌው ንግግራቸውን ሲቀጥሉ አንድም ሰው ቃል አልተነፈሰም።

"ነገር ግን ትውፊቱ የበረሃውን መልእክቶች ማመን እንዳለብንም ይነግረናል። የምናውቀውን ነገር ሁሉ የተማርነው ከበረሃው ነው።"

ሽማግሌው የሆነ ምልክት ሲሰጡ ሁሉም ተነስተው ቆሙ። ስብሰባው አብቅቷል። የሁቃሆቹ እሳቶች ጠፉ፤ ዘቦቹ በተጠንቀቅ ቆሙ። ልጁ ለመሄድ ሲዘጋጅ ሽማግሌው እንደገና መናገር ጀመሩ።

"ነገ ኦሲሱ ውስጥ ማንም ሰው የጦር መሳሪያ እንዳይዝ የሰራነውን ደንብ እናፈርሳለን። ሙሉውን ቀን ጠላቶቻችን ስንቃኝ እንውላለን። ጀንበር ስትጠልቅ ደግሞ ሰዎቹ መሳሪያቸውን መልሰው ያስረክቡናል። ከጠላቶቻችን ወገን አስር ሰዎች በሞቱ ቁጥር አንድ ወርቅ ይሰጥሀል።

"ሆኖም መሳሪያዎች እንደ በረሃው አመላቸው የማይጨበጥ ነገሮች በመሆናቸው ካልተጠቀምክባቸው፣ በሌላ ጊዜ ልጠቀምባቸው ብትል ላይሰሩልህ ይችላሉ። ቀኑ እስኪጠናቀቅ ድረስ ከመሳሪያዎቹ ቢያንስ አንድ እንኳን ጥቅም ላይ ሳይውል ቢቀር፣ አንደኛው አንተ ላይ ያርፋል።"

ብላቴናው ከድንኳኑ ሲወጣ ኦሲሱ የበራው በሙሉዋ ጨረቃ ብርሃን ብቻ ነበር። ወደ ራሱ ድንኳን ለመድረስ የሃያ ደቂቃ መንገድ ይጠብቀዋል፤ እናም መንገዱን ጀመረ።

በተከሰተው ነገር ተነቃቅቷል። በሁለንታ ነፍስ ውስጥ ማለፍ ችሏል፤ ይህን ማድረጉ ምናልባትም ህይወቱን ያስከፍለው ይሆናል። አስፈሪ ድርድር ነው።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ሆኖም አጣፈንታውን ለመከተል በጎቹን ከሸጠበት ቀን ጀምሮ አደገኛ ድርድሮችን ሲያደርግ ነበር። እናም ልክ ግመል ነጂው እንዳለው፣ ነገ መሞት በሌላ ቀን ከመሞት የከፋ አይሆንም። እያንዳንዱ ቀን ወይ ይኖርበታል፤ ወይም የአንድ ሰው ከዚህ ዓለም መለየት ይጻፍበታል። ሁሉም ነገር የአንድ ቃል ጥገኛ ነው፦ "መክቱብ።"

ምንም ዓይነት ቁጭት ሳይሰማው በጸጥታ እየተጓዘ ነው። እሱ ነገ ቢሞት፣ እግዚአብሔር ሊመጣ ያለውን ክስተት መለወጥ አልፈቀደም ማለት ነው። ቢያንስ መንገዶችን ካቋረጠ፣ ክሪስታል መደብር ውስጥ ከሰራ፣ የበረሃውን ጸጥታና የፋጡማን ዓይኖች ካወቀ በኋላ ነው የሚሞተው። ከረጅም ጊዜ በፊት ቤቱን ጥሎ ከወጣ ወዲህ እያንዳንዷን ቀን በደንብ ነው የኖራት። ነገ ቢሞትም እንኳን የሚሞተው ከሌሎች እረኞች የበለጠ አይቶ ነውና ኩራት ይሰማዋል።

ድንገት የመብረቅ ዓይነት መባረቅ ሰማ፤ አጋጥሞት የማያውቀው ዓይነት ነፋስ መሬት ላይ ወረወረው። አካባቢው በሽክርክሪታም አቧራ ተሞላና ጨረቃዋን ከእይታ ሰወራት። ከፊት ለፊቱ በሚያስፈራ ጩኸት ላዩ ላይ ሊወጣበት የሚል ግዙፍ ነጭ ፈረስ ታየው።

እይታን የሚሰውረው አቧራ በትንሹ ረገብ ሲል ብላቴናው ባየው ነገር ተብረከረከ። ከእንሰሳው በላይ እስከታች ጥቁር በጥቁር የለበሰ፣ ግራ ትከሻው ላይ ፋልኮን ያስቀመጠ ፈረሰኛ ተቀምጧል። ጥምጣም አድርጓል፤ ከዓይኑ በቀር ሙሉ ፊቱ በጥቁር መሐረብ ተሸፍኗል። የበረሃ መልእክተኛ ይመስላል፤ ሁኔታው ግን ከተራ መልእክተኛነት የገዘፈ ነበር።

ይሄ አስገራሚው ፈረሰኛ ትልቅ ባለ ደጋን ቅርጽ ሠይፍ መዘዘ። ስለቱ በጨረቃዋ ብርሃን አብረቀረቀ።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"የአእዋፋቱን በረራ ትርጉም ለማንበብ የደፈረው ማነው?" ጠየቀው፤ ድምጹን ሠይፉ በሃምሳ ሺዎቹ የአልፋዩም የቴምር ዛፎች ውስጥ የሚያስተጋባው እስኪመስል ድረስ እየጮኸ።

"እኔ ነኝ የደፈርኩት" አለ ብላቴናው። የሳንቲያጎ ማታሞሮስ ምስል፣ በነጩ ፈረሱ ላይ ሆኖ፣ አረማዊያን ከሰኮናው ስር ሆነው ታየው። ሰውየው እሱን ነው የሚመስለው፤ ልዩነቱ ምግባር መለዋወጣቸው ነው።

"እኔ ነኝ የደፈርኩት" ብሎ ደገመለትና የሠይፉን ምት ለመቀበል ራሱን ዝቅ አደረገ። "የሁለንታን ነፍስ ማየት በመቻሌ አያሌ ነፍሶች ይድናሉ።"

ሠይፉ አላረፈበትም። ይልቁንም ሰውየው የብላቴናውን ግንባር እስኪነካ ድረስ ዝቅ አደረገው። ጠብታ ደም ከግንባሩ ፈነ ለች።

ፈረሰኛው ልክ እንደብላቴናው አይንቀሳቀስም። ብላቴናው ማምለጥ እንኳን አልታየውም። በልቡ ያልተለመደ ዓይነት ደስታ ተሰማው፦ እጣ ፈንታውን ስለመከተሉ ሊሰዋ ነው። ስለፋጡማም ጭምር። ለማንኛውም ንግሮቹ እውነተኛ ናቸው።

አሁን ከጠላቱ ጋር ተፋጧል፤ ስለመሞት ማሰብ ግን አይጠበቅበትም - የሁለንታ ነፍስ ይጠብቀዋል፤ ብዙም ሳይቆይ የዚያ አካል ይሆናል። ነገ ደግሞ ጠላቱም ጭምር የዚያ ነፍስ አንድ አካል ይሆናል።

ፈረሰኛው ሠይፉን የልጁ ግንባር ላይ እንዳደረገ ነው። "የጭልፊቶቹን በረራ ለምን አነበብክ?"

"ያነበብኩት አእዋፉ ሊነግሩኝ የፈለግሁትን ብቻ ነው። አሲሱን መታደግ ፈልገዋል። ነገ ሁላችሁም ትሞታላችሁ፤ ምክንያቱም እናንተ ካሏችሁ ሰዎች የበለጠ አሲሱ ውስጥ አሉ።"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ሠይፉ ባለበት ቆየ፡፡ "አላህ የፈቀደውን ትሰውጥ ዘንድ አንተ ማን ነህ?"

"አላህ ሰራዊቱን ፈጠረ፣ ጭልፊቶቹንም ፈጠረ፡፡ አላህ የአዕዋፉን ቋንቋ አስተማረኝ፡፡ ነገር ሁሉ በአንድ እጅ ተጽፏልና" አለ ብላቴናው፣ የግመል ነጂውን ቃላት እያስታወሰ፡፡

ፈረሰኛው ሠይፉን ከብላቴናው ግንባር ላይ አነሳለት፤ ብላቴናው ከፍተኛ እፎይታ ተሰማው፡፡ ሆኖም አሁንም ማምለጥ አይችልም፡፡

"ትንበያዎችህን ተጠንቀቅ" አለ ፈረሰኛው፡፡ "አንድ ነገር ከተጻፈ በኋላ ሊለወጥ የሚችልበት ዘዴ የለም፡፡"

"ያየሁት ሰራዊት ነው" አለ ብላቴናው፡፡ "የጦርነቱን ውጤት አላየሁም፡፡"

ፈረሰኛው በመልሱ የረካ መሰለ፡፡ ሠይፉን ግን እጁ ላይ አቆየው፡፡ "አንድ ባእድ በባእድ ምድር ላይ ምን ይሰራል?"

"እጣ ፈንታዬን እየተከተልኩ ነው፡፡ ልትረዳው የምትችለው ነገር አይደለም፡፡"

ፈረሰኛው ሰይፉን ወደ አፎቱ መለሰው፤ ብላቴናውም ዘና አለ፡፡

"ወኔህን መፈተን ነበረብኝ" አለ ፈረሰኛው፡፡ "ወኔ የሁለንታን ልሳን ለመረዳት በጣም አስፈላጊ ብቃት ነው፡፡"

ብላቴናው ተደነቀ፡፡ ፈረሰኛው በጣም ጥቂት ሰዎች ብቻ ስለሚያውቁት ነገር እየተናገረ ነው፡፡



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ይሄን ያህል ርቀት ከመጣህ በኋላ ማቆም የለብህም" ቀጠለ። "በረሃውን ልትወደው ይገባል፤ ነገር ግን ፈጽሞ ሙሉ በሙሉ አትመነው። ምክንያቱም በረሃው ሰውን ሁሉ ይፈትናል፦ እያንዳንዱን እርምጃ ይፈታተናል፣ አቅመ ቢሶቹንም ይገድላል።"

የሚናገረው ነገር ብላቴናውን አረጋዊውን ንጉሥ አስታወሰው።

"ተዋጊዎቹ ከመጡና፤ ራስህ እስከ ጀንበር መጥለቂያ ድረስ ትከሻህ ላይ ከቆየልህ፤ መጥተህ ፈልገኝ" አለ እንግዳው ሰው።

ሰይፉን የመዘዘው ያው እጁ አሁን አለንጋ ያዘ። ፈረሱ እንደገና የአቧራ ደመና እያስነሳ ጋለበ።

"የት ነው የምትኖረው?" ጮኸ ብላቴናው።

አለንጋውን የያዘው እጅ ወደ ደቡብ አመለከተው።

ብላቴናው ከአልኬሚስቱ ጋር ተገናኘ።

* * *

በማግስቱ ጠዋት በአል-ፋዩም የቴምር ዛፎች ውስጥ የተሸሸጉ ሁለት ሺ የታጠቁ ጦረኞች ነበሩ። ፀሐይ በአናት ከመሆኗ በፊት አምስት መቶ የጎሳው አባላት በአድማሱ ላይ ብቅ አሉ። ፈረሰኛ ተዋጊዎች ከሰሜን በኩል ወደ ኦሲሱ ገቡ፤ ሰላማዊ ጉዞ ይምሰል እንጂ ሁሉም በየመጎናጸፊያዎቻቸው ሥር መሳሪያዎቻቸውን ደብቀው ይዘዋል። በማዕከለ አል-ፋዩም ወደሚገኘው



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ነጩ፡ ድንኳን ሲደርሱ ባለ አንድ አፍ ሰይፎቻቸውንና ጠብመንጃዎቻቸውን አወጡ፡፡ ከዚያም በድንኳኑ ላይ ጥቃት ሰነዘሩ፤ ድንኳኑ ግን ባዶ ነበር፡፡

የኦሲሱ ሰዎች የበረሃውን ፈረሰኞች ከበው በግማሽ ሰዓት ውስጥ ከአንዱ በስተቀር ሁሉንም ወራሪዎች ፈጇቸው፡፡ ህፃናቱ በቴምር ዛፎቹ በተፈጠረው ጫካ ውስጥ ተደብቀው ስለነበር ምን እንደተፈጠረ አላዩም፡፡ ሴቶቹ ለባሎቻቸው ደህንነት እየጸለዩ በየድንኳኖቻቸው ውስጥ በመቆየታቸው እነሱም ጦርነቱን አላዩም፡፡ ግዳዮቹ በየሜዳው ባይዘረሩ ኖሮ፣ እንደማንኛውም የኦሲሱ ቀን በመሰለ ነበር፡፡

ከወራሪዎቹ የተረፈው ተዋጊ የሻለቃ ጦሩ አዛዥ ብቻ ነበር፡፡ የዚያኑ እለት ከሰዓት በኋላ የጎሳው መሪዎች ፊት ቀርቦ ትውፊቱን ለምን እንደጣሰ ተጠየቀ፡፡ አዛዡም ሰዎቹ ረሃብና ጥም እንደጎዳቸው፣ ከአያሌ ቀናት የጦር ውሎ በኋላ እንደደከሙና፤ በዚህም ምክንያት ኦሲሱን ዘርፈው ወደ ጦርነቱ ለመመለስ መወሰናቸውን ተናገረ፡፡

የጎሳ መሪው ለሞቱት ሰዎች ማዘናቸውን፣ ነገር ግን ትውፊቱን መታደጋቸውን ተናገሩ፡፡ አዛዡም የውርደት ሞት እንዲሞት ፈረዱበት፡፡ በስለት ወይም በጥይት በመገደል ፋንታ በአንድ የሞተ የዘንባባ ዛፍ ላይ ተሰቅሎ አካላቱ በበረሃው ንፋስ እንዲበጣጠቅ ተፈረደበት፡፡

የጎሳ መሪው ብላቴናውን አስጠርተው ሃምሳ ወርቆችን ሰጡት፡፡ ስለ የግብጹ ዮሴፍ ነግረውት የነበረውን ታሪክ ነግረውት፣ ብላቴናው የኦሲሱ አማካሪ እንዲሆን ጠየቁት፡፡

* * *



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ጀንበር ስትጠልቅና የመጀመሪያዎቹ ከዋክብት ሲታዩ፣ ብላቴናው በደቡብ አቅጣጫ መጓዝ ጀመረ። በመጨረሻ አንድ ብቸኛ ድንኳን ተመለከተ፤ አልፎ ሂያጅ አረቦችም ሥፍራው በጂኒዎች የተያዘ እንደነበረ ነገሩት። ብላቴናው ግን ቁጭ ብሎ መጠበቁን ተያያዘው።

ጨረቃ በማዕከለ ሰማይ እስክትታይ ድረስ አልኬሚስቱን አላየውም ነበር። አልኬሚስቱ ሁለት የሞቱ ጭልፊቶችን በትከሻው ተሸክሟል።

"መጥቻለሁ" አለው ብላቴናው።

"መምጣት አልነበረብህም" መለሰ አልኬሚስቱ። "ወይስ እጣ ፈንታህ ይሆን እዚህ ያመጣህ?"

"በጎሳዎች መካከል የተነሱት ጦርነቶች እስካሉ ድረስ በረሃውን ማቋረጥ አይቻልም። ለዚህ ነው የመጣሁት።"

አልኬሚስቱ ከፈረሱ ወረደ፤ ብላቴናው ወደ ድንኳኑ አብሮት እንዲገባም ምልክት ሰጠው። አሲሉ ውስጥ እንዳሉት እንደ ብዙዎቹ ድንኳኖች ዓይነት ነው። አልኬሚስቶች ይጠቀሙባቸዋል ብሎ ያሰባቸውን እንደ ማቅለጫ አይነት ቁሶች ፈለገ፤ አንድም አላገኘም። ጥቂት መጻሕፍት፣ ምግብ ማብሰያ ምድጃ፣ እንዲሁም በምስጢራዊ ንድፎች የተሸፈኑ ምንጣፎች ናቸው ያሉት።

"ተቀመጥ። የሆነ ነገር እንጠጣና እነዚህን ጭልፊቶች እንበላቸዋለን" አለ አልኬሚስቱ።

ብላቴናው ጭልፊቶቹ ትናንት ያየቸው ጭልፊቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ ቢጠራጠርም ምንም አልተናገረም። አልኬሚስቱ እሳት አያያዘ፤ ብዙም



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ሳይቆይ በጣፋጭ መዓዛ ድንኳኑን ሞላው፡፡ ከሁቃሆች መዓዛ በበለጠ መዓዛ፡፡

"ስለምን ልታገኘኝ ፈለግህ?" ብላቴናው ጠየቀው፡፡

"በንግሮቹ ምክንያት" አልኬሚስቱ መለሰለት፡፡ "ነፋሱ እንደምትመጣና እገዛ እንደሚያስፈልግህ ነግሮኛል፡፡"

"ነፋሱ ስለ እኔ አይደለም የተናገረው፡፡ ስለ ሴላኛው የውጭ ዜጋ፣ ስለ እንግሊዙ ነው፡፡ አንተን በመፈለግ ላይ ያለው እሱ ነው፡፡"

"እሱ አስቀድሞ ሊያከናውናቸው የሚገባ ነገሮች አሉ፡፡ ሆኖም ትክክለኛው መስመር ላይ ነው፡፡ በረሃውን ለመረዳት ሙከራውን ጀምሯል፡፡"

"ታዲያ እኔስ?"

"አንድ ሰው ከልቡ የሆነ ነገር ሲሻ፣ ዓለሙ ሁሉ ያ ሰው ህልሙን እውን ያደርግ ዘንድ ሊያግዘው ይነሳል" አለ አልኬሚስቱ፣ የአረጋዊውን ንጉሥ ቃላት መልሶ እያስተጋባ፡፡ ብላቴናው ሃሳቡ ገብቶታል፡፡ ወደ እጣፈንታው ለመድረስ የሚያግዘው አንድ ሌላ ሰው አግኝቷል፡፡

"እና ልታስተምረኝ ነዋ?"

"አይደለም፡፡ ማወቅ ያለብህን ሁሉ አውቀኸዋል፡፡ እኔ ወደ ድብቅ ሀብትህ አቅጣጫ ልመራህ ብቻ ነው፡፡"

"የጎሳ ጦርነቱ እኮ አለ" ብላቴናው ሃሳቡን ደገመው፡፡



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"በረሃው ውስጥ ምን እየተፈጠረ እንዳለ አውቃለሁ።"

"አዱኛዬን እኮ አግኝቻለሁ። ግመል አለኝ፤ ከክሪስታል መደብሩ ያጠራቀምኩት ገንዘብ አለኝ፤ ሃምሳ ቁራጭ ወርቆች አሉኝ። በአገሬ የናጠጥኩ ሃብታም እሆናለሁ።"

"ነገር ግን ከእነዚህ አንዳቸውም ከፒራሚዶቹ የተገኙ አይደሉም" አለ አልኬሚስቱ።

"ፋጡማም አለችኝ። ካገኘሁት ሃብት ሁሉ ትበልጣለች።"

"እሷም ብትሆን ከፒራሚዶቹ አልተገኘችም።"

በጽጥታ ተመገቡ። አልኬሚስቱ አንድ ጠርሙስ ከፈተና በብላቴናው ብርጭቆ ውስጥ ቀይ ፈሳሽ ጨመረ። ከቀመሳቸው ወይኖች ሁሉ በጥፍጥናው ወደር የማይገኝለት ወይን ነው።

"ወይን እዚህ አልተከለከለም እንዴ?"

"ወደ አፍ የሚገባው ሳይሆን ከአፍ የሚወጣው ነው የሚያረክሰው" አለው አልኬሚስቱ።

አልኬሚስቱ ፍርሃት ይረጫል። ብላቴናው ግን ወይኑን ሲጠጣ ተዝናና። በልተው ሲጨርሱ ከድንኳኑ ውጪ ከዋክብቱን ባደበዘዘቻቸው ደማቅ የጨረቃ ብርሃን ተቀመጡ።

"እየጠጣህ ራስህን አስደስት" አለ አልኬሚስቱ ብላቴናው ደስተኝነት እየተሰማው እንደሆነ አስተውሎ። "ዛሬ ለሊት ልክ ለፍልሚያ እንደሚዘጋጅ ተዋጊ በደንብ እረፍ።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ልብህ ባረፈችበት የትኛውም ሥፍራ ሀብትህን እንደምታገኘው አስታውስ። እግረ መንገድህን የተማርከው ነገር ሁሉ ትርጉም ይኖረው ዘንድ ያንን ሃብት ማግኘት አለብህ።

"ነገ፣ ግመልህን ሸጥና ፈረስ ግዛ። ግመሎች አታላዮች ናቸው፡- በሺ የሚቆጠሩ እርምጃዎችን ተጉዘውም ፈጽሞ የሚደክሙ አይመስሉም። ከዚያ ድንገት በርከክ ይሉና በዚያው ይሞታሉ። ፈረሶች ግን ቀስ በቀስ ነው የሚደክሙት። ሁሌም እነሱ ምን ያህል ሊያገለግሉህ እንደሚችሉና መቼ እንደሚሞቱ ታውቃለህ።"

* * *

በተከታዩ ምሽት፣ ብላቴናው ፈረስ ላይ ጉብ ብሎ ወደ አልኬሚስቱ ድንኳን መጣ። አልኬሚስቱም ዝግጁ ነበርና ሠንጋ ፈረሱ ላይ ወጥቶ ፋልኮኑን በግራ ትከሻው ላይ አስቀመጠ። ብላቴናውንም፣ "በበረሃው ውስጥ ህይወት ያለበትን ሥፍራ አሳየኝ። የህይወት ምልክቶችን ማየት የሚችሉ ብቻ ናቸው ድብቅ ሃብት ማግኘት የሚችሉት" አለው።

በአሸዋዎቹ ላይ በጨረቃ ብርሃን መጋለብ ጀመሩ። በረሃው ውስጥ ህይወት ማግኘት መቻሉን እንጃ ሲል አሰበ - ብላቴናው። በረሃውን ያን ያህል አላውቀውም።

አልኬሚስቱን እንደዚሁ ሊለው ፈልጎ ነበር፤ ነገር ግን ፈርቶታል። ጭልፊቶችን አይቷቸው የነበረበት አለታማ ስፍራ ደረሱ፤ አሁን ግን ጸጥታና ነፋስ ብቻ ናቸው ያሉት።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"በረሃው ውስጥ ህይወት እንዴት ማግኘት እንደምችል አላውቅም" አለ ብላቴናው። "ህይወት መኖሩን አውቃለሁ፤ ሆኖም የት ልፈልገው እንደምችል አላውቅም።"

"ህይወት ህይወትን ይስባል" መለሰለት - አልኬሚስቱ።

ይሄኔ ብላቴናው ነገሩ ገባው። በአለቶቹና በአሸዋው ላይ እየጋለበ ላለው ፈረሱ ልጓሙን አላላለት። አልኬሚስቱ ለግማሽ ሰዓት ያህል የብላቴናውን ፈረስ ተከተለው። የኦሲሱ የቴምርም ሆነ የዘንባባ ዛፎች አሁን ከአይታቸው ውጪ ሆነዋል - ከበላያቸው ያለችውን ግዙፍ ጨረቃና በበረሃው አለቶች ላይ የሚንጸባረቀው ብርማ ብርሃን ብቻ ናቸው የሚታዩዋቸው። በድንገት፣ ያለ ምንም ግልጽ ምክንያት የብላቴናው ፈረስ ዝግ ብሎ መጓዝ ጀመረ።

"እዚህ ህይወት አለ" አለው ብላቴናው አልኬሚስቱን። "እኔ የበረሃውን ቋንቋ አላውቀውም፣ ፈረሴ ግን የህይወትን ቋንቋ ያውቃል።"

ከፈረሶቻቸው ወረዱ፤ አልኬሚስቱ ምንም አልተናገረም። በዝግታ እየተራመዱ አለቶቹን ፈተሹ። አልኬሚስቱ ድንገት ቆመና ወደ መሬት አጎነበሰ። ድንጋዮቹ መሐል የሆነ ጉድጓድ አለ። አልኬሚስቱ እጁን፣ ከዚያም እስከ ክርኑ ድረስ፣ ቀጥሎም እስከ ትከሻው ድረስ ወደ ጉድጓዱ አስገባ። እዚያ ጉድጓድ ውስጥ የሆነ ነገር እየተንቀሳቀሰ ነው፤ ለልጁ የሚታዩት የአልኬሚስቱ ዓይኖች ብቻ ናቸው፤ የእነዚህ ዓይኖች እንቅስቃሴ ለብላቴናው የአልኬሚስቱን ጥረት ይነግረዋል። እጁ ደግሞ ጉድጓዱ ውስጥ ካለ የሆነ ነገር ጋር እየታገለ ይመስላል። ከዚያም ብላቴናውን ባስደነቀው እንቅስቃሴ እጁን አወጣና ፈንጠር አለ። በእጁ የእባብ ጭራ ይዟል።

ብላቴናው ከአልኬሚስቱ ራቅ ብሎ ፈንጠር አለ፤ እባቡ የበረሃውን ጸጥታ በሚያሰማው የቁጣ ድምጽ ረብሾ በኃይል ታገለው። በደቂቃ ሰውን መግደል የሚችል መርዝ የሚተፋ ኮብራ ነው።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"መርዙን ተጠንቀቀው" አለ ብላቴናው። ምንም እንኳን አልኬሚስቱ እጁን ጉድጓድ ውስጥ ያስገባና፣ ያለጥርጥር ተነድፎ ቢሆንም ሁኔታው የቀዘቀዘ ነበር። "የአልኬሚስቱ እድሜ ሁለት መቶ አመት ነው" ብሎ ነግሮት ነበር እንግሊዙ። መቼም ስለ የበረሃው እባቦች ምን ማድረግ እንዳለበት አይጠፋውም።

ባልንጀራው ወደ ፈረሱ ሄዶ ሰይፉን ሲያወጣ ብላቴናው ተመለከተው። በስለቱም አሸዋው ላይ አንድ ክብ ሰራና እባቡን እዚያ ውስጥ አስቀመጠው። እባቡ ወዲያውኑ ዘና አለ።

"አታስብ" አለ አልኬሚስቱ። "ከክቡ አይወጣም። በረሃው ውስጥ ህይወት አግኝተሃል፤ ይህ ነው የሚያስፈልገኝ ንግር።"

"ለምንድነው ያን ያህል አስፈላጊ የሆነው?"

"ምክንያቱም ፒራሚዶቹ በበረሃው የተከበቡ ናቸው።"

ብላቴናው ስለፒራሚዶቹ ማውራት አልፈለገም። ከፍቶታል፤ ከትናንት ምሽት ጀምሮ ሐዘን እየተሰማው ነው። ሃብቱን ፍለጋውን ሊቀጥል ነው ማለት ፋጡማን ሊተዋት ነው ማለት ነው።

"የበረሃውን መንገድ እመራሃለሁ" አልኬሚስቱ ተናገረ።

"ኦሲሱ ውስጥ መቆየት እፈልጋለሁ" መለሰ ብላቴናው።

"ፋጡማን አግኝቻለሁ፤ ለእኔ ደግሞ እሷ ከድብቅ ሃብት ትበልጥብኛለች።"

"ፋጡማ የበረሃው ሴት ናት" አለ አልኬሚስቱ። "ወንዶች ለመመለስ ሲሉ ርቀው መሄድ እንዳለባቸው ታውቃለች። በዚያ ላይ እሷ አዱኛዋን



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

አገኝታለች - አንተን። አሁን ደግሞ አንተ የምትፈልገውን ነገር ታገኝ ዘንድ ትመኛለች።"

"እኔ ለመቅረት ብወስንስ?"

"ምን እንደሚፈጠር ልንገርህ። የኦሲሱ አማካሪ ትሆናለህ። ብዙ በጎችና ብዙ ግመሎችን መግዛት የሚያስችሉ ወርቆች ይኖሩሃል። ፋጡማን ታገባታለህ፤ ለአንድ ዓመት ያህል ሁለታችሁም ደስተኞች ትሆናላችሁ። በረሃውን መውደድ ትጀምራለህ፤ ሃምሳ ሺውንም የዘንባባ ዛፎች አንድ በአንድ ታውቃቸዋለህ። ዓለም ሁልጊዜም እንዴት እንደሚለዋወጥ ያሳዩህ ዘንድ ሲያድጉ ታያቸዋለህ። ንግሮችን የመረዳት ችሎታህም እየተሻሻለ ይሄዳል፤ ምክንያቱም በረሃው እዚህ መምህራን ካሉ ሁሉ የበለጠ ምርጥ መምህር ነው።

"በሁለተኛው ዓመት ስለ ድብቅ ሐብትህ ታስታውሳለህ። ንግሮቹ ስለ እሱ ደጋግመው ቢነግሩህም ችላ ልትላቸው ትሞክራለህ። እውቀትህን ለኦሲሱና ለነዋሪዎቹ ደህንነት ታውለዋለህ። የጎሳው መሪዎች የምትሰራውን ያደንቁልሃል። ግመሎችህም ብልጽግናና ሥልጣንን ያመጡልሃል።

"በሶስተኛው ዓመት ንግሮቹ ስለ ሐብቱና ስለ እጣፈንታህ መናገራቸውን ይቀጥላሉ። አንተ በየምሽቱ ኦሲሱ ውስጥ መዟዟር ታበዛለህ፤ ፋጡማ ደግሞ ከፍለጋህ ያደናቀፈችህ እሷ እንደሆነች ስለሚሰማት ደስታ ይርቃታል። ሆኖም ትወዳታለህ፤ እሷም ፍቅሯን መልሳ ትሰጥሃለች። እሷ እንደ በረሃ ሴትነቷ ባሏን መጠበቅን ስለምታውቅ እዚሁ ቅር ብላ እንዳልጠየቀችህ ታስታውሳለህ። ስለዚህም አትወቅሳትም። ነገር ግን ምናልባት መሄድ እችል ይሆናል ብለህ በማሰብ ብዙ ጊዜ በበረሃው አሸዋ ላይ መለስ ቀለስ ትላለህ... ለፋጡማ ያለህን ፍቅር ይበልጥ ልትተማመንበት



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ስለመቻልህ እያሰብክ። ምክንያቱም አሲሱ ላይ የሚያቆይህ ፈጽሞ ተመልሼ ባልመጣስ የሚል ስጋትህ ነው። በዚህ ጊዜ ንግሮቹ ድብቅ ሃብትህ ለዘላለም ተቀብሮ መቅረቱን ይነግሩሃል።

"ከዚያ በአራተኛው አመት፣ ንግሮቹ ስለተውካቸው ይተዉሃል። የጎሳ መሪዎቹም ይህን ይረዱና፣ ከአማካሪነት ስልጣንህ ያስነሱሃል። ያኔ ግን የብዙ ግመሎችና ከፍተኛ መጠን ያለው ንብረት ባለቤት የሆነ ከበርቴ ነጋዴ ትሆናለህ። በቀረው ህይወትህ እጣፈንታህን አለመከተልህና አሁን ለመጀመርም መዘግየትህ እየታወቀህ ትኖራለህ።

"ፍቅር አንድን ሰው እጣፈንታውን ከመከተል እንደማያግደው መገንዘብ አለብህ። ፍለጋውን ከተወው፣ ፍቅሩ ድሮም እውነተኛ ፍቅር... የሁለንታን ቋንቋ የሚናገር ፍቅር አልነበረም ማለት ነው።"

አልኬሚስቱ አሸዋው ላይ የሳለውን ክብ አጠፋው፣ እባቡ ወደ አለቶቹ ተስቦ ገባ። ብላቴናው ሁልጊዜም ወደ መካ መጓዝ የሚፈልገውን የክሪስታል ነጋዴ፣ አልኬሚስቱን ፍለጋ የመጣውንም እንግሊዝ አሰባቸው። በበረሃው የምታምነውንም ሴት አሰባት። ወደ አፈቀራት ሴት ያመጣውንም በረሃም አሻግሮ ተመለከተው።

በየፈረሶቻቸው ተቀመጡ፣ አሁን ወደ አሲሱ በሚመልሳቸው መንገድ አልኬሚስቱን የሚከተለው ብላቴናው ሆነ። ነፋሱ የአሲሱን ድምጾች ተሸክሞ አመጣላቸው፣ ብላቴናው የፋጡማን ድምጽ ነጥሎ ለመስማት ሞከረ።

በዚህ አንድ ኮብራ በክብ መስመር ውስጥ ባየበት ምሽት ግን፣ ትከሻው ላይ ገጼ አሞራ አስቀምጦ የሚጋልበው አስገራሚ ፈረሰኛ ስለፍቅርና ስለድብቅ ሃብት፣ ስለ በረሃው ሴቶችና ስለ ብላቴናው እጣ ፈንታ አውርቶለታል።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"አብሬህ እሄዳለሁ" አለ ብላቴናው። ወዲያውኑም በልቡ ሰላም ተሰማው።

"ነገ ጀንበር ከመውጣቷ በፊት እንነሳለን" ነበር የአልኬሚስቱ ብቸኛ ምላሽ።

* * *

ብላቴናው እንቅልፍ ባይኑ ሳይዞር አደረ። ጎህ ከመቅደዱ ከሁለት ሰዓታት በፊት፣ ድንኳኑ ውስጥ ከተኙት ልጆች አንዱን ቀስቅሶ፣ የፋጡማን መኖሪያ ጠየቀው። ወደ እርሷ ድንኳን ሲደርሱ ብላቴናው ለልጁ አንድ በግ ለመግዛት የሚበቃውን ያህል ወርቅ ሰጠው።

ከዚያም ይህንኑ ጓደኛውን ፋጡማ ወደተኛችበት ድንኳን ሄዶ፣ ቀስቅሶ፣ እየጠበቃት መሆኑን እንዲነግርለት ጠየቀው። ወጣቱ አረብም እንደ ተጠየቀው በማድረጉ ሰሌላ በግ መግዣ የሚበቃው ወርቅ ተሰጠው።

"አሁን ለብቻችን ተወን" አለው ብላቴናው አረቡን፣ አረቡም የኦሲሱን አማካሪ በመርዳቱ ኩራት እየተሰማው እንዲሁም በጎች ለመግዛት የሚያስችለው በቂ ገንዘብ በማግኘቱ እየተደሰተ ወደ እንቅልፉ ተመለሰ።

ፋጡማ በድንኳኑ መግቢያ ብቅ አለች። ሁለቱ ወደ ዘንባባዎቹ ሄዱ። ብላቴናው ይሄ ድርጊታቸው ትውፊቱን መጣስ መሆኑን ቢያውቅም፣ አሁን ያ አሳሳቢ አይደለም።

"መሄዴ ነው" አላት። "እንደምመለስ እንድታውቂልኝ እፈልጋለሁ። አፈቅርሻለሁ፣ ምክንያቱም..."



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ተወው" ፋጡማ አቋረጠችው። "አንድ ሰው የሚፈቀረው ስለተፈቀረ ብቻ ነው። ለማፍቀር ምክንያት አያስፈልገውም።"

ብላቴናው ግን ቀጠለ፤ "ህልም አየሁ፤ ከንጉስም ተገናኘሁ። ክሪስታል ሸጥኩ፤ በረሃውንም አቋረጥኩ። ጎሳዎቹ ጦርነት በማወጃቸው ምክንያት ደግሞ፣ አልኬሚስቱን ፍለጋ ወደ ውሃው ጉድጓድ ሄድኩ። ስለዚህም የማፈቅርሽ መላው የሁለንታ አካላት አንቺን አገኝሽ ዘንድ ስለረዱኝ ነው።"

ተቃቀፉ። አንዳቸው አንዳቸውን ሲነኩ የመጀመሪያቸው ነው።

"እመለሳለሁ" አለ ብላቴናው።

"ከዚህ በፊት በረሃውን በናፍቆት እመለከተው ነበር" አለች ፋጡማ። "አሁን ግን በተስፋ ነው የማየው። አንድ ቀን አባቴ ሄደ፤ ሆኖም ለእናቴ ነው የተመለሰላት፤ ከዚያ ጊዜ ወዲህ ሁል ጊዜም ተመልሶ ይመጣል።"

ሌላ ምንም አልተነጋገሩም። በዘንባባዎቹ ውስጥ ጥቂት ተራመዱ፣ ከዚያም ብላቴናው ድንኳኗ ደጃፍ ላይ ትቷት ሄደ።

"እመለሳለሁ፤ ልክ አባትሽ ለእናትሽ እንደተመለሱላቸው" አላት።

የፋጡማ አይኖች በእንባ እንደተሞሉ አየ።

"እያለቀስሽ ነው?"

"እኔ የበረሃ ሴት ነኝ" አለች ፊቷን ቀለስ እያደረገች። "ከሁሉም በላይ ግን ሴት ነኝ።"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ፋጡማ ወደ ድንኳኗ ተመለሰች፤ የቀን ጸሃይ በወጣች ጊዜም ለዓመታት ያከናወነቻቸውን የእለት ስራዎቿን ልትሰራ ወጣች። ነገሩ ሁሉ ግን ተቀይሯል። ብላቴናው ከእንግዲህ እሲሱ ውስጥ አይኖርም፤ እሲሱም ለትናንት ብቻ የነበረው ትርጉም ከእንግዲህ አይኖረውም። ከእንግዲህ ወዲያ ሃምሳ ሺ የዘንባባ ዛፎችና ሶስት መቶ የውሃ ጉድጓዶች ያሉት፣ መናኞች ከረጅም ጉዟቸው እረፍ የሚሉበት መዳረሻ ሥፍራ መሆኑን ያበቃል። ከዚህ ቀን ጀምሮ እሲሱ ለፋጡማ እና ይሆናል።

ከዚያ ቀን ጀምሮ በረሃው ነው ተፈላጊ የሚሆነው። በየእለቱ ታየዋለች፤ በሃብት ፍለጋ ጉዞው ብላቴናው የትኛዋን ኮከብ እንደሚከተልም ትገምታለች። የከናፍሯን መሳም በነፋሱ ትልክለታለች፤ ነፋሱ የብላቴናውን ፊት ዳስሶ እሷ በህይወት ስለመኖሯ እንደሚነግረው ተስፋ ስለምታደርግ።

ሀብቱን ፍለጋ የወጣን ደፋር የምትጠብቅ ሴት ስለመሆኗ ይነግረዋል። ከዚያ ቀን ጀምሮ በረሃው ለእሷ አንድን ነገር ብቻ የሚወክል ይሆናል፦ የብላቴናውን የመመለስ ተስፋን።

* * *

"ትተኸው ስለመጣኸው ነገር አታስብ" አለው አልኬሚስቱ ብላቴናውን፣ በበረሃው አሸዋ ላይ የፈረስ ጉዟቸውን እንደጀመሩ። "ሁሉም ነገር በሁለንታ ነፍስ ላይ ተከትቧል፤ በዚያም ላይ ለዘለዓለም ይኖራል።"

"ወንዶች ከመሔድ ይልቅ ስለመመለስ ያልማሉ" አለ ብላቴናው። ከበረሃው ዝምታ ጋር መልሶ ተላምዷል።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"አንድ ሰው የሚያገኘው ነገር ከንጹህ ቁስ የተሰራ ከሆነ መቼም አይበላሽም። እናም አንድ ሰው ሁሌም ተመልሶ መምጣት ይችላል። ያገኘኸው እንደ አንድ ኮከብ ፍንዳታ ያለ ቅጽበት ብልጭታ ብቻ ከሆነ፣ ብትመለስም ምንም አታገኝም።"

ሰውየው በልሳነ አልኬሚ ነው የሚያወራው። ብላቴናው ግን ስለፋጡማ መናገሩ መሆኑ ገብቶታል።

ትቶት ስለመጣው ነገር አለማሰብ ከባድ ነው። በረሃው በማያቋርጥ አሰልቺነቱ ብላቴናውን ማለም አስጀመረው። አሁንም ዘንባባዎቹ፣ የውሃ ጉድጓዶቹና የሚወዳት ሴት መልክ ይታየዋል። እንግሊዙ በቤተሙከራው ሲሞክር፣ አስተማሪነቱን ያልተገነዘበው ግመል ነጂም ይታየዋል። አልኬሚስቱ ፍቅር ይዞት አያውቅ ይሆናል ብሎ አሰበ - ብላቴናው።

አልኬሚስቱ ገዴውን ትከሻው ላይ እንዳደረገ ከፊት ለፊቱ ይጋልባል። ወፉ የበረሃውን ቋንቋ በደንብ ያውቀዋል፤ እናም በቆሙ ቁጥር ለአደን ይበራል። በመጀመሪያው ቀን ጥንቸል ይዞ ተመለሰ፤ በሁለተኛው ደግሞ ሁለት ወፎችን።

ምሽት ላይ መኝታቸውን አነጣጠፉና እሳቶቻቸውን አዳፈኗቸው። የበረሃው ምሽቶች ቀዝቃዛ ከመሆናቸውም ባሻገር የጨረቃዋ መጠን በተቀያየረ ቁጥር እየጨለሙ፣ እየጨለሙ እየመጡ ነው። በጎሳዎቹ መካከል ያለው ጦርነት እንዳያገኛቸው የሚሏቸውን ማስጠንቀቂያዎች ብቻ እየተነጋገሩ ለሳምንት ተጓዙ። ጦርነቱ ቀጥሏል፤ አንዳንዴም ነፋሱ የደሙን ሽታ ተሸክሞ ይመጣል። በአቅራቢያቸው ውጊያዎች ሲካሄዱ ነበር፤ ነፋሱም የብላቴናው ዓይኖች ልብ ያላሏቸውን ነገሮች ያሳየው ዘንድ የንግሮች ቋንቋ አብሮት መኖሩን አስታወሰው።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

በሰባተኛው ቀን አልኬሚስቱ ከወትሮው ቀደም ብሎ ለማረፍ ወሰነ። ገጼው ግዳይ ለመጣል በረረ፤ አልኬሚስቱ ደግሞ የውሃ ኮዳውን ለብላቴናው ሰጠው።

"ጉዞህን ወደ ማጠናቀቁ ተቃርበሃል" አለ አልኬሚስቱ። "እንኳን እጣ ፈንታህን ለመከተል በቃህ።"

"አንተ ግን ይህን ሁሉ መንገድ ስንመጣ ምንም አልነገርከኝም" አለው ብላቴናው። "ከምታውቃቸው ነገሮች አንዳንዶቹን የምታስተምረኝ መስሎኝ ነበር። ከጥቂት ጊዜያት በፊት ስለ አልኬሚ የተጻፉ መጻሕፍት ካሉት ሰው ጋር በረሃው ውስጥ ስጓዝ ነበር። ሆኖም ከመጻሕፍቱ አንድም ነገር መማር ሳልችል ቀረሁ።"

"መማሪያ መንገዱ አንድ ብቻ ነው" መለሰ አልኬሚስቱ። "ተግባር ብቻ። ማወቅ የሚያስፈልግህን ነገር ሁሉ የተማርከው በጉዞህ አማካይነት ነው። መማር የሚያስፈልግህ አንድ ሌላ ነገር አለ።"

ብላቴናው ምን እንደሆነ ማወቅ ፈለገ፤ አልኬሚስቱ ግን ገጼውን ፍለጋ አድማሱን እየቃኘ ነው።

"ለምን አልኬሚስት ተባልክ?"

"ስለሆንኩ ብቻ ነዋ!"

"ሌሎች አልኬሚስቶች ወርቅ መስራት ፈልገው የማይሳካላቸው በምን ምክንያት ነው?"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"የሚፈልጉት ወርቅ ብቻ ስለሆነ ነው" ባልንጀራው መለሰ። "እጣ ፈንታቸውን ሊኖሩት ሳይፈልጉ፣ የእጣፈንታቸውን ድብቅ ሃብት ፍለጋ ይወጣሉ።"

"ላውቀው የሚገባው ሌላ ነገር ምንድነው?" ብላቴናው ጠየቀ። አልኬሚስቱ ግን አድማሱን መመልከቱን ቀጠለ። በመጨረሻም ገጼ አምራው ምግባቸውን ይዞ መጣ። ነበልባሉን ከሰዎች እይታ ለመሰወር ጉድጓድ ቆፈሩና እሳት አያያዙ።

"አልኬሚስት የሆንኩት አልኬሚስት በመሆኔ ነው" አለ ምግቡን እያዘጋጀ። "ሳይንሱን የተማርኩት ከአያቴ ነው፤ እሱ ደግሞ ከአባቱ... እንዲህ እያለ እስከ ፍጥረተ አለም ድረስ ይሄዳል። በነዚያ ጊዜያት ዓቢዩ ሥራ በኤመራልድ ላይ ብቻ ነበር ሊጻፍ የሚችለው። ሰዎች ግን ቀላል ነገሮችን ማጣጣልና አጫጭር ጽሁፎችን፣ አንድምታዎችን፣ እንዲሁም ፍልስፍናዊ ምርምሮችን መጻፍ ጀመሩ። እነሱ ከፊተኞቹ የተሻለ ዘዴ እንደሚያውቁም ይሰማቸው ጀመር። ሆኖም የኤመራልዱ ጽላት ዛሬም ህያው ነው።"

"የኤመራልዱ ጽላት ላይ ምንድነው የተጻፈው?" ብላቴናው ማወቅ ፈለገ።

አልኬሚስቱ አሸዋው ላይ መሳል ጀመረና፣ ሥዕሉን አምስት ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ አጠናቀቀ። እሱ እየሳለ እያለ ብላቴናው ስለ አረጋዊው ንጉስና ያን ቀን ስለተገናኙባት ስፍራ አስታወሰ፤ ገጠመኙ ከብዙ ዓመታት በፊት ያጋጠመው ዓይነት ሆኖበታል።

"የኤመራልዱ ጽላት ላይ የተጻፈው ይሄ ነው" አለ አልኬሚስቱ እንደጨረሰ።

"ኮድ ነው" አለ ብላቴናው በትንሹ እየተበሳጨ። "የእንግሊዙ መጻሕፍት ውስጥ ያየሁትን ይመስላል።"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"አይመስልም" አልኬሚስቱ መለሰ። "የእነዚያን ጭልፊቶች በረራ ነው የሚመስለው፤ በአመክንዮ ብቻ ሊረዱት አይቻልም። የኤመራልዱ ጽላት ወደ ሁለንታ ነፍስ በቀጥታ መግቢያ ነው።

"ጠቢባን ይሄ ዓለም የገነት ቅጂ መሆኑን ይገነዘባሉ። የዚህ ዓለም ህልውና፣ ፍጹም የሆነ ዓለም ህልው ለመሆኑ ማረጋገጫ ነው። እግዚአብሔር ይህንን ዓለም የፈጠረው፣ ሰዎች መንፈሳዊ አስተምህሮቶቹንና ድንቅ ጥበቡን በሚታዩ ነገሮች አማካይነት መረዳት ይችሉ ዘንድ ነው። ለዚህ ነው በተግባር የምነግርህ።"

"የኤመራልዱን ጽላት መረዳት አለብኝ?" ጠየቀ ብላቴናው።

"የአልኬሚ ቤተሙከራ ውስጥ ብትሆን ኖሮ ይሄ ጊዜ የኤመራልዱን ጽላት መረዳት ትችል ዘንድ ምርምር የምትጀምርበት ትክክለኛ ጊዜ ይሆን ነበር። አንተ ግን በረሃ ውስጥ ነህ። ተነከርበት። በረሃው ዓለምን የምታውቅበትን መረዳት ይሰጥሃል፤ በርግጥ በገጸ-ምድር ላይ ያለ ነገር ሁሉ ይህን ሊያደርግ ይቻለዋል። በረሃውን ማወቅ እንኳን አይኖርብህም፡- ማድረግ የሚጠበቅብህ በአንዲት የአሸዋ ቅንጣት ላይ መመሰጥ ብቻ ነው፤ ከዚያ በእርሷ ውስጥ የሥነፍጥረትን ድንቆች ማየት ትችላለህ።"

"ራሴን በረሃው ውስጥ የምነክረው እንዴት ነው?"

"ልብህን አዳምጥ። ልብህ ከሁለንታ ነፍስ በመምጣቱና አንድ ቀንም ወደዚያው የሚመለስ በመሆኑ ሁሉንም ነገር ያውቃል።"

* * *



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ለሁለት ቀናት ያህል በረሃውን በዝምታ አቋረጡ። በጣም የተፋፋመው ጦርነት ወዳለበት ሥፍራ እየቀረቡ በመሆኑ አልኬሚስቱ የሚጓዘው በጥንቃቄ ነበር። በጉዟቸው ወቅት ብላቴናው ልቡን ለማዳመጥ ሞከረ።

እንዲያ ማድረግ ቀላል አልነበረም፤ በፊት በፊት ልቡ ሁሌም እውነቱን ይነግረው ነበር፤ የበኋላው ግን እውነት አልነበረም። ልቡ ማዘኑን ለሰዓታት የሚነግረው ጊዜ አለ፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ በበረሃው ፀሐይ ስሜታዊ ይሆንና ብላቴናው እንባውን ለመደበቅ እንዲሞክር ያደርገዋል። ስለ ድብቅ ሃብቱ ሲያወራ ምቱ ይፈጥናል፤ የብላቴናው ዓይኖች ማለቂያ የሌላቸው አድማሳት ላይ ሲተከሉ ምቱ ይዘገያል። ሆኖም ልቡ በአልኬሚስቱና በብላቴናው መሐል ጸጥታ በነገሰበት ወቅት እንኳን ዝም አይልም ነበር።

"ልቦቻችንን ማዳመጥ ያለብን ለምንድነው?" ብላቴናው ጠየቀ ማደሪያቸውን ሲያበጃጁ።

"ምክንያቱም፣ ልብህ የትም ይሁን፣ ሀብትህን የምታገኘው እዚያ በመሆኑ ነው።"

"ልቤ ግን ተረብሿል" አለ ብላቴናው። "የራሱ ህልሞች አሉት፤ ስሜታዊ ይሆናል፤ ደግሞም አንድ የበረሃ ሴት አፍቃሪ ሆኗል። ስለ እሷ ሳስብ ልቤ ስለራሴ እየጠየቀኝ ብዙ ሌሊቶችን አፍጥጬ አነጋለሁ።"

"ጥሩ ነው። ልብህ ሕያው ነው። የሚልህን ማዳመጥህን ቀጥል።"

* * *

በተከታዮቹ ቀናት፣ ሁለቱ ተጓገች በአያሌ የታጠቁ ተዋጊዎች አጠገብ አለፉ፤ ሌሎቹንም ከአድማሱ ባሻገር ተመለከቱዋቸው። የብላቴናው ልብ ስለ



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ፍርሃት መናገር ጀመረ። ፍስጋ ወጥተው ስላልተሳካላቸው ሰዎች የሚናገሩ ታሪኮችን ነገረው።

አንዳንድ ጊዜ ሀብቱን ሳያገኝ ስለመቻሉ፣ ወይም በረሃው ውስጥ ሲሞት ስለመቻሉ እየነገረ ያስፈራራዋል። በሌላ ጊዜ መርካቱን ለብላቴናው ይነግረዋል፡- ምክንያቱም ፍቅርና ሃብትን አግኝቷልና።

"ልቤ ከሃዲ ነው" አለ ብላቴናው ለአልኬሚስቱ። "ፍለጋዬን እንድቀጥል አይፈልግም።"

"ይሄ የሚመስል ነገር ነው" አልኬሚስቱ መለሰ። "በተፈጥሮው አንተ ህልምህን በመከተልህ ያለህን ነገር ሁሉ እንዳታጣ ይፈራል።"

"ታዲያ ልቤን ማዳመጥ ያለብኝ ለምንድነው?"

"ከእንግዲህ ዝም ልታሰኘው ስለማትችል። የሚነግርህን ነገር እንዳልሰማ ለመምሰል ብትሞክርም እንኳን አንተ ስለህይወትና ስለ ዓለም እያሰብክ ያለኸውን እየደገመልህ ሁሌም ውስጥህ ይኖራል።"

"ከሃዲም ቢሆን አድምጠው ነው የምትለኝ?"

"ክህደት ሳይታሰብ የሚመጣ ነገር ነው። ልብህን በደንብ ካወቅኸው አንተ ላይ ክህደት ሊፈጽምብህ አይችልም። ምክንያቱም ህልሞቹንና ምኞቶቹን፣ እነሱንም እንዴት መያዝ እንዳለብህ ታውቃለህና።

"ከልብህ ማምለጥ አትችልም። ስለዚህ የሚልህን መስማት ይሻላል። ለዚህ ነው ያልተጠበቀ አደጋን ከእንግዲህ የማትፈራው።"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

በረሃውን በማቋረጥ ላይ ሳሉ ብላቴናው ልቡን ማዳመጡን ቀጠለ። ሽወዳዎቹንና ማታለሉቹን ተረድቶ፣ እንዳለ መቀበልንም ለመደ። ፍርሃቱን አጣ፣ ወደ ኦሲሱ የመመለስ ፍላጎቱንም ረሳው፣ ምክንያቱም አንድ ከሰዓት በኋላ ልቡ ደስተኛ መሆኑን ነግሮታል። "አንዳንዴ የምነጫነጨው" አለው ልቡ፣ "የሰው ልብ በመሆኔ ምክንያት ነው፣ የሰዎች ልቦች እንደዚህ ናቸው። ሰዎች በጣም ወሳኝ ህልማቸውን መከተል ይፈራሉ፣ ምክንያቱም ህልማቸው ለእነሱ እንደማይገባ፣ ወይም ሳይሳካላቸው እንደሚችል ይሰማቸዋል። እኛ ልቦቻቸው ደግሞ ለዘላለም ትተውን የራቁትን ተፈቃሪዎቻችንን፣ ጥሩ ሊሆኑ ይችሉ የነበሩ ነገር ግን ያልሆኑ ቅጽበቶችን፣ ወይም ምናልባት የሚገኙ ነገር ግን ለዘላለም አሸዋው ውስጥ ተቀብረው የቀሩ ሀብቶችን እያሰብን እንፈራለን። ምክንያቱም እነዚህ ነገሮች ቢከሰቱ አስከፊ ስቃይ ይደርስብናል።"

*  *  *

"ልቤ እንዳይጎዳ ነው የሚፈራው" ብላቴናው ለአልኬሚስቱ አንድ ምሽት ጨረቃ አልባውን ሰማይ እየተመለከቱ ሳለ ነገረው።

"የመጎዳት ፍርሃት ከመጎዳት ከራሱ የከፋ መሆኑን ለልብህ ንገረው። ህልሙን ፍለጋ የወጣ የትኛውም ልብ ተጎድቶ እንደማያውቅ፣ ምክንያቱም እያንዳንዷ የፍለጋው ሰከንድ ከእግዚአብሔር እና ከዘላለማዊነት ጋር መገናኛ መሆኗንም ንገረው።"

"እያንዳንዷ የፍለጋው ሰከንድ ከእግዚአብሔርና ከዘላለማዊነት ጋር መገናኛ ሰከንድ ናት" ብላቴናው ለልቡ ነገረው። "ከልቤ ድብቅ ሃብቱን ስፈልግ፣ እያንዳንዱ ቀን ብርሃናማ ሆኖልኛል፣ ምክንያቱም እያንዳንዱ ሰዓት የማሳካው ህልም አንድ አካል ነውና። ከልቤ ድብቅ ሃብቱን እየፈለግሁ



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

እያለሁ፣ ለአንድ የበግ እረኛ የማይቻሉ የሚመስሉ ነገሮችን ለመሞከር ወኔ ባይኖረኝ ኖሮ በምንም መንገድ ላውቃቸው የማልችላቸውን ነገሮች በእግረ መንገድ አውቄያለሁ።"

ከዚያ በኋላ ልቡ ሙሉውን ከሰዓት በኋላ ጸጥ ብሎለት ቆየ። ያን እለት ምሽትም ብላቴናው ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወሰደው፤ እንደነቃ ልቡ ከሁለንታ ነፍስ የመጡ ነገሮችን ይነግረው ጀመር። ከሁሉም ደስተኛ ሰዎች ጋር እግዚአብሔር መኖሩን ነገረው። ልክ አልኬሚስቱ እንዳለው ከአንዲት የበረሃው አሸዋ ቅንጣትም ውስጥ ደስተኝነት ሊገኝ መቻሉን ደግሞ ነገረው። ምክንያቱም የአሸዋ ቅንጣትዋ የስነ ፍጥረት ቅጽበት ናት፤ ሁለንታም እሷን ለመፍጠር ብዙ ሚሊዮን ዓመት ፈጅቶበታል። "በምድር ያለ ሰው ሁሉ የሚጠብቀው ድብቅ ሃብት አለው" አለው ልቡ። "እኛ የሰዎች ልቦች ስለ እነዚያ ሃብቶች ብዙ ጊዜ አንናገርም፤ ምክንያቱም ሰዎች እነሱን ፍለጋ የመውጣት ፍላጎት የላቸውም። ስለ ሃብቶቹ ለህፃናት ብቻ እናወራላቸዋለን። ኋላ ላይ ግን ህይወት በራሷ አቅጣጫ ወደ እጣፈንታዋ ትሄድ ዘንድ እንተዋታለን። የሚያሳዝነው በጣም ጥቂቶች ናቸው ወደ እጣፈንታቸውና ወደ ደስተኝነት የሚያደርሳቸውን መንገድ የሚከተሉት። ለአብዛኞቹ ሰዎች አለም አስፈሪ ስፍራ ትመስላቸዋለች፤ በዚህም ምክንያት አለም አስፈሪ ትሆንባቸዋለች።

"ስለዚህም እኛ ልቦች ለስለስ እያልን እንናገራለን። መጮሃችን አልቀረም፤ ሆኖም ቃሎቻችን እንዳይሰሙ እንመኛለን፡- ሰዎች ልቦቻቸውን ባለመከተላቸው ምክንያት እንዲጎዱ አንፈልግም።"

"ሰዎች ህልሞቻቸውን ይከተሉ ዘንድ ልቦቻቸውን መንገራቸውን ለምን ያቋርጣሉ?" ብላቴናው አልኬሚስቱን ጠየቀው።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ምክንያቱም እሱ ነው አንድን ልብ በጣም የሚጎዳው፡፡ ልቦች ደግሞ መጎዳት አይፈልጉም፡፡"

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ብላቴናው ልቡን ተረዳው፡፡ መናገሩን እንዳያቆምም ጠየቀው፡፡ ከህልሙ ቢርቅ ልቡ እንዲጫነውና ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው ጠየቀው፡፡ ብላቴናውም ማስጠንቀቂያውን በሰማ ጊዜ መልእክቱን እንደሚከተለው ማለ፡፡

ምሽት ላይም ይህንን ሁሉ ለአልኬሚስቱ ነገረው፡፡ አልኬሚስቱም የብላቴናው ልብ ወደ ሁለንታ ነፍስ መመለሱን ተገነዘበ፡፡

"እና አሁን ምን ማድረግ ነው ያለብኝ?" ብላቴናው ጠየቀው፡፡

"በፒራሚዶቹ አቅጣጫ ቀጥል" አለ አልኬሚስቱ፡፡ "ለንግሮቹ ትኩረት መስጠትህንም ቀጥል፡፡ ልብህ አሁንም ድብቅ ሀብትህ ያለበትን ሥፍራ ሊያሳይህ አቅም አለው፡፡"

"አሁንም እሱን ብቻ ነው ማወቅ ያለብኝ?"

"አይደለም" አልኬሚስቱ መለሰለት፡፡ "አሁንም ቢሆን ማወቅ ያለብህ ነገር፦ አንድ ህልም እውን ከመሆኑ በፊት የሁለንታ ነፍስ በፍለጋው ወቅት የተገኘውን ትምህርት ይፈትናል፡፡ ይህን የሚያደርገው ክፉ ስለሆነ አይደለም፤ ይልቁንም ህልሞቻችንን ከማሳካት በተጨማሪ፣ ህልማችንን ስንከተል ባገኘናቸው ትምህርቶች የተካንን እንሆን ዘንድ ነው፡፡ ይሄ ነው ብዙዎች ተስፋ የሚቆርጡበት ነጥብ፡፡ ይሄ ነው በበረሃው ቋንቋ እንደምንናገረው፣ ዘንባባዎቹ በአድማሱ ላይ ይታዩት ሲጀምሩ መንገደኛው በጥም የሚሞትበት" ነጥብ ነው፡፡



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"እያንዳንዱ ፍለጋ በጀማሪ እድል ነው የሚጀምረው። እያንዳንዱ ፍለጋ የሚደመደመውም በባለእድሉ በከባድ ፈተና ውስጥ ማለፍ ነው።"

ብላቴናው አንድ የቆየ የአገሩ አባባል ታወሰው። "ሲነጋ ሲል ይጨልማል" ይላል።

* * *

በተከታዩ ቀን የመጀመሪያው ግልጽ የአደጋ ምልክት ታየ። ሶስት የታጠቁ ተዋጊዎች ብላቴናውንና አልኬሚስቱን ቀረቧቸውና ምን እያደረጉ እንደሆነ ጠየቋቸው።

"በገዴ አሞራዬ እያደንኩ ነው" አልኬሚስቱ መለሰ።

"መታጠቅ አለመታጠቃችሁን መፈተሽ ይኖርብናል" አለ ከተዋጊዎቹ አንዱ።

አልኬሚስቱ በዝግታ ከፈረሱ ላይ ወረደ፤ ብላቴናውም እንዲሁ። "ይሄን ሁሉ ገንዘብ የያዝከው ለምንህ ነው?" የብላቴናውን ቦርሳ እየፈተሸ።

"ፒራሚዶቹ ጋር ለመድረስ ስለሚያስፈልገኝ ነው" አለ።

የአልኬሚስቱን ንብረቶች ሲፈትሽ የነበረው ሰው ደግሞ በፈሳሽ የተሞላች ትንሽዬ የክሪስታል ብልቃጥ እና ከዶሮ እንቁላል በትንሹ ከፍ የምትል ቢጫ የጠርሙስ እንቁላል አገኘ።

"እነኚህ ምንድ ናቸው?" ጠየቀው።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"የፈላስፋው ጠጠር እና እድሜ ቀጥል ማየ-ህይወት ናቸው። የአልኬሚስቶች ዓቢይ ሥራዎች ናቸው። ያንን ፈሳሽ የተጎነጨ ሰው በሽታ አይነካውም፤ የዚህ ጠጠር ሽራፊ ደግሞ ማንኛውንም ዓይነት ብረት ወደ ወርቅ ይለውጣል።"

አረቦቹ ሳቁበት፤ አልኬሚስቱም አብሯቸው ሳቀ። በምላሹ ተደንቀው ብላቴናውንም አልኬሚስቱንም ከነሙሉ ንብረታቸው ትተዋቸው አለፉ።

"አብደሃል?" ብላቴናው መሔዳቸውን ተመልክቶ አልኬሚስቱን ጠየቀው። "ለምንድነው እንደዚያ ያደረከው?"

"ከህይወት ቀላል ትምህርቶች አንዱን ላሳይህ ብዬ ነው" አልኬሚስቱ መለሰለት። "ታላላቅ ሃብቶችን ይዘህ ለሰዎች ብትነግራቸው የሚያምንልህ ሰው በቀላሉ አታገኝም።"

የበረሃ ጉዟቸውን ቀጠሉ። እያንዳንዱ ቀን ባለፈ ቁጥር የብላቴናው ልብ ዝምታ እየጨመረ መጣ። ከእንግዲህ ስላለፉም ሆነ ስለሚመጡ ነገሮች የማወቅ ፍላጎት የለውም፤ በበረሃው ለመመሰጥና ከብላቴናው ጋር ከሁለንታ ነፍስ ባህር ለመጠጣት ዝም ብሏል። ብላቴናውና ልቡ ጓደኛሞች ሆነዋል፤ አሁን አንዳቸው ሌላቸውን የመክዳት አቅም የላቸውም።

ልቡ የሚያናግረው ብላቴናውን ለማነቃቃትና ብርታትን ሲሰጠው ብሎ ነው፤ ምክንያቱም የበረሃው የዝምታ ቀናት አሰልቺዎች ናቸው። ልቡ ለብላቴናው ስለጠንካራ ጎኖቹ ይነግረዋል፡- በጎቹን እስከመተውና እጣፈንታውን እስከመከተል ስላደረሰው ወኔው፣ እንዲሁም ክሪስታል መደብሩ ውስጥ ስለነበረው ጥንካሬውም ይነግረዋል።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ልቡ ብላቴናው ልብ ያላለውንም ነገር ነግሮታል፡- አስግተውት ስለነበሩ ግን ደግሞ ስላላስተዋላቸው አደጋዎች፡፡ አንድ ጊዜ ብላቴናው ከአባቱ የወሰደውን ጠብመንጃ ራሱን እንዳያቆስል ብሎ ልቡ እንደደበቀበት አወራለት፡፡ ብላቴናው በጣም ታሞ መስከ ላይ ወደ ላይ ሲለው ቆይቶ ከባድ እንቅልፍ የተኛበትን ቀንም አስታወሰው፡፡ ከፊቱ በርቀት ብላቴናውን ገድለው በጎቹን ሊዘርፉት መንገድ ላይ የሚጠብቁት ሁለት ሌቦች ነበሩ፡፡ እሱ ባጠገባቸው ሳያልፍ በመቅረቱ ግን መንገድ ቀይሮ የሔደ መስሏቸው ጉዟቸውን ቀጥለዋል፡፡

"የሰው ልቡ ሁሌም ረዳቱ ነው?" ብላቴናው አልኬሚስቱን ጠየቀው፡፡

"እጣፈንታቸውን እውን ለማድረግ የሚጣጣሩ ሰዎች ልቦች ከሆኑ ብዙ ጊዜ ረዳቶች ይሆናሉ፡፡ ሆኖም ህፃናትን፣ ሰካራሞችንና አዛውንቶችንም ጭምር ልቦቻቸው ይረዱዋቸዋል፡፡"

"ይሄ ማለት ፈጽሞ አደጋ አያጋጥመኝም ማለት ነው?"

"ልብህ የሚችለውን ያደርግልሃል ማለት ብቻ ነው" አለ አልኬሚስቱ፡፡

በከሰዓት በኂላ ጉዟቸውን ከተዋጊ ጎሳዎች በአንደኛው ሠፈር አለፉ፡፡ በሰፈሩ ጥጋጥግ ቆንጆ ቆንጆ ነጫጭ ጀለቢያ የለበሱ አረቦች ከነሙሉ ትጥቃቸው ዝግጁ ሆነው ይታያሉ፡፡ ሰዎቹ ሁቃህዎቻቸውን እያጨሱ የፍልሚያ ገድሎቻቸውን ያወራሉ፡፡ ለሁለቱ ተጓገኞች ትኩረት የሰጣቸው የለም፡፡

"አደጋ የለም" አለ ብላቴናው፣ ሰፈሩን እያለፉ ሲሄዱ፡፡

አልኬሚስቱ የተናደደ መሰለ፡- "በልብህ ተማመን፣ ነገር ግን በረሃ ውስጥ መሆንህን አትዘንጋ፡፡ ሰዎች እርስበርሳቸው ሲዋጉ፣ የሁለንታ ነፍስ



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

የፍልሚያውን ጩኸት መስማት ትችላለች:: ከጸሐይ በታች ባሉ ነገሮች ጦስ ከሚመጡ ችግሮች የሚያመልጥ የለም::"

ሁሉም ነገሮች አንድ ናቸው፣ ሲል አሰበ ብላቴናው:: ከዚያም በረሃው የአልኬሚስቱን ንግግር ትክክለኛነት ማሳየት የፈለገ ይመስል፣ ሁለት ፈረሰኞች ከኋላቸው መጡባቸው::

"ከዚህ ማለፍ አትችሉም" አለ አንደኛው:: "ጎሳዎቹ የሚፋለሙበት ሥፍራ ላይ ነው ያላችሁት::"

"ርቂ አልሔድም" አልኬሚስቱ መለሰለት፣ የፈረሰኛው ዓይኖች ላይ አይኖቹን ተክሉ:: ለጥቂት ጊዜ መሐላቸው ዝምታ ሰፈነ፣ ከዚያም አልኬሚስቱና ብላቴናው ጉዟቸውን ይቀጥሉ ዘንድ ተስማሙ::

ብላቴናው የሃሳብ ልውውጡን በአድናቆት ተመልክቷል:: "እነዚያ ፈረሰኞች ላይ በአስተያየትህ ተጽእኖ አሳረፍክባቸው" አለ::

"ዓይኖችህ የነፍስህን ብርታት ያሳያሉ" አልኬሚስቱ መለሰ::

እውነት እኮ ነው ብሎ አሰበ ብላቴናው:: በጦር ሰፈሩ ውስጥ ከበርካቶቹ መሳሪያ የታጠቁ ሰዎች መሐል ዓይኖቹን ተክሉ ሁለቱን የሚመለከታቸው አንድ ሰው እንደነበረ አስተውሏል:: ሩቅ ከመሆኑ የተነሳ መልኩን መለየት እንኳን አይቻልም:: ብላቴናው ግን ያ ሰው እሱንና አልኬሚስቱን ይመለከታቸው እንደነበረ እርግጠኛ ነው::

መጨረሻ ላይ በአድማሱ ላይ የተዘረጉትን ተራሮች እንዳለፉ ፒራሚዶቹ ጋር ለመድረስ የሁለት ቀን መንገድ ብቻ እንደቀራቸው ነገረው::



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"የመሰያያ ጊዜያችን ከደረሰ" አለ ብላቴናው፣ "ስለ አልኬሚ አስተምረኝ::"

"ስለ አልኬሚ እኮ አሁንም ታውቃለህ:: አልኬሚ የሁለንታን ነፍስ ዘልቆ የመግባትና ላንተ ብቻ ተብሎ የተቀመጠልህን ሀብት የማግኘት ነገር ነው::"

"አአይ:: እንደሱ ማለቴ እኮ አይደለም:: እኔ የተናገርኩት እርሳስን ወደ ወርቅ ስለመለወጥ ነው::"

አልኬሚስቱን የበረሃውን ዓይነት ዝምታ ዋጠው፤ ለብላቴናው ምላሹን የሰጠው ሊመገቡ ጉዟቸውን ባቋረጡ ጊዜ ነበር::

"በህዋው ላይ ያለ ነገር ሁሉ በለውጥ ሂደት የተገኘ ነው" አለው:: "እናም ለጠቢባን፣ ወርቅ ከሌሎቹ ብረቶች በበለጠ አዝጋሚ የለውጥ ሂደት የተገኘ ብረት ነው:: ለምን ብለህ አትጠይቀኝ፤ ለምን እንደሆነ አላውቅም:: የማውቀው ትውፊቱ ሁሌም ትክክል መሆኑን ነው::

"ሰዎች የጠቢባኑን ቃላት ተረድተዋቸው አያውቁም:: ስለዚህም ወርቅ አዝጋሚ የለውጥ ትእምርት በመሆን ፈንታ የግጭት መነሻ ሆነ::"

"በንግሮች የሚነገሩ ብዙ ቋንቋዎች አሉ" አለ ብላቴናው:: "የግመል ጩኸት ከጩኸትነት ያለፈ እንዳልሆነ የሚሰማኝ ጊዜ ነበረ:: ከዚያ የአደጋ ማስጠንቀቂያ ሆነ:: በመጨረሻ ደግሞ ተመልሶ ጩኸት ብቻ ሆነብኝ::"

ንግግሩን ተወው:: አልኬሚስቱ ቀድሞውኑ ይህን ሁሉ ሳያውቀው አልቀረም::

"እውነተኛ አልኬሚስቶችን አውቃለሁ" አልኬሚስቱ ቀጠለ:: "ራሳቸውን በአብያተ ሙከራቸው ውስጥ ዘግተው ወርቅ እንደተለወጠው ለመለወጥ



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ይሞክሩ ነበር። በኋላ የፈላስፋውን ጠጠር አገኙ፤ ምክንያቱም አንድ ነገር ወደ ሌላ ቅርጽ ሲለወጥ በዙሪያው ያሉ ነገሮች ሁሉም አብረውት ይለወጣሉ።

"ሌሎች በአጋጣሚ ጠጠሩን አገኙት። ቀድሞውኑም ተሰጥኦው ነበራቸው፤ ነፍሶቻቸውም ከሌሎች ነፍሶች ይልቅ ለእንዲህ ያሉ ነገሮች የተዘጋጁ ነበሩ። ሆኖም ከቁጥር አይገቡም። እጅግ በጣም ጥቂቶች ናቸው።

"ደግሞ ሌሎችም ነበሩ፤ ወርቅ ብቻ የሚፈልጉ። ምስጢሩን በፍጹም አላገኙትም። እርሳስ፣ መዳብ እና ብረት ሊያሳኩት የሚገባ የየራሳቸው እጣ ፈንታ እንዳላቸው ዘንግተዋል። በሌላው እጣ ፈንታ ጣልቃ የሚገባ ማንም ቢሆን የራሱን እጣ ፈንታ ማወቅ እንኳን አይቻለውም።"

የአልኬሚስቱ ቃላት እንደ እርግማን ተስተጋቡ። ከመሬት ላይ አንድ ቅርፊት አነሳ።

"ይሄ በረሃ ባህር ነበር" አለ።

"እኔም አስተውዬዋለሁ" ብላቴናው መለሰ።

አልኬሚስቱ ቅርፊቱን ለብላቴናው እያቀበለው ጆሮው ላይ እንዲያደርገው ነገረው። ልጅ እያለ ብዙ ጊዜ እንደዚህ አድርጎ የባህሩን ድምጽ ሰምቷል።

"ባህሩ እዚህ ቅርፊት ላይ ቀርቷል፤ ምክንያቱም እጣፈንታው ይኸው ነው። በረሃው ተመልሶ በውሃ እስኪሸፈን ድረስም እንደዚህ መሆኑን አይተውም።"

ፈረሶቻቸው ላይ ተቀመጡና በግብጽ ፒራሚዶች አቅጣጫ ጋለቡ።

* * *



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

የብላቴናው ልብ የአደጋ ድምጽ በሰማ ጊዜ ድንበር እየጠለቀች ነበር። ግዙፍ ግዙፍ በሆኑ የአሸዋ ጋራዎች ተከበዋል፤ ብላቴናው እሱም የሆነ ነገር ተሰምቶት እንደሆነ ብሎ አልኬሚስቱን ተመለከተው። አልኬሚስቱ ግን ምንም አይነት አደጋ መኖሩን የተረዳ አይመስልም። ከአምስት ደቂቃ በኋላ ሁለት ፈረሰኞች ከፊታቸው እየጠበቋቸው እንደሆነ ተመለከተ። ለአልኬሚስቱ ምንም ከመናገሩ በፊት ሁለቱ ፈረሰኞች አስር ሆኑ። ከዚያም ከየአሸዋ ጋራዎቹ ሥር ወጥተው አካባቢውን አጥለቀለቁት።

ሙሉ ሰማያዊ ለብሰው በጥምጣማቸው ዙሪያ ጥቁር ቀለበቶችን ያጠለቁ ጎሰኞች ናቸው። ፊታቸው ከአይኖቻቸው በቀር በሰማያዊ ዓይነርግቦቻቸው ተሸፍነዋል።

ገና ከሩቅ ሳይቀር ዓይኖቻቸው የነፍሶቻቸውን ጥንካሬ ያሳያሉ። እኒሁ ዓይኖቻቸው ስለሞትም ይናገራሉ።

* * *

ሁለቱ በቅርብ ወዳለ የጦር ሰፈር ተወሰዱ። አንድ ወታደር ብላቴናውንና አልኬሚስቱን መሪው ከበታቾቹ ጋር ስብሰባ ወደያዘበት ድንኳን አስገባቸው።

"እነኚህ ሰላዮች ናቸው" አለ ከሰዎቹ አንዱ።

"እኛ ተጓዦች ነን" አልኬሚስቱ መለሰ።

"ከሶስት ቀን በፊት በጠላት ጦር ሰፈር ታይታችኋል። እዚያ ካለ አንድ ወታደር ጋር ስትነጋገሩ ነበር።"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"እኔ በረሃውን የምዞር፣ ስለከዋክብት የማውቅ ሰው ነኝ" አለ አልኬሚስቱ። "ስለ ወታደሮቹም ሆነ ስለ ጎሳዎቹ እንቅስቃሴ የማውቀው የለም። እኔ ይህን ወዳጄን መንገድ እየመራሁት ብቻ ነኝ።"

"ወዳጅህ ምንድነው?" የጦር መሪው ጠየቀ።

"አልኬሚስት ነው" መለሰ አልኬሚስቱ። "የተፈጥሮን ኃይሎች መረዳት ይችላል። እጅግ ልዩ የሆነ ኃይሉን ሊያሳያችሁም ይፈልጋል።"

ብላቴናው በዝምታ እና በፍርሃት አዳመጠ።

"ፀጉረ ልውጥ ሰው እዚህ ምን ይሰራል?" ከሰዎቹ ሌላኛው ጠየቀ።

"ለእናንተ ጎሳ ሊያበረክት ገንዘብ አምጥቶላችኋል" አለ አልኬሚስቱ፣ ብላቴናው ከመናገሩ በፊት። የብላቴናውን ቦርሳ ወሰደና የወርቅ መሐልቆቹን ለጦር መሪው ሰጠው።

አረቡ ዝም ብሎ ተቀበለው። ብዙ መሳሪያዎችን ለመግዛት ይበቃዋል።

"አልኬሚስት ምንድነው?" በመጨረሻ ጠየቀ።

"ተፈጥሮንና ዓለምን መረዳት የሚችል ሰው ነው። ከፈለገም ይህን ሰፈር በነፋስ ኃይል ብቻ ማጥፋት ይችላል።"

ሰዎቹ ሳቁ። ከጦርነት ጣጣዎች ጋር ተላምደዋል፤ ነፋስ ገዳይ ሆኖ ሊመታቸው እንደማይችል ያውቃሉ። ሁሉም ግን የልብ ምታቸው ሲፈጥን ተሰማቸው። በረሃኞች እንደመሆናቸው አስማተኞችን ይፈሯቸዋል።

"ሲያደርገው ማየት እፈልጋለሁ" አለ ጦር መሪው።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ሶስት ቀናት ያስፈልጉታል" አልኬሚስቱ መለሰ፡፡

"ኃይሉን ለማሳየት ሲል ብቻ ራሱን ወደ ነፋስነት ይለውጣል፡፡ ካልቻለ ለጎሳዎ ክብር ህይወታችንን እንሰጥዎታለን፡፡"

"የእኔ የሆነውን ነገ[illegible] ሰጡኝ አትችሉም" አለ የጦር መሪው በትምክህተኛነ[illegible] ሰጓጉ[illegible] የጠየቁትን የሶስት ቀናት ጊዜ ሰጣቸው፡፡

ብላቴናው በፍርሃት እየተንቀጠቀጠ ነባር[illegible]ሰቱ ከድንኳኑ ይወጣ ዘንድ አበረታታው፡፡

"መፍራትህን አታሳያቸው" አለ አልኬሚ[illegible] ደፋሮች በመሆናቸው ፈሪዎችን ይንቋቸዋል፡፡"

ብላቴናው ግን መናገር እንኳን አልቻ[illegible]፡፡ መናገር የቻለው በጦር ሰፈሩ መሐል ለመሐል የእግር ጉዞ ካደረጉ [illegible] ነው፡፡ እነሱን ማሰር አስፈላጊ አልነበረም፡- አረቦቹ ፈረሶቻቸውን ብቻ ነው የነጠቋቸው፡፡ እናም አሁንም ዓለሙ ሥፍር ቁጥር የሌላቸውን ቋንቋዎቹን ገለጠ፡- ከቅጽበታት በፊት ማብቂያ የለሽ እና ነፃ የነበረው በረሃ አሁን ሊጥሱት የማይቻል ግንብ ሆነ፡፡

"ያለኝን ሁሉ ሰጠሃቸው!" ብላቴናው ተናገረ፡፡ "ህይወቴን ሙሉ ያጠራቀምኩትን ሁሉ!"

"ብትሞት የምታገኘው ጥቅም ምንድነው?" አልኬሚስቱ መለሰ፡፡ "ገንዘብህ ለሶስት ቀናት ያህል አትርፎሃል፡፡ ብዙ ጊዜ ገንዘብ የሰውን ህይወት አያተርፍም፡፡"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ብላቴናው ግን የጥበብን ቃል መስማትን በጣም ፈርቷል። ራሱን ወደ ነፋስነት እንዴት መለወጥ እንደሚችል አያውቅም። እሱ አልኬሚስት አይደለም!

አልኬሚስቱ ከወታደሮቹ አንዱን ሻይ እንዲመጣለት ጠይቆት ሻዩን የብላቴናው እጅ ላይ አፈሰሰበት። የእፎይታ ማእበል በላዩ ላይ አረፈ፤ አልኬሚስቱም ብላቴናው ያልተረዳቸውን ጥቂት ቃላት አነበበ።

"ለፍርሃትህ እጅህን አትስጥ" አለ አልኬሚስቱ ያልተለመደ ሞገስ ባለው ድምጽ። "ከሰጠህ ከልብህ መነጋገር አትችልም።"

"ያም ሆነ ይህ ራሴን ወደ ነፋስነት እንዴት መለወጥ እንደምችል አላውቅም።"

"ሰው እጣፈንታውን የሚከተል ከሆነ፣ ማወቅ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ያውቃል። ህልምን እንዳይሳካ የሚያደርገው አንድ ብቸኛ ነገር ውድቀትን መፍራት ነው።"

"ውድቀትን አልፈራም። ራሴን ወደ ነፋስነት እንዴት እንደምለውጥ ስለማላውቅ ብቻ ነው።"

"እንደሱ ከሆነ መማር ይኖርብሃል፤ ህይወትህ በእሱ ላይ የሚወሰን ነውና።"

"ባልችልስ?"

"እጣፈንታህን እውን በማድረግ ጉዞህ መሐል ትሞታለህ። ይሄ ደግሞ የእጣፈንታቸውን ምንነት እንኳን ሳያውቁ እንደሚሞቱ ሚሊዮኖች ከመሞት በጣም ይሻላል።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ሆኖም አትጨነቅ" ቀጠለ አልኬሚስቱ። "ብዙ ጊዜ የሞት ፍርሃት ሰዎችን ስለ ህይወቶቻቸው የበለጠ እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል።"

የመጀመሪያው ቀን አለፈ። በጦር ሰፈሩ አቅራቢያ ከባድ ጦርነት ተካሂዶ ስለነበር፣ በርካታ ቁስለኞች ወደ ጦር ሰፈሩ ተመለሱ። ሟቾቹ ወታደሮች በሌሎች ተተኩ፤ ህይወትም እንደነበረችው ቀጠለች። ሞት ምንም ነገር አይለውጥም ሲል አሰበ - ብላቴናው።

"ቆይተህም ልትሞት ትችል ነበር" አለው አንድ ወታደር አንዱን የወገኑን አስከሬን። "ሰላም ከወረደ በኋላ ልትሞት ትችል ነበር። ነገር ግን መቼም ይሁን መቼ መሞትህ አይቀርም ነበር።"

ቀኑ ሲመሽ ብላቴናው ገጼውን ይዞ ወደ በረሃው የሄደውን አልኬሚስቱን ፍለጋ ወጣ።

"አሁንም ራሴን እንዴት ወደ ነፋስነት መለወጥ እንደምችል አልታየኝም" ብላቴናው ደገመለት።

"የነገርኩህን አስታውስ፦ ይህ ዓለም የእግዚአብሔር በዓይን የሚታይ ብቻ ገጽታው ነው። የአልኬሚ ተግባር ደግሞ መንፈሳዊ ፍጽምናን ከቁሳዊው ዓለም ጋር ማገናኘት ነው።"

"ምን እያደረግህ ነው?"

"ገጼ አሞራዬን እየመገብኩ።"

"ራሴን ወደ ነፋስነት መለወጥ ከተሳነኝ መሞታችን ነው" አለ ብላቴናው። "ገጼህን ለምን ትመግበዋለህ?"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"አንተ ትሞት ይሆናል" አለ አልኬሚስቱ። "እኔ ራሴን ወደ ነፋስነት እንዴት መለወጥ እንደምችል አውቃለሁ።"

* * *

በማግስቱ ብላቴናው በጦር ሰፈሩ አቅራቢያ ያለ ማማ ላይ ወጣ። ጠባቂዎቹ ፈቅደውለታል፤ ምክንያቱም ራሱን ወደ ነፋስነት መለወጥ ስለሚችለው አስማተኛ ሰምተዋል፤ እናም ሊጠጉት አልፈለጉም። ምንም ቢያደርግ በረሃውን ማለፍ አይችልም።

የማግስቱን ቀን ሙሉ ከሰዓት በኋላ በረሃውን እየቃኘ እና ልቡን እያደመጠ አሳለፈ። በረሃው ፍርሃቱን እንዳወቀበት ብላቴናው ተረድቷል።

ሁለቱም በአንድ ቋንቋ ነው የሚናገሩት።

* * *

በሳልስቱ የጦር መሪው ከመኮንኖቹ ጋር ስብሰባ ተቀመጠ። አልኬሚስቱን ወደ ስብሰባው ጠራውናም፤ "ራሱን ወደ ነፋስነት የሚለውጠውን ብላቴና እናይ ዘንድ እንሂድ" አለ።

"እንሂድ" አልኬሚስቱ መለሰ።

ብላቴናው ትናንት ወደነበረበት ማማ ወሰዳቸው። ሁሉንም ይቀመጡ ዘንድ ጠየቃቸው።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ትንሽ ጊዜ ይወስዳል" አለ ብላቴናው።

"አንችኩልም" የጦር መሪው መለሰ። "እኛ በረኸኞች ነን።"

ብላቴናው ወደ አድማሱ ተመለከተ። በርቀት ተራሮች አሉ። የአሸዋ ቁልሎች፣ አለቶችና በህይወት መሰንበት መቻል በሚያጠራጥርበት በዚህ በረሃ መኖርን የመረጡ እጽዋት አሉ። ለአያሌ ወራት የተጓዘበት በረሃም አለ፤ ያን ያህል ጊዜ ቢቆይበትም በጣም በትንሹ ነው የሚያውቀው። በዚያ በትንሹ ክፍል እንግሊዙን፣ ሲራራዎችን፣ የጎሳ ጦርነቶች፣ እንዲሁም ሃምሳ ሺ የዘንባባ ዛፎችና ሶስት መቶ የውሃ ጉድጓዶች ያሉትን ኦሲስ አይቷል።

"ዛሬ ከዚህ ምን ትሻለህ?" በረሃው ጠየቀው። "እኔን በማየት ትናንት ያጠፋኸው ጊዜ አልበቃህም?"

"የሆነ ቦታ የምወዳትን ሴት ይዘሃል" አለ ብላቴናው። "ያንተን አሸዋዎች ስመለከት፣ እሷንም እያየኋት ነው። ወደ እሷ መመለስ እፈልጋለሁ፤ እናም ራሴን ወደ ነፋስነት መለወጥ እችል ዘንድ ያንተን እርዳታ እሻለሁ።"

"ፍቅር ምንድነው?" ጠየቀ በረሃው።

"ፍቅር የገዴው ከአሸዋዎችህ በላይ መብረር ነው። በእርሱ ምክንያት አንተ ምንጊዜም ግዳይ ይዞ የሚመለስብህ ለምለም መስክ ነህ። እሱ አለቶችህን፣ ያሸዋ ጋራዎችንና ተራሮችህን ያውቃዋል፤ አንተ ደግሞ ለእርሱ ቸር ነህ።"

"ገዴው መንቆሮች የእኔን የራሴን ቁራሽ ይሸከማሉ" አለ በረሃው። "ለዓመታት ካለችኝ ትንሽ ውሃ እየመገብኩ ስለግዳዩ ሳስብለትና፣ ግዳዩንም የት እንደሚያገኝ ስመራው ኖሬያለሁ። አንድ ቀን የእሱ ግዳይ በገጼ ላይ



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ስለመኖሩ በምደሰትበት ወቅት ገዴው ከሰማይ ተወርውሮ መጥቶ የፈጠርኩትን ይነጥቀኛል፡፡"

"ግን እኮ መጀመሪያውኑ ግዳዩን የፈጠርከው ለዚሁ ነው" ብላቴናው መለሰ፡፡ "ገዴውን ለመመገብ፡፡ ገዴው ሰውን ይመግባል፡፡ ከዚያ ሰው ደግሞ ግዳዩ ተመልሶ የሚበቅልበትን አሸዋህን ይመግባል፡፡ ዓለም እንዲህ ናት፡፡"

"እና ይሄ ነው ፍቅር?"

"አዎን፤ ይሄ ነው ፍቅር፡፡ እሱ ነው ግዳዩን ገዴው፣ ገዴውን ሰው፣ ሰውን ደግሞ በረሃውን የሚያደርገው፡፡ እሱ ነው እርሳሱን ወደ ወርቅ የሚለውጠው፤ ወርቁንም ወደ አፈር የሚመልሰው፡፡"

"የምትናገረው ነገር አልገባኝም" አለ በረሃው፡፡

"ሆኖም ቢያንስ ከአሸዋዎችህ በአንድ ሥፍራ የምትጠብቀኝ ሴት መኖሯ ይገባሃል፡፡ ለዚህም ነው ራሴን ወደ ነፋስነት መለወጥ ያለብኝ፡፡"

በረሃው መልስ ሳይሰጠው ጥቂት ቆየ፡፡

ከዚያም እንዲህ አለው፡- "ነፋሱ መንፈስ ይችል ዘንድ አሸዋዬን እሰጥሃለሁ፣ እኔ ብቻዬን ምንም ሳደርግልህ አልችልም፡፡ ነፋሱን እንዲረዳህ መጠየቅ አለብህ፡፡"

የሆነ ትንፋሽ ይነፍስ ጀመረ፡፡ የጎሳው ጠረኞች እሱ በማያውቀው ቋንቋ እርስ በርሳቸው እየተነጋገሩ ብላቴናውን ከርቀት ያዩታል፡፡

አልኬሚስቱ ፈገግ አለ፡፡



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ነፋሱ ወደ ብላቴናው ቀርቦ ፊቱን ዳሰሰው። ነፋሳት የማያውቁት ነገር የሰምና ብላቴናው ከበረሃው ጋር ያወራውን ነፋሱ አውቆታል። ነፋሳት በመላው አለም ቢነፍሱም እትብቴ የተቀበረበትም ሆነ ለአገሬ አፈር ልብቃ የሚሉበት የትውልድም የሞትም ስፍራ የላቸውም።

"እርዳኝ" አለ ብላቴናው። "አንድ ቀን የማፈቅራትን ሴት ድምጽ ተሸከመህ አምጥተህልኛል።"

"በበረሃና በነፋስ ልሳን መናገርን ማን አስተማረህ?"

"ልቤ" መለሰ ብላቴናው።

ነፋሱ ብዙ ስሞች አሉት። በዚህኛው ክፍለ ዓለም ሲሮኮ ይሉታል - እርጥበትን ከውቅያኖሶቹ ወደ ምሥራቅ ያመጣልና። ልጁ በመጣበት ሩቅ አገር ደግሞ ሌቫንተር ይሉታል - የበረሃውን አሸዋዎችና የሙሮችን የጦርነት ጩኸቶች ይዞ መጥቷል ብለው ያምናሉና። የእርሱ በጎች ይኖሩበት ከነበረው የግጦሽ መስክ ባሻገር የሚኖሩ ሰዎች ነፋሱ ከአንዳሉዚያ ነው የመጣው ይሉ ይሆናል። በእውነቱ ከሆነ ግን ነፋሱ መምጫም መሔጃም የለውም፤ ለዚህም ነው ከበረሃው ይበልጥ ብርቱ የሆነው። አንድ ቀን የሆነ ሰው በረሃው ላይ ዛፎችን ይተክልና በጎችም ያረባ ይሆናል፤ ነፋሱን ግን ፈጽሞ መግራት አይችልም።

"ነፋስን መሆን አትችልም" አለ ነፋሱ። "ሁለታችን በጣም የተለያየን ነገሮች ነን።"

"ይሄ እውነት አይደለም" አለ ብላቴናው። "በጉዞዎቼ የአልኬሚስቶችን ምስጢራት ተምሬያለሁ። በውስጡ ነፋሳት፣ በረሃዎች፣ ውቅያኖሶች፣



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ኮከቦችና በዚህ ሁሉንታ ላይ የተፈጠረው ነገር ሁሉ አሰኝ። ሁላችንም የተፈጠርነው በአንድ እጅ ነው፤ ስለዚህም አንድ ነፍስ ነው ያለን። እንዳንተ መሆን፣ በሁሉም የዓለም ጥግ መድረስ መቻል፣ ባህሮችን ማቋረጥ፣ ሃብቴን የደበቁትን አሸዋዎች መገላለጥና የማፈቅራትን ሴት ድምጽ መሸከም እፈልጋለሁ።"

"በቀደም ከአልኬሚስቱ ጋር ያወራኸውን ሰምቻለሁ" አለ ነፋሱ። "ሁሉም ነገር የየራሱ እጣፈንታ አለው ብሎሃል። ነገር ግን ሰዎች ራሳቸውን ወደ ነፋስነት መለወጥ አይችሉም።"

"ለጥቂት ጊዜያት ብቻ ነፋስ መሆንን አስተምረኝ" አለ ብላቴናው። "ከዚያ እኔና አንተ ሰዎችና ነፋሶች ስላሏቸው ገደብ የለሽ እድሎች ማውራት እንችላለን።"

የነፋሱ ጉጉት ተነሳሳ፤ እንዲህ ያለ ነገር ሊጋጥሞት አያውቅም። ስለ እነዚያ ነገሮች ማውራቱን ቢፈልገውም፣ አንድን ሰው ወደ ነፋስ እንዴት እንደሚለውጥ አያውቅም። ነፋሱ እስካሁን ምን ያህል ነገሮች እንዴት ማድረግ እንዳለበት እንደሚያውቅ ልብ በሉ! በረሃዎችን ፈጥሯል፤ መርከቦችን አስምጧል፤ ደኖችን አውድሟል፤ እንዲሁም በሙዚቃዎችና ባልተለመዱ ረብሻዎች በተሞሉ ከተሞች ውስጥ ነፍሷል። ወሰን የሌለው ይመስላል፤ ግና ብላቴናው ነፋሱ ሊችላቸው የሚገቡ ሌሎች ነገሮች አሉ እያለው ነው።

"ይህንን ነው ፍቅር የምንለው" አለ ብላቴናው ነፋሱ የተጠየቀውን ሊሰጠው እንደሆነ ሲገባው።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ስትፈቀር ምንም ነገር መፍጠር ትችላለህ። ስትፈቀር ምን እየተፈጠረ እንዳለ መረዳት አያስፈልግህም፤ ምክንያቱም ሁሉ ነገር የሚሆነው አንተው ውስጥ ነው፣ እናም ሰዎች ሳይቀሩ ራሳቸውን ወደ ነፋስነት መለወጥ ይችላሉ። ነፋሱ እስከረዳቸው ድረስ ነው ግን።"

ነፋሱ ኩራተኛ በመሆኑ ብላቴናው እያየው ባለው ነገር እየተበሳጨ መጣ። የበረሃውን አሸዋ እያነሳ በሃይል ያቦነው ጀመር። በመጨረሻ ግን መላውን ዓለም መዞር ቢችልም እንኳን ሰውን ወደ ነፋስነት መለወጥ አለመቻሉን ማመን ነበረበት። ደግሞም ስለፍቅርም ምንም አያውቅም።

"በዓለም ዙሪያ ስጓዝ ሰዎች ስለ ፍቅር ሲያወሩና ሰማያትን ሲማጸኑ ብዙ ጊዜ ተመልክቻለሁ" አለ ነፋሱ፣ አለማወቁን በማመኑ እየተቆጣ። "ሰማያትን መጠየቅ ይሻል ይሆናል።"

"እሺ፣ በሉ እንኳን እርዳኝ" አለ ብላቴናው። "በዚህ ሥፍራ ላይ የጸሃይን ብርሃን የሚጋርድ የነፋስ ማእበል አስነሳ። ከዚያ ዓይኔን ሳላጠፋ ሰማይ ሰማያትን ማየት እችላለሁ።"

ነፋሱም ባለ ኃይሉ ነፈሰ፤ ሰማይም በአሸዋ ተሸፈነ። ፀሐይ ወደ ወርቃማ ዲስክነት ተቀየረች።

ጦር ሰፈሩ ውስጥ ምንም ማየት አይቻልም። በረሃኞቹ ይህን ነፋስ ለምደውታል። "ሱሙም" ብለውም ይጠሩታል፤ ከባህር ማእበል እንኳን የከፋ ነፋስ ነው። ፈረሶቻቸው ተጯጯሁ፣ ጦር መሳሪያዎቻቸውም በነፋስ ተሞሉ።

አንዱ አዛዥ ወደ ጦር መሪው ዞሮ፣ "ይሄን ነገር ማስቆማችን ሳይበጅን አይቀርም!" አለው።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ብላቴናውን ማየት አልሆነላቸውም። ፊቶቻቸው በሰማያዊ ልብሶቻቸው ተሸፍነዋል፤ ዓይኖቻቸውም ፍርሃታቸውን ያሳያሉ።

"እናስቁመው" ሌላኛው አዛዥ ተናገረ።

"የአላህን ታላቅነት ማየት እሻለሁ" አለ የጦር መሪው በአክብሮት።

"አንድ ሰው ራሱን እንዴት ወደ ነፋስነት መለወጥ እንደሚችል ማየት እፈልጋለሁ።"

ንግግሩ ይለሳለስ እንጂ ፍርሃታቸውን ያሳዩትን የሁለቱን ሰዎች ስም በጭንቅላቱ ጽፏል። እውነተኛ በረኸኞች ፈሪዎች አይደሉምና፣ ነፋሱ እንደቆመለት እነዚህን ሁለት ፈሪዎች ከያሉበት እዝ ያስወግዳቸዋል።

"ፍቅር እንደሚገባሽ ነፋሱ ነገረኝ" አላት ብላቴናው ፀሐይን። "ስለፍቅር የምታውቂ ከሆነ ደግሞ ስለ ሁለንታ ነፍስም ማወቅሽ አይቀርም፤ ምክንያቱም እርሱ ሥሪቱ ከፍቅር ነውና።"

"ካለሁበት ሆኜ" አለች ጸሐይ፣ "የሁለንታን ነፍስ ማየት እችላለሁ። ከነፍሴ ጋር ይነጋገራል፤ በህብረትም እጽዋት እንዲያድጉ፣ በጎችም መጠለያ እንዲያገኙ እናደርጋለን። ካለሁበት ሆኜ፣ እንዲህ ከምድር ርቄ፣ ማፍቀርን ተምሬያለሁ። ደግሞም አውቃለሁ፣ ወደ ምድር ትንሽ ቀረብ ብል በምድር ያለ ነገር ሁሉ ይሞታል፤ የሁለንታ ነፍስ ህልውናም በዚያው ያከትማል። ስለዚህ እርስ በርስ እንተሳሰባለን፤ እርስ በርስም እንፈላለጋለን፤ እኔ ህይወትና ሙቀት እሰጠዋለሁ፣ እሱ ደግሞ መኖሪያ ዓላማዬን ይሰጠኛል።"

"ስለዚህ ስለፍቅር ታውቂያለሽ ማለት ነው" አለ ብላቴናው።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"የሁለንታን ነፍስም አውቀዋለሁ፤ ምክንያቱም በህዋው ላይ በነበረን ማብቂያ የለሽ ጉዞ ብዙ አውርተናል። እስካሁን ድረስ ያጋጠመው ትልቁ ችግሩ ሁሉም ነገር አንድ መሆኑን መረዳት የቻሉት ማእድናትና ተክሎች ብቻ መሆናቸው ነው። ብረት መዳብን ወይም መዳብ ወርቅን መሆን የለበትም። እያንዳንዱ እንደ አንድ ልዩ ፍጡር የየራሱን ትክክለኛ ተግባር ይወጣል፤ እናም ይህንን የጻፈው እጅ መፍጠሩን አምስተኛው ቀን ላይ አቁሞ ቢሆን ኖሮ ይሄ ሁሉ ነገር አንድ የሰላም ህብረ ዝማሬ ይሆን ነበር።

"ግና በስድስተኛው ቀንም ፈጠረ" ፀሐይ ቀጠለች።

"ብልህ ነሽ፣ ምክንያቱም እያንዳንዱን ነገር ከርቀት ታስተውይዋለሽ" አለ ብላቴናው። "ሆኖም ስለ ፍቅር አታውቂም። ስድስተኛ ቀን ባይኖር ኖሮ የሰው ልጅ ህልው አይሆንም ነበር፤ መዳብም መዳብ ብቻ፣ እርሳስም እርሳስ ብቻ ሆነው ይቀሩ ነበር። ሁሉም ነገር የየራሱ እጣፈንታ ያለው መሆኑ ሃቅ ነው፤ ነገር ግን አንድ ቀን ያ እጣፈንታ እውን ይሆናል። ስለዚህ እያንዳንዱ ነገር ራሱን ከእሱ ወደተሻለ ነገር መለወጥና አዲስ እጣፈንታ መፈለግ አለበት፤ አንድ ቀን የሁለንታ ነፍስ አንድ ነገር ብቻ እስኪሆን ድረስ።"

ፀሐይዋ በነገሩ አሰበችበት፣ የብርሃኗን ድምቀት ለመጨመር ወሰነች። ውይይታቸውን በደስታ ሲከታተል የቆየው ነፋስ ደግሞ ፀሐይዋን ብላቴናውን በብርሷ እንዳታውረው ለመከላከል ግፊቱን አበረታው።

"ስለዚህም ነው አልኬሚ የኖረው" አለ ብላቴናው።

"ሁሉም የተደበቀ ሃብቱን ይፈልግ፣ ያገኝም ዘንድ፤ ከዚያም ከቀደመ ህይወቱ የተሻለ መሆንን ይፈልግ ዘንድ ነው። እርሳስ ሚናውን



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

የሚጫወተው ዓለም እርሳስን መፈለግ እስኪያቆም ድረስ ነው፤ ያኔ እርሳስ ራሱን ወደ ወርቅነት መለወጥ ይኖርበታል።

"ይህንኑ ነው አልኬሚስቶች የሚሠሩት። ከሆንነው የተሻልን ለመሆን ስንጥር በዙሪያችን ያለው ነገር ሁሉ የተሻለ እንደሚሆን ያሳያሉ።"

"ታዲያ በምን ምክንያት ነው ስለ ፍቅር አታውቂም ያልከኝ?" ፀሐይ ብላቴናውን ጠየቀችው።

"ምክንያቱም እንደ በረሃው እንቅስቃሴ አልባ መሆን፣ ወይም እንደ ነፋሱ ዓለምን ማናወጥ ፍቅር አይደለም። እንዳንቺም በርቀት ሁሉን ነገር መቃኘትም ፍቅር አይደለም። ፍቅር የሁለንታ ነፍስ የሚለውጥና የሚያሻሽል ኃይል ነው። መጀመሪያ እንዳወቅሁት የሁለንታ ነፍስ ፍጹም መስሎኝ ነበር። ቆይቼ ግን እርሱም እንደሌላው መሆኑንና የራሱ መሻቶችና ጦርነቶች እንዳሉት ተረዳሁ። የሁለንታን ነፍስ የምንመግበው እኛው ነን፤ ስለዚህም የምንኖርበት ዓለም የተሻለ ወይም የባሰ የሚሆነው እኛ የተሻልን ወይ የባስን መሆን ላይ ተመስርቶ ነው። እዚያ ላይ ነው እንግዲህ የፍቅር ኃይል የሚመጣው። ምክንያቱም ስናፈቅር፣ ምን ጊዜም ከሆንነው የተሻልን ለመሆን እንጥራለን።"

"እና አሁን ከእኔ የምትፈልገው ምንድነው?" ጠየቀች ፀሐይ።

"ራሴን ወደነፋስነት ለመለወጥ እንድትረጂኝ እፈልጋለሁ" መለሰ ብላቴናው።

"ከፍጡራን ሁሉ አዋቂ መሆኔን ፍጥረት ሁሉ ያውቃል" አለች ፀሃይ። "ግና አንተን ወደ ነፋስ መቀየርን አላውቅበትም።"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ታዲያ ማንን ነው ማናገር ያለብኝ?"

ፀሐይ ጥቂት አሰብ አደረገች። ነፋሱ የፀሐይም እውቀት ገደብ እንዳለው ለዓለም ለመንገር ቋምጦ ንግግራቸውን ተጠግቶ እያዳመጠ ነው።

"ሁሉን የጻፈውን እጅ አናግረው" አለች ፀሐይ።

ነፋስ በደስታ አፏጨ፤ ከእስከዛሬው በላቀ ኃይልም ነፈሰ። ድንኳኖቹ ከመሬት ጋር የተቆራኙባቸው ካስማዎች እየተነቃቀሉ፣ እንሰሶቹም ከታሰሩባቸው ገመዶች ነፃ እየወጡ ነው። ሲመለከቱ የቆሙትም ሰዎች በነፋሱ እንዳይወሰዱ በመስጋት እጆቻቸውን አቆላልፈው ቆሙ።

ብላቴናው ሁሉን ወደ ከተበው እጅ ዞረ። በዚያው ቅጽበት ሁለንታ በዝምታ መዋጡ ተሰማውና፤ ላለመናገር ወሰነ።

ፍቅር ከልቡ ፈሰሰ፤ ብላቴናውም መጸለይ ጀመረ። ከዚህ በፊት ጸልዮት የማያውቀው ዓይነት ቃላት የሌሉበት፣ ተማጽኖዎችም ያልገቡበት ጸሎት። ጸሎቱ በጎቹ አዲስ ግጦሽ ስለማግኘታቸው ምስጋና አላቀረበም፤ ብላቴናው ብዙ ክሪስታል ይሸጥ ዘንድም አልተማጸነም፤ ያገኛት ሴት በፍቅር ጸንታ ትጠብቀው ዘንድም አልጠየቀም። በዝምታ ውስጥ።

ብላቴናው በረሃው፣ ነፋሱና ፀሐዩ ራሳቸው በዚያ እጅ የተጻፉትን ምልክቶች ለመረዳት እየሞከሩ፣ የየራሳቸውን መንገድ ለመከተል እየሻቱ እና በአንዲት የኤመራልድ ጽላት ላይ የተጻፈውን ለማወቅ እየጣሩ መሆኑን ተገነዘበ። ነገሮች በምድርና በህዋ ላይ በየሥፍራው ተበታትነው መገኘታቸውን፣ ከዚህ መገኘታቸውም ጋር ምንም ዓይነት ምክንያት ወይም ፋይዳ አለመያያዙን ተመለከተ፤ በረሃዎቹም ሆኑ ነፋሶቹ፣ ፀሐይዋም ሆነች ህዝቡ



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ስምን እንደተፈጠሩ እንደማያውቁ ማየትም ቻለ። ነገር ግን ያ ገባሬ ኩሉ የሆነ እጅ ለዚህ ሁሉ ምክንያት ነበረው፤ እናም ያ እጅ ብቻ ነው ተአምራትን መከሰት፣ ወይም ባህርን ወደ በረሃ ወለወጥ፣ … ወይም ሰውን ወደ ነፋስ መለወጥ የሚቻለው። ምክንያቱም ስድስቱ የስነፍጥረት እለታት ወደ ዓቢይ ሥራነት ወደሚለወጥበት ነጥብ ሁለንታን የመራ አንድ ታላቅ ንድፍ መሆኑን መገንዘብ የሚችለው ያ እጅ ብቻ ነው።

ብላቴናው የሁለንታን ነፍስ ቢመረምረው የእግዚአብሔር ነፍስ አንድ አካል ሆኖ አገኘው። የእግዚአብሔር ነፍስ ደግሞ የራሱ ነፍስ መሆኑን አስተዋለ። እናም እሱ፣ ብላቴናው ተአምራትን መከሰት እንደሚችል ተገነዘበ።

*   *   *

ሲሙም እስከዛሬ ነፍሶበት በማያውቀው ልክ ነፈሰ። አረቦቹ ራሱን ወደ ነፋስ ስለለወጠውና በበረሃው ውስጥ አቻ በሌለው የጦር መሪ እዝ ሥር ያለን የጦር ሠፈር ሙሉ በሙሉ ለማውደም ተቃርቦ ስለነበረው ብላቴና ገድል ከእንግዲህ ወዲያ ለሚመጡ አያሌ ትውልዶች ይተርኩላቸዋል።

ሲሙም መንፈሱን ሲያቆም የሁሉም ዓይን ብላቴናው ወደነበረበት ሥፍራ ተወረወረ። እሱ ግን በዚያ ሥፍራ አልነበረም፤ ብላቴናው ከጦር ሠፈሩ አንድ ሩቅ ጥግ በአሸዋ ከተሸፈነ ሰይፍ አጠገብ ቆሟል።

ሰዎቹ በምትሃቱ ተሸብረዋል። ሆኖም በገጻቸው ላይ ፈገግታን የሚረጩ ሁለት ሰዎች እዚያ መሐል ነበሩ፡- እነርሱም አልኬሚስቱና ጦር መሪው ነበሩ፤ አልኬሚስቱ ፍጹም የሆነ ደቀመዝሙርን አግኝቷልና፣ ጦር መሪው ደግሞ የአላህን ታላቅነት አይቷልና በፈገግታ ተሞልተዋል።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

በማግስቱ ጀኔራሉ ለብላቴናውና ለአልኬሚስቱ የክብር አሸኛኘት አደረገላቸው፤ እስከፈለጉት ሥፍራ ድረስ የሚሸኟቸውን አጃቢዎችንም ሰጣቸው።

* * *

ቀኑን ሙሉ ተጓዙ። አመሻሹ ላይ አንድ የቅብጥ ገዳም ጋር ደረሱ። አልኬሚስቱ ከፈረሱ ወርዶ፣ ሽኚዎቹ ወደ ጦር ሰፈራቸው መመለስ እንደሚችሉ ነገራቸው።

"ከአሁን ጀምሮ ብቻህን ትሆናለህ" አለ አልኬሚስቱ።

"ፒራሚዶቹ ጋር ለመድረስ የሶስት ሰዓት መንገድ ብቻ ነው የቀረህ።"

"አመሰግንሃለሁ" አለ ብላቴናው። "የሁለንታን ቋንቋ አስተምረኸኛል።"

"ቀድሞውኑ የምታውቀውን ነው የቀሰቀስኩት።"

አልኬሚስቱ የገዳሙን መዝጊያ አንኳኳ። ጥቁር የለበሱ መነኩሴ ወደ መግቢያው መጡ። ሁለቱ ለጥቂት ደቂቃዎች በቅብጥ ቋንቋ ተነጋገሩና፣ አልኬሚስቱ ብላቴናውን አስገባው።

"ኩሽናቸውን አንድ አፍታ እንድጠቀምበት ነው የጠየቅኋቸው" አለና አልኬሚስቱ ፈገገ።

በጓሮ በኩል ወደሚገኘው ኩሽና አመሩ። አልኬሚስቱ እሳት አያያዘ፤ መነኩሴው ደግሞ ቁራጭ እርሳስ አመጡለት። አልኬሚስቱ እርሳሱን መጥበሻው ላይ አደረገው። እርሳሱ ቀልጦ ፈሳሽ ሲሆን፣ አልኬሚስቱ



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ከቦርሳው ያንን ያልተለመደ ቢጫ እንቁላሉን አወጣ። ከእንቁላሉ ላይ እንደፀጉር የቀጠነ ፍቅፋቂ ወስዶ በሰም ሸፈነው፣ ከዚያም እርሳሱ ያለበት መጥበሻ ላይ ጨመረው።

ውሁዱ ደም መሰለ። አልኬሚስቱ መጥበሻውን ከእሳቱ ላይ አውርዶ ይበርድ ዘንድ አስቀመጠው። ከዚያም ከመነኩሴው ጋር ስለጎሳ ጦርነቶቹ ያወራ ጀመር።

"በቀላሉ የሚያቆሙ አይመስሉም" አላቸው መነኩሴውን። መነኩሴው ተበሳጭተዋል። ጦርነቱ እስኪቆም ብለው ሲራራዎች ጊዛ ላይ አርፈዋል። "ሆኖም እግዚአብሔር የፈቀደው ይሆናል" አሉ መነኩሴው።

"ልክ ብለዋል" አልኬሚስቱ መለሰ።

መጥበሻው ሲቀዘቅዝ መነኩሴውና ብላቴናው በአድናቆት ተመለከቱት። እርሳሱ የመጥበሻውን ቅርጽ ይዟል፣ እርሳስነቱም ጠፍቷል። ወርቅ ሆኗል።

"እኔም አንድ ቀን እንደዚህ ማድረግ እችል ይሆን?" ብላቴናው ጠየቀ።

"ይሄ የእኔ እጣፈንታ ነበር፣ ያንተ አይደለም!" መለሰ አልኬሚስቱ።

"ነገር ግን ይሄም እንደሚቻል ላሳይህ ብዬ ነው።"

ወደ ገዳሙ መግቢያ ተመለሱ። በዚያም አልኬሚስቱ ከብ ጥፍጥፉን ወርቅ ለአራት ከፈለው።

"ይሄ የእርሶዎ ነው" አለ አንዱን ቁራጭ ለመነኩሴው እየሰጠ።

"ለመንገደኞች ለሚያሳዩት ደግነት ይሁን።"



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ኧረግ! ይሄን ያህል ክፍያ እኮ አይገባኝም" መነኩሴው መለሱ።

"ሌላ ጊዜ እንዲህ እንዳይሉ። ህይወት ከሰማችዎት፣ ከዚህ በኂላ ከዚህ ያነሰ ልትሰጥዎት ትጀምራለች።"

አልኬሚስቱ ወደ ብላቴናው ዞረ። "ይሄ ደግሞ ላንተ ነው። ለጄኔራሉ የሰጠኸውን መተኪያ ይሁንህ።"

ብላቴናውም ለጄኔራሉ የሰጠው ከዚህ በጣም ያነሰ እንደነበረ ሊናገር ነበር። ሆኖም አልኬሚስቱ መነኩሴውን ያላቸውን ሰምቷልና በዝምታ አለፈው።

"ይሄ ደግሞ ለእኔ ነው" አለ አልኬሚስቱ አንደኛውን ቁራጭ ለራሱ እያስቀረ። "ምክንያቱም የጎሳ ጦርነቶች ወዳሉበት በረሃ መመለስ አለብኝ።"

አራተኛውን ቁራሽ ለመነኩሴው ሰጣቸው።

"ይሄ ለብላቴናው ነው። ባስፈለገው ጊዜ ይጠቀምበት ዘንድ።"

"እኔ እኮ ግን ድብቅ ሃብቴን ፍለጋ ነው የምሄደው" አለ ብላቴናው። "ደግሞም ወደ እሱ በጣም ተቃርቤያለሁ።"

"እንደምታገኘውም እርግጠኛ ነኝ" አለ አልኬሚስቱ።

"ታዲያ ይሄ ምን ያደርግልኛል?"

"ሃብት ንብረትህን ሁለት ጊዜ አጥተሃል። አንድ ጊዜ በሌባው፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በጄነራሉ። እኔ መንፈሳዊ እምነት ያለኝ ሽማግሌ አረብ ነኝ፤ ስለዚህም በምሳሌዎቻችን አምናለሁ። እንዲህ የሚል ምሳሌያዊ አነጋገር



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

አለን፣ "አንዴ ያጋጠመ ነገር መልሶ አያጋጥምም። ሁለት ጊዜ ያጋጠመህ ነገር ግን ለሶስተኛ ጊዜ ያጋጥምሃል።" በየፈረሶቻቸው ላይ ተቀመጡ።

* * *

"ስለ ህልሞች አንድ ታሪክ ብነግርህ እወዳለሁ" አለ አልኬሚስቱ።

ብላቴናው ፈረሱን ቀረብ አደረገው።

"በጥንታዊት ሮም፣ በዘመነ ጢባርዮስ፣ ሁለት ወንዶች ልጆች ያሉት አንድ መልካም ሰው ነበረ። አንደኛው ልጁ ወታደር ነውና በጣም ሩቅ ወደሆኑት የግዛቲቱ ክልሎች ይላክ ነበር። ሁለተኛው ባለቅኔ ነበር፣ እናም መላዋን ሮም በውብ ስንኞቹ ያስደስት ነበር።

"አንድ ምሽት፣ አባት ህልም አየ። አንድ መልአክ ወደ እርሱ ቀርቦ፣ ከልጆቹ የአንደኛው ቃላት ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፉ በመላው ዓለም ይታወቃሉ፤ ይደገማሉም። አባት ተመስገን እያለና እያለቀሰ ከህልሙ ባነነ፤ ምክንያቱም ህይወት ቸር በመሆኗ የትኛውም አባት ቢያውቀው የሚኮራበትን እውነት ገልጣለታለች።

"ብዙም ሳይቆይ አባት በሰረገላ ሲገጭ የነበረን ህፃን አተርፋለሁ ብሎ ሲሞክር ሞተ። እድሜውን ሙሉ የኖረው በጽድቅ ምግባር ነበርና ቀጥታ ወደ መንግሥተ ሰማያት ተወሰደ፤ በዚያም በህልሙ ያየውን መልአክ አገኘው።

"'ሁሌም መልካም ሰው ነበርክ' አለው መልአኩ። 'ህይወትህን በፍቅር ኖረሃት በክብር እየሞትክ ነው። አሁን እኔ የተመኘኸውን ማንኛውንም ነገር ልሰጥህ ዝግጁ ነኝ።'



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"'ህይወት ለእኔ መልካም ሆናልኝ ነበር' አለ ሰውየው። 'በህልሜ ስትታየኝ፣ የልፋቴን ዋጋ እንዳገኘሁ ተሰማኝ፤ ምክንያቱም የልጁ ቅኔዎች በመጪዎቹ ትውልዶች ይነበባሉ። ለራሴ የምፈልገው ነገር የለም። ሆኖም ማንም አባት በምግባር አንፃ፣ በትምህርት አበልጽጎ ያሳደገው ልጁ ዝነኛ ሲሆንለት ኩራት ይሰማዋል። እኔ የምፈልገው ከብዙ ጊዜ በኋላ የልጄን ቃላት ማየት መቻልን ነው።'

"መልአኩ የሰውየውን ትከሻ ነካውና፣ 'ሁለቱም ወደ ሩቅ፣ መጪ ህይወት ነጎዱ። አንድ ባእድ ቋንቋ የሚነገርበት ግዙፍ ሥፍራም ደረሱ። ሰውየው በደስታ አነባ።

"'የልጄ ቅኔዎች ዘመን የማይሽራቸው እንደሆኑ አውቅ ነበር' አለው መልአኩን ማንባቱን ሳያቆም፣ እነዚህ ሰዎች የሚናገሩት ከልጄ ግጥሞች የትኛውን እንደሆነ ልትነግረኝ ትችላለህ?

"መልአኩ ወደ ሰውየው ቀረብ አለና በአቅራቢያቸው ወዳለ መቀመጫ ወስዶት አብረውት ተቀመጡ።

"'የባለቅኔው ልጅህ ቅኔዎች በመላው ሮም ዝነኞች ናቸው' አለ መልአኩ። 'የጢባርዮስ ዘመን ሲፈጸም ግን ቅኔዎቹ ይረሳሉ። አሁን የምትሰማቸው ቃላት የወታደሩ ልጅህ ቃላት ናቸው።'

ሰውየው መልአኩን በአድናቆት ተመለከተው።

"'ልጅህ ሩቅ አገር ተልእኮ ሲያገለግል ቆይቶ የመቶ አለቅነት ማእረግ አገኘ። መልካም ሰው ነበር። አንድ ቀን ከአሽከሮቹ አንዱ ታመመበት፤ አሽከሩ ሊሞት ደረሰ። ልጅህ በሽተኞችን ስለሚፈውሰው መምህር ሰምቷልና



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

መምህሩ ወዳለበት ገሰገሰ። በመንገዱም ላይ እሱ የሚፈልገው ሰው የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑንም አወቀ። በእርሱ የተፈወሱ ሰዎችን ሲያገኛቸው የሰውየውን ትምህርቶች ነገሩት። እናም ምንም እንኳን የሮማ መቶ አለቃ ቢሆንም፣ እምነቱን ቀይሮ እምነታቸውን ተቀበለ። ጥቂት ቆይቶም የሚፈልገውን ሰው አገኘው፡፡

"'አንድ አሽከሩ ከሞት አፋፍ ላይ መሆኑን ነገረው፤ መምህሩም ከእርሱ ጋር ወደ ቤቱ ለመሔድ ፈቀደ። መቶ አለቃው ግን በእምነቱ የጸና ነበረ፣ የመምህሩን ዓይኖች አይቶ በእርግጥም ከእግዚአብሔር ልጅ አጠገብ መቆሙን አመነ፡፡

"'ልጅህ የተናገረው እንዲህ ነበር' አለው መልአኩ። 'በዚያች ቅጽበት የተናገራቸውና ተዘንግተውም የማያውቁት የልጅህ ቃላት እኒህ ነበሩ፡- "ጌታዬ ወደ ቤቴ ትገባ ዘንድ የተገባኝ ሰው አይደለሁም። ነገር ግን አንተ አንድ ቃል ብትናገር ባሪያዬ ይድናል።"

አልኬሚስቱም አለ፣ "ምንም ይሥራ ምንም፣ በምድር ላይ ያለ ሰው ሁሉ ለዓለም ታሪክ ማእከላዊ ሚና ይጫወታል። ነገር ግን አይታወቀውም።"

ብላቴናው ፈገግ አለ። የህይወት ጥያቄዎች ለአንድ እረኛ ይሄን ያህል ወሳኝ ይሆናሉ ብሎ አስቦ አያውቅም ነበር።

"ደህና ሁን" አለ አልኬሚስቱ።

"ደህና ሁን" መለሰ ብላቴናው።

* * *



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ብላቴናው ልቡ የሚነግረውን እያዳመጠ ለብዙ ሰዓታት በረሃውን በግልቢያ አቋረጠ፡፡ ልቡ ነው ሃብቱ የት እንደተደበቀ የሚነግረው፡፡

"ድብቅ ሃብትህ ባለበት፣ ልብህም ይኖራል" ብሎ ነግሮታል አልኬሚስቱ፡፡

ልቡ ግን ስለሌሎች ነገሮች እያወራ ነበር፡፡ በሁለት የተለያዩ አጋጣሚዎች ያየውን አንድ ህልም ለመከተል የበጎች መንጋውን ስለተወው እረኛ በኩራት ይናገራል፡፡ ስለ እጣፈንታ፣ ሩቅ ሩቅ ሥፍራዎችን ወይም ቆነጃጅት ሴቶችን ፍለጋ ስለተጓዙና በያዟቸው ሃሳቦች ምክንያት እንቅፋቶች ተጋርጠውባቸው ስለነበሩ አያሌ ሰዎች ይናገራል፡፡ ስለጉዞዎች፣ ስለ አዳዲስ ግኝቶች፣ ስለ መጻሕፍትና ስለ ለውጥ ይናገራል፡፡

ሌላኛውን የአሸዋ ኮረብታ ሲወጣ ሲል ልቡ አንሾካሾከለት፡- "የምታነባበትን ሥፍራ ልብ በል፡፡ የእኔ መገኛ እዚያ ነው፤ የድብቅ ሃብትህ መገኛም እዚያ ነው፡፡"

ብላቴናው ኮረብታውን በዝግታ ወጣ፡፡ ሙሉዋ ጨረቃ በከዋክብት በደመቀው ሰማይ ላይ ዛሬም ወጥታለች፡- ኦሲሱን ትቶ ከመጣ ወር ሆኖታል፡፡ የጨረቃዋ ብርሃን በኮረብታዎቹ መሃል ያጠላቸው ጥላዎች እየተንከባለለ የሚሔድ እንደሚመስል ባህር ያለ ምስል ፈጥረዋል፤ ሁኔታውን ከአልኬሚስቱ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ በረሃው ውስጥ የተገናኘባትን ቅጽበት አስታወሰው፡፡ ከዚያ ጨረቃዋ በበረሃው ጸጥታ እና ድብቅ ሃብቱን በመፈለግ ላይ ባለ በአንድ ሰው ጉዞ ላይ አረፈች፡፡

በኮረብታው ጫፍ ላይ ሲደርስ፣ ልቡ ዘለለ፡፡ በዚያ ሥፍራ በጨረቃ ብርሃንና በበረሃው ብሩህነት ደምቀው፤ ባለ ግርማ ሞገሶቹ የግብጽ ፒራሚዶች ቆመዋል፡፡



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ብላቴናው ተንበርክኮ አለቀሰ። በእጣፈንታው እንዲያምን ስለአደረገው ንጉሥ፣ ነጋዴ፣ እንግሊዙ እና አልኬሚስቱን ያገኝ ዘንድ መንገድ የሆነለትን እግዚአብሔርን አመሰገነ።

ከሁሉም በላይ ደግሞ፣ ፍቅር አንድን ሰው እጣፈንታውን ከመከተል እንደማያግደው የነገረችውን የበረሃ ሴት በማግኘቱም አመሰገነው።

ከፈለገ አሁኑኑ ወደ አሲሱ ተመልሶ፣ ወደ ፋጡማ ሔዶ፣ ኑሮውን እንደ አንድ ተራ እረኛ መኖር ይችላል። የሁለንታን ቋንቋ ከተረዳ ወዲህ እርሳስን ወደ ወርቅ እንዴት መለወጥ እንደሚችል ቢያውቅም፣ አልኬሚስቱ በረሃው ውስጥ መኖር ቀጥሎ የለምን? እሱ ሳይንሱንና ኪነጥበቡን ለማንም የማሳየት ግዴታ የለበትም። ብላቴናው እጣፈንታውን እውን ለማድረግ ሲሞክር ማወቅ ያለበትን ነገር ሁሉ መማሩን፣ እንዲሁም የማያልማቸውን ነገሮች ሁሉ በተግባር ማግኘቱን ለራሱ ነገረው።

አሁን ግን ድብቅ ሃብቱን ሲያገኝ ባለበት ደቂቃ፣ የትኛውም ፕሮጀክት ዓላማውን እስኪያሳካ ድረስ እንደማይጠናቀቅ ራሱን አስታወሰው። ብላቴናው በዙሪያው ያለውን አሸዋ አየው፣ እንባው በተንጠባጠበት ሥፍራ አንዲት የበረሃ ጢንዚዛ በአሸዋው ውስጥ በፍጥነት ስትሹለከለክ ተመለከተ። በዚህ ወቅት የሚታዩ ጢንዚዛዎች በግብጽ የእግዚአብሔር ተምሳሌቶች ተደርገው እንደሚቆጠሩ ያውቃል።

ሌላ ንግር! ብላቴናው አሸዋውን መቆፈር ጀመረ። እየቆፈረ እያለም አንድ ጊዜ የክሪስታል ነጋዴው ማንም ሰው ጓሮው ፒራሚድ ሊያቆም ይችላል ያለውን አብሰለሰለው። ብላቴናው ግን ከአሁን ጀምሮ እስከ ህይወቱ ፍጻሜ ድረስ እንኳን ድንጋይ ቢከምር አንድ ፒራሚድ መሥራት እንደማይችል ገባው።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ሌሊቱን ሙሉ የመረጠው ቦታ ላይ ቢቆፍርም ምንም አላገኘም። ፒራሚዶቹ ከተሠሩ ጀምሮ ያሉት ምእተ ዓመታት የተጫኑት ያህል ተሰማው። ሆኖም አላቋረጠም። ቆፍሮ ያወጣውን አሸዋ አልፎ አልፎ ከሚመልስበት ነፋስ ጋር እየታገለ ቁፋሮውን ለመቀጠል ጣረ። እጆቹ መዛላቸው አንሶ ተላላጡ፤ እሱ ግን ልቡን አዳመጠው። ልቡ እንባው የተንጠባጠበበት ሥፍራ ላይ እንዲቆፍር ነግሮታል።

ጉድጓድ ውስጥ ያጋጠሙትን ድንጋዮች ለማውጣት እየታገለ እያለ የእግር ኮቴ ተሰማው። ብዙ ምስሎች ወደ እርሱ እየተጠጉ ነው። የጨረቃ ብርሃን ከጀርባቸው ይከተላቸው ነበርና ብላቴናው ዓይኖቻቸውንም ሆነ መልካቸውን ማየት አልቻለም።

"ምን እየሰራህ ነው?" አንዱ ምስል ጠየቀው።

ብላቴናው ፈርቶ ነበርና አልመለሰለትም። ድብቅ ሃብቱ ያለበትን ሥፍራ አግኝቶታል፤ ሊፈጠር የሚችለው ነገር ግን አስግቶታል።

"የጎሳ ጦርነቶቹ ስደተኞች ነን፣ ስለዚህም ገንዘብ እንፈልጋለን" ሌላኛው ምስል ተናገረ። "እሱ ውስጥ ምን እየደበቅህ ነው?"

"ምንም እየደበቅሁ አይደለም" ብላቴናው መለሰ።

ሆኖም ከእነርሱ አንዱ ብላቴናውን ይዞ ከጉድጓዱ አስወጣው። ሌላኛው፣ የብላቴናውን ቦርሳ ሲፈትሽ የነበረው ደግሞ ያንን የወርቅ ቁራጭ አገኘ።

"እዚህ ውስጥ ወርቅ አግኝቻለሁ" አለ።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ጨረቃዋ ብላቴናውን በያዘው አረብ ፊት ላይ አበራች፤ ብላቴናው በአረቡ ዓይኖች ውስጥ ሞት ታየው።

"መሬት ውስጥ የቀበረው ሌላም ወርቅ ይኖረው ይሆናል"

ብላቴናው ቁፋሮውን እንዲቀጥል አደረጉት፤ ምንም አላገኙም። ፀሐይዋ እንደወጣች ሰዎቹ ብላቴናውን መደብደብ ጀመሩ። ብላቴናው ቆሳስሎ እየደማ ነው፤ ልብሶቹ በላዩ ላይ ተበጫጭቀዋል፤ እሱም ሞቱ እንደተቃረበ ተሰማው።

"የምትሞት ከሆነ ገንዘብ ምን ያደርግልሃል? ገንዘብ ያንድን ሰው ህይወት ሁሌም አይታደግም" ብሎት ነበር አልኬሚስቱ። በመጨረሻ ብላቴናው "ድብቅ ሃብቴን ለማግኘት ነው የምቆፍረው!" ብሎ ሰዎቹ ላይ ጮኸባቸው። አፉ ቢደማና ቢያባብጥም፣ ሁለት ጊዜ የግብጽ ፒራሚዶች አጠገብ ስለተቀበረ ሀብት ህልም ማየቱን ለአጥቂዎቹ ነገራቸው።

የቡድኑ መሪ የሚመስለው ሰውዬ አንዱን እንዲህ አለው፡- "ተወው። ሌላ ነገር የለውም። ይህንን ወርቅም ሠርቆት መሆን አለበት።"

ብላቴናው ራሱን ወደ መሳት ተቃርቦ አሸዋው ላይ ወደቀ። መሪው እየወዘወዘው "መሔዳችን ነው" አለው።

ከመሔዳቸው በፊት ግን ወደ ብላቴናው ተመልሶ ነገረው፡- "አትሞትም። ትኖራለህ፤ አንድ ሰው ይህን ያህል ደደብ መሆን እንደሌለበትም ትረዳለህ። ከሁለት ዓመት በፊት እኔም ስለዚሁ ሥፍራ ተደጋጋሚ ህልም አይቼ ነበር። ወደ ስፔን ሄጄ አረኞችና በጎች የሚያድሩበትን አንድ የፈረሰ ቤተክርስቲያን መፈለግ እንዳለብኝ አለምኩ። በህልሜም በቤተልሔሙ



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ፍርስራሽ ላይ የበቀለ የዋርካ ዛፍ እንዳለና የዛፉን ሥሮች ብቆፍራቸው የተቀበረ ሃብት እንደማገኝ ተነገረኝ፡፡ ሆኖም፣ ገና ለገና ተደጋጋሚ ህልም አየሁ ብዬ ሙሉውን በረሃ የማቋርጥ ደደብ አይደለሁም፡፡"

ሰዎቹ ከእይታ ተሰወሩ፡፡

ብላቴናው እየተንገዳገደ ተነሳና ፒራሚዶቹን መልሶ አያቸው፡፡ የሚስቁበት መሰለው፣ ልቡ በደስታ እየፈነደቀ መልሶ ሳቀባቸው፡፡

ምክንያቱም አሁን ድብቅ ሃብቱ የት እንደሚገኝ አውቋል፡፡



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

# ድህረ ታሪክ

ብላቴናው መሽትሽት ሲል የተራቆተው ትንሽዬ ቤተክርስቲያን ጋር ደረሰ። ዋርካው አሁንም እዚያው ትንሽዬ ቤተልሔሙ ሥፍራ ላይ ነው ያለው፤ አሁንም ግማሽ በግማሽ በወደመው ጣሪያ በኩል ከዋክብቱ ይታያሉ። በዚህ ሥፍራ ከበጎቹ ጋር የነበረበትን ጊዜ አስታወሰ፤ ሰላማዊ ሌሊት ነበረ... ከህልሙ በስተቀር።

አሁን ከበጎቹ ጋር አልመጣም፤ ከአካፋ ጋር እንጂ። ሰማዩን እየተመለከተ ለረጅም ጊዜ ተቀመጠ። ከዚያም የወይን ጠርሙሱን አወጣና ጥቂት ተጎነጨለት። ከአልኬሚስቱ ጋር በረሃው ውስጥ የተቀመጠባትና ከዋክብቱን እያዩ አብረው ወይን የጠጡባትን ምሽት አስታወሰ። ስለተጓዘባቸው በርካታ መንገዶች፣ እና እግዚአብሔር ወደ ድብቅ ሃብቱ የሚያደርሰውን መንገድ ለእሱ ስለገለጸበት ያልተለመደ ዘዴ አሰላሰለ። በተደጋጋሚው ህልሙ ምክንያታዊነት ባያምን ኖሮ ከጂፕሲዋ ሴትዮ፣ ከንጉሱ፣ ከሌባው ወይም



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ከሌሎቹ ሰዎች ጋር አይገናኝም ነበር። "ዝርዝሩ ብዙ ነው። መንገዱ ግን ንግሮቹ ውስጥ ተጽፏልና፣ ልሳሳት የምችልበት ሁኔታ አልነበረም" አለ ለራሱ።

ካንቀላፋበት ሲነቃ ጸሃይዋ ከርራ ነበር። የዋርካውን ሥር መቆፈር ጀመረ።

"አንተ ሽማግሌ ጠንቋይ" ብላቴናው ወደ ሰማዩ ጮኸ። "የማታውቀው ታሪክ የለም። ወደዚህ ቤተክርስቲያን መመለሻ እንዲሆነኝ ብለህ ሳይቀር ገዳሙ ውስጥ ወርቅ አስቀምጠህልኛል። ዝብትልትል ብዬ ወደ ገዳሙ ስመለስ መነኩሴው ሳቁብኝ። ከዚያ አደጋ ልታድነኝ አትችልም ነበር?"

"አዎ" ነፋሱ የተሸከመው ድምጽ ተናገረ። "ነግሬህ ቢሆን ኖሮ ፒራሚዶቹን አታያቸውም ነበር። ውቦች ናቸው አይደል?"

ብላቴናው ፈገግ አለና ቁፋሮውን ቀጠለ። ከአንድ ሰዓት በኋላ የስፔን የወርቅ ሳንቲሞች ያሉበት ካዝና አገኘ። የከበሩ ደንጋዮች፣ በቀይና በነጭ ላባዎች ያጌጡ የወርቅ ጭምብሎች እንዲሁም የተጊያጊያጡ የድንጋይ ሃውልቶች ከተቀበረው ሃብት መሐል አሉበት። እነዚህ ሁሉ አገሪቱ ከብዙ ዓመታት በፊት በወረራ ያገኘቻቸውና የተረሱ ሃብቶች ናቸው።

ብላቴናው ዑሪም እና ቱሚምን አወጣ። እነዚህን ድንጋዮች አንድ ጊዜ፣ ያውም አንድ ማለዳ ገበያ ውስጥ በነበረ ጊዜ ብቻ ነው የተጠቀመባቸው። ህይወቱና መንገዱ ሁሌም በቂ ንግሮችን ሲለግሱት ቆይተዋል።

ዑሪምና ቱሚምን ካዝናው ውስጥ አስቀመጣቸው። እነሱም የአዲሱ ሃብቱ አካላት ናቸው፤ ምክንያቱም ከእንግዲህ ሊያያቸው የማይቻለው የአረጋዊው ንጉስ ማስታወሻዎች ናቸው።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"እውነት ነው፤ ህይወት እጣፈንታቸውን ለሚከተሉ ሰዎች እውነትም ደግ ናት" ሲል አሰበ ብላቴናው። ከዚያም በቃሉ መሠረት ለጂፕሲዋ ሴትዮ ከሐብቱ አንድ አስረኛውን ሲሰጣቸው ወደ ታሪፋ መሄድ እንዳለበት አስታወሰ። "እነኚያ ጂፕሲዎች በእርግጥም ብልሆች ናቸው" ሲልም ተደነቀ። ምናልባት ብዙ ጊዜ ስለሚጓዙ ይሆናል።

ነፋሱ እንደገና መንፈስ ጀመረ። ሌቫንተር ነው፣ ከወደ አፍሪካ የሚመጣው ነፋስ። የበረሃውን ጠረንም ሆነ የሙሮችን የወረራ ማስፈራሪያ ይዞ አልመጣም። ይልቁንም፣ ብላቴናው በደንብ የሚያውቀውን የሽቶ መዓዛ እና የከንፈር መሳም ከሩ...ቅ ሥፍራ የእሱ ከናፍር ላይ እስኪያርፍ ድረስ ቀስ...ቀስ እያለ የመጣ መሳምን ይዞ ነው ነፋሱ የመጣው።

ብላቴናው ፈገግ አለ። ይህንን ስታደርግ የመጀመሪያዋ ነው።

"እየመጣሁ ነው፤ ፋጡማ" አለ።



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

# ፓውሎ ኮዬልሆ ማነው?

ፓውሎ ከመሐንዲስ አባቱ ፔድሮ ኬይማ ኮዬልሆ ደ ሶዛ እና ከቤት እመቤት እናቱ በነሐሴ ወር 1974 በብራዚሏ ሪዮ ዲጄኔሮ ተወለደ። ገና ከጅምሩ ከያኒ ለመሆን ይመኝ ነበር። ጥብቅ የሥነሥርዓት ቁጥጥር በሚበዛበት የኢየሱሳዊያን ትምህርት ቤትም ተሰጥኦውን መለየት ቻለ - እናም ጸሐፊነቱን አወቀ። የፓውሎ ወላጆች ግን ስለ እርሱ ሌላ ቋንቋ ነበራቸው። ለስነጽሑፍ የነበረውን መሰጠት ሊያስተውት ጫና አድርገውበት ሳይሳካላቸው ሲቀርም ልጁ አእምሮው ተነክቷል ብለው ተጠራጠሩ። በዚህም ምክንያት አስራ ሰባት ዓመት ሲሞላው አባቱ ሁለት ጊዜ በአእምሮ ሆስፒታል ሊያሳክመው ወስዶታል። ወላጆቹ በኋላም ፓውሎ እንደ የቴአትር ቡድን ውስጥ ሲቀሳቀልና ከዚያም በጋዜጠኛነት መሥራት ሲጀምር መልሰው ወደ አእምሮ ሐኪም ወስደውታል።

ፓውሎ የመንጋ አስተሳሰብን አይከተልም! ይልቁንም ሁሌም አዲስ አዲስ ነገር ለማግኘት ይጥራል። በ1968 ጨቋኝ በነበረው የብራዚል መንግሥት



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

ላይ የሽምቅ ውጊያና የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ሲጋጋሉ ፓውሎ የለውጥ አራማጅ የፖለቲካ አቋም ይዞ፣ ከሰላምና ፍቅር ወዳዱ ትውልድ ጋር ተባብሯል። የካርሎስ ካስታኔዳን እግር ተከትሎ መንፈሳዊ እውቀትንና ልምድን ፍለጋ በመላው ላቲን አሜሪካ ተዘዋውሯል። ቴአትር ቤት ከመሥራቱም በላይ "2001" የሚባል መጽሔትም ጀምሯል። ራውል ሴክሳስ ከሚባል የሙዚቃ አቅራቢ ጋር በግጥም ደራሲነት የብራዚልን የሮክ ሙዚቃ ለመለወጥ ሰርቷል። በ1973 ፓውሎና ራውል "አማራጭ ማኅበረሰብ" የተሰኘውና ሃሳብን በነፃነት ለመግለጽ መብት የሚታገለው ድርጅት አባል ሆነዋል፤ እንዲያውም ስለ ነፃነት የሚጮሁ ተከታታይ ኩምክናዎችንም ደርሷል፤ ከውናል። የድርጅቱ አባላት ወህኒ በወረዱ በሁለተኛው ቀን ፓውሎ በነጭ ለባሽ ወታደሮች ታፍኖ ሥቃይ ደርሶበታል።

ይሄ ገጠመኙ ከፍተኛ ተጽእኖ አሳድሮበታል። ፓውሎ በ26 ዓመቱ የህይወትን ዳር ዳሯን መኖር በቃኝ "መደበኛ" አኗኗር ይኑረኝ ብሎ ወሰነ። በሙዚቃ ኢንዱስትሪው ውስጥ በሥራ አሥኪያጅነት አገለገለ። መጻፍ ቢሞክርም ከአንድ ከማያውቀው ሰው ጋር እስኪገናኝ ድረስ ድርሰትን ሥራዬ ብሎ አልያዘውም ነበር። መጀመሪያ ላይ ሰውየው በህልሙ ታየው፤ ከሁለት ወራት በኋላ ደግሞ ፓውሎ ሰውየውን አምስተርዳም አንድ ካፌ ውስጥ አገኘው። እንግዳው ሰውም ፓውሎ ወደ ካቶሊክነቱ ተመልሶ የእስማትን በጎ ጎን እንዲያጠና ሃሳብ አቀረበለት። የመካከለኛው ዘመን የመናኞች መንገድ በሆነው የሳንቲያጎ መንገድ በእግሩ እንዲጓዝም አበረታታው።

ያንን ጉዞውን ባጠናቀቀ በዓመቱ /በ1978/፣ ፓውሎ "ዘ ፒልግሪሜጅ" የተሰኘውን መጽሐፉን ጻፈ። መጽሐፉ ተርታ ሰዎችም እጅግ ልዩ የሆኑ ነገሮች ሲያጋጥማቸው የመቻሉን ሁኔታ ከራሱ ገጠመኝ በመነሳት የገለጸበት መጽሐፍ ነው። ከአመት በኋላ ደግሞ በዓይነቱ ከበፊቱ በጣም የሚለየውን



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

"ዘ አልኬሚስት" ጻፈ፡፡ የመጀመሪያው እትም 900 ቅጂ ብቻ ነበር የተሸጠለት፤ በመሆኑም አሳታሚው ዳግም የፓውሎን ሥራዎች ላለማተም ወሰነ፡፡

ፓውሎ ግን ህልሙን ለመተው እጅ የሚሰጥ አልሆነም፡፡ ሌላ ግዙፍ አሳታሚ ድርጅት አገኘ፡፡ "ብራይዳ" የተባለ መጽሐፉን አሳተመ፡፡ መጽሐፉ ገና ወደ እንግሊዝኛ ሳይተረጎም ጀምሮ ከፍተኛ የመገናኛ ብዙሃን ትኩረት አገኘ፡፡ በዚህ ጊዜ የቀድሞዎቹ መጻሕፍት "ዘ አልኬሚስት" እና "ዘ ፒልግሪሜጅ" የከፍተኛ ሽያጭ ዝርዝር ውስጥ ገቡ፡፡ "ዘ አልኬሚስት" ከብራዚል የስነጽሑፍ ሥራዎች የትኛውም ሥራ ተሸጦ በማያውቅበት ብዛት እጅግ ብዙ ቅጂዎች ተሸጡ፡፡

የፓውሎ ታሪክ በዚህ አያበቃም፡፡ በከፍተኛ ሽያጭ ሰንጠረዥ ውስጥ የገቡና የአንባቢውን ልብ በየአገሩ መዝለቅ የቻሉ በርካታ መጻሕፍትን ጽፏል፡፡ እነርሱም፡-

- ባይ ዘ ሪቨር ፒየድራ አይ ሳት ዳውን ኤንድ ዌፕት
- ዘ ፊፍዝ ማውንቴን
- ቬሮኒካ ዲሳይድስ ቱ ዳይ
- ዘ ዴቭል ኤንድ ሚስ ፕራይም፣
- ኢለቨን ሚኒትስ እና
- ዘ ዛሂር ናቸው፡፡



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner

በመቶ ዓመት አንድ የአንባቢውን ቀልብ የሚገዛ፣ ሕይወቱንም የሚለውጥ አንድ ድንቅ መጽሐፍ ይታተማል። አልኬሚስቱ እንዲህ ያለ ምሉዕ በኩለሄ መጽሐፍ ነው።

ፓውሎ ኮዔልሆ O Alquimista ብሎ የዛሬ ሃያ ዓመት በፖርቹጋል ቋንቋ ካሳተመው በኋላ ከሰማንያ በላይ በሚሆኑ ቋንቋዎች ተተርጉሞ በመላው ዓለም (ከ150 በላይ ሀገሮች) በብዙ ሚሊዮን ሕዝብ ተነቧል።

በርካታ ሃያስያን "በዚህ ዘመን የተገኘ ዘመን አይሽሬ (ክላሲክ) ሥራ" ብለውታል። በየትም ሀገር፣ በየትኛውም ዘመን ገና ብዙ የሚነበብ፣ ገና ብዙ የሚለውጥ፣ በረከቱ ለመቢ ትውልዶች የሚዳረስ ታላቅ መጽሐፍ ነው።

አልኬሚስቱ [illegible] እንደተረት በሚጥም፣ እንደሆነ [illegible] በሚያስበረብር፣ እንደ ፍልስፍናዊ ወግ በጽሞና በሚያሳስብ፣ እንደ ሊቦለድ ልብ በሚሰርቅ፣ እንደ የእምነት መጽሐፍት ልብን በሚገዛ አተራረክ አንባቢውን እንደማረከ እነሆ ሃያ ዓመት ሞላው። ኮዔልሆ እና ሳንቲያጎ ገና ለብዙ ሃያ ዓመታት "ህልሞቻችሁን ተከተሉ፣ እውን ታደርጓቸውም ዘንድ ታገሉ፣" እያሉ ይኖራሉ።

[illegible] ብር 15.00

EMAY Printers Plc